

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በቀረቡ የይግባኝ አቤቱታዎች ላይ በሕገ መንግስት ትርጉም እና የውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ

በፌዴሬሽን ምክር ቤት

የሕገ መንግስት ትርጉም እና የውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ

መስከረም /2016 ዓ.ም

ይግባኝ ባይ፡----------የሕግ ታራሚ አምዴ ቱሉ ሳምበታ

ተጠሪ ፡---------- የኦሮሚያ ፍትሕ ቢሮ (የኦ/አብ/ክ/መ/ሰ/ሸዋ ዞን

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ28/09/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም ሰበር ሰሚ ችሎት ድርጊቱን መፈጸሜ ሳይረጋገጥ በሀሰት ምስክር እና በተቀነባበረ ውሸት የተሰጠው ውሳኔ በደንብ ሳያጣራ አላግባብ የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 (1)፣ 20 (4፣ 6)፣ 37 እና 80 (3) መሰረት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት ለምክር ቤቱ በይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በሰሜን ሸዋ ማረሚያ ቤት በደገም ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ይግባኝ ባይ ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆኑ የተመሰረተ ነው፡፡ ከሳሽ በ1ኛ ክስ አንድ በሬ በ2ኛ ክስ ሁት በሬዎች እና 3ኛ ክስ ሁለት በሬዎች በመመስረት በተለያዩ ቀናት እና ቦታ ጨለማን ተገን በማድረግ ሰርቀው በአይሱዚ ሞኑዝ ሲሄዱ ተይዘዋል በማለት ክስ መስርቷል፡፡

ተከሳሾች ፍ/ቤት ቀርበው እምነት ክህደት ሲጠየቁ ክደው ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሾች ክደው የተከራከሩ ስለሆነ ዐ/ህግ ምስክር አቅርበው እንዲያስመሰክሩ አዞ ምስክሮች ቀርበው መስክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ተከሳሾች ስለተመሰከረባቸው እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቶ የመከላከያ ምስክሮችን አስቀርቦ ከተሰሙ በኋላ ተከሳሾች የተመሰከረባቸውን መከላከል ስላልቻሉ ጥፋተኛ በማለት በ13 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ይግባኝ ባይ ለሰሜን ሸዋ ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን ያስቀርባል በማለት ካከራከረ በኋላ ጥፋተኛ እነቱን በመቀበል ቅጣቱን በማሸሻል በ7 አመት ከ6 ወር እንደቀጣ ወስኗል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲሁም ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተው፡፡ የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልግም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴሬሽን ም/ቤት ትርጉም እንዲሰጣቸው ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር ከሳሽ በ1ኛ ክስ አንድ በሬ በ2ኛ ክስ ሁት በሬዎች እና 3ኛ ክስ ሁለት በሬዎች በተለያዩ ቀናት እና ቦታ ጨለማን ተገን በማድረግ ሰርቀው በአይሱዚ ጭነው ሲሄዱ ተይዘዋል በማለት ተከሶ የተሰጠ ቅጣት ላይ የቀረበ ይግባኝ እንደሆነ ተረድተናል፡፡

ይግባኝ ባይ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲሁም ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳግባቡ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተው እንደዚሁ የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ መዝገቡን ተመልክቶ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልግም በማለት ወስኗል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 731/15

ይግባኝ ባይ፡---------- ወ/ሮ ዘላለም ጎጂ መለሰ

ተጠሪ ፡---------- አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣሸቀጥ እና ሆቴሎች ንግድ አ/ማ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አማሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ23/10/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም ሰበር ሰሚ ችሎት ድርጊቱን መፈጸሜ ሳይረጋገጥ በሀሰት ምስክር እና በተቀነባበረ ውሸት የተሰጠው ውሳኔ በደንብ ሳያጣራ አላግባብ የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25፣ 35 ፣ 37 መሰረት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት ለምክር ቤቱ በይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ጉዳዩም የአሰሪ እና ሰራተኛ ክርክር ነው፡፡የአሁን ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው የቀረበ ክስ ነበር፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት በቀን 27/07/2010 ዓ.ም በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት ከጥቅምት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በግንዘብ ተቀባይነት የስራ መደብ በወር ደመወዝ ብር 3606 እየተከፈለኝ ሳገለግል ቆይቻለሁ፡፡ ከድርጅቱ አቶ ሮዛ መንበረ የተባለ ግለሰብ ጽፎ የሰጠኝ የዕቃ ግዢ ቼክ በድርጅቱ ሱፐር ቫይዘር ታይቶ አካውንቱ ዝግ ነው በመባሉ በግሌ ባለቸኩን በተደጋጋሚ ጊዜ ጠይቄ ከአቅሜ በላይ ሲሆን ለተጠሪ ድርጅት እና ለፖሊስ አሳውቄአለሁ፡፡

ነገር ግን ድርጅቱ በቀን 10/05/2000 ዓ.ም በተጻፈ የስነስርዓት እርምጃ ብር 10626 ከወርሃዊ ደመወዜ ላይ 1/3ኛ እየተቀነሰ ለድርጅቱ ገቢ እንዲሆን፣ የ2 ቀን ደመወዝ በቅጣት እንድከፍል እና የ2ኛ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ታህሳስ 11 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ደመወዝ ተከፍሎኝ ከስራ እንድመለስ ተደርጌ ነበር፡፡ እኔም ከላይ የተጠቀሰው እርምጃ አላግባብ ስለሆነ እንዲስተካከልልኝ በ19/05/2010 ዓ.ም ለድርጅቱ አመልክቼ መልስ እየተጠባበቅሁ እያለ ስራ ገበታቸው ላይ ከ5 ቀን በላይ አልተገኙም በማለት ያለማስጠንቀቂያ በ16/05/2010 ዓ.ም ከስራ አሰናብቶኛል፡፡

ተጠሪ የወሰደው የማሰናበት እርምጃ ሕገወጥ በመሆኑ ተጠሪ ወደስራ እንዲመለስልኝ ይወሰንልኝ ይህ ካልሆነ በአማራጭ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተጠይቆ የአሁን ይግባኝ ባይ ከስራ የተሰናበቱት ያለበቂ ምክንያት ከጥር 16 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ ለተከታታይ ከ5 የስራ ቀናት በላይ በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ነው፡፡

የስር አመልካች ከስልጣናቸው ውጪ ስንቅ የሌለው ደረቅ ቸክ በመቀበል ከድርጅቱ ግምቱ የብር 10,626.00 የሚያወጣ ዕቃ በመስጠታቸው በዲሲፕሊን ተከሰው እንዲባረሩ ከተደረገ በኋላ በሰራተኛው ስምምነት መሰረት ማባረር እንደማንችል ተነግሮን መባረሩ ቀርቶ ከደሞዛቸው 1/3 እየተቆረጠ የሚያልቅ ከላይ የተጠቀሰውን ብር እንዲከፍሉ ተወስኖ እያለ የአሁን ይግባኝ ባይ በስራ ገበታቸው በተከታታይ 5 ቀናት ከስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው በህጉ መሰረት የተሰናበቱ ስለሆነ የሚከፈል ደሞዝም ሆነ ጥቅማጥቅም የለም በማለት መልስ ሰጠዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ይግባኝ ባይ ከጥር 16 እስከ ጥር 25/2010 ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት በላይ ሥራ መቅረታቸውን አምነው ነገር ግን የቀረሁት ዕዳ አለብኝ የተባለው ገንዘብ ከደመወዜ ላይ እንዳይቆረጥ ገልጨ መልስ እስኪሰጠኝ እየጠበቅሁ ነበር በማለት የገለጽ ሲሆን አመልካች በተወሰደባቸው አስተዳደራዊ እርምጃ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው ለሚመለከተው አካል ቅሬታ አቅርበው ስራቸውን መቀጠል እንጂ ከስራ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት መቅረታቸው ህጋዊ ባለመሆኑ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27(1-ለ) መሰረት ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍ/ቤት እና ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ አቅርበው ተቀባይነት የለውም በሚል ተዘግቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ አመልክተው ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ተሰጧል፡፡

አሁንም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ ትርጉም እንዲሰጣቸው ለፌዴሬሽን ም/ቤት ይግባኝ ብለዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር ድርጅቱ በቀን 10/05/2000 ዓ.ም በተጻፈ የስንስርዓት እርምጃ ብር 10626 ከወርሃዊ ደመወዜ ላይ 1/3ኛ እየተቀነሰ ለድርጅቱ ገቢ እንዲሆን፣ የ2 ቀን ደመወዝ በቅጣት እንድከፍል እና የ2ኛ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ታህሳስ 11 ቀን 2009 ዓ.ም

ጀምሮ ያለው ደመወዝ ተከፍሎአቸው ከስራ እንዲመለሱ በደረጉ አግባብነት ያለው ውሳኔ ነበር ነገር ግን የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ተጠቃሚ ሆነው ማለትም ወደ ስራ ተመልሰው እየሰሩ ቅሬታቸውን ማቅረብ ሲገባቸው በስራ መደባቸው ላይ ሳይገኙ በመቅረታቸው የተሰጠው ፍርድ ከሕግ ውጪ ነው ለማለት እንደማይቻል ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 739/15

ይግባኝ ባይ፡-..... ወ/ሮ በቀለች ድንቁ ከቶ

ተጠሪ ፡-..... አዲስ ፋና ጠቅላላ ሽቀጣሽቀጥ እና ሆቴሎች ንግድ አ/ማ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ21/11/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በጋሰራ ወረዳ ፍ/ቤት የተፈጸመ የሕገ መንግስት ጥሰት በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ሳይታረም እስከ ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ድረስ በመድረሱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 (1) ፣ 79 (3) 40 (4)፣ መሰረት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት ለምክር ቤቱ በይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት በባሌ ዞን በጋሰራ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ይግባኝ ባይ የስር አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት የመሬት ጉዳይ ክርክር ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የሚች እናቴ ወ/ሮ አበበች አያኔ እና አባቴ አቶ ድንቁ ከቶ ይዞታ መሬት በ1967 ዓ.ም ጀምሮ የሚጠቀምበትን መሬት የከተማ መስተዳድሩ ካሳ ሳይከፍለን እና ተተኪ ቦታ

ሳይሰጠን ስለያዘብን ቀርቦ ተጠይቆ ከሌሎች ወራሾች ጋር የሚኖረኝን ድርሻየን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ መስርተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መልስ ሲሰጥ የጠየቀው መሬት የወላጆቿ አይደለም፡፡ የካሳ ጥያቄ በአዋጅ 455/97 መሰረት በመጀመሪያ መቅረብ ያለበት ለፍርድ ቤት አይደለም፡፡ አከራካሪው መሬት ይዞታ በከተማ መስተዳደሩ ስር የገባው በ1983 ዓ.ም ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል፡፡መሬቱ በአሁኑ ስዓት ለነዋሪዎች የተከፋፈለ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ መሬቱ በ1979 ዓ.ም ለከተማው አስተዳድር የገባ እና በ1983 ዓ.ም ከተማ አስተዳድሩ ለሕዝብ አከፋፍሏል፡፡መሬቱ መንግስት ከወሰደው 26 አመት ያለፈው ስለሆነ ክርክሩ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ እና በሰበር ችሎት ለክልሉ ፍ/ቤቶች እንዲሁም ለፌደራሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት መዝገቡን ተዘግቷል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በነዚህ ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ መዝገቡን መርምሮ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴሬሽን ም/ቤት በይግባኝ ትርጉም እንዲሰጣቸው አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር መሬቱ በ1979 ዓ.ም ለከተማው አስተዳድር የገባ እና በ1983 ዓ.ም ከተማ አስተዳድሩ ለሕዝብ እንዳከፋፈለ እና መሬቱ በመንግስት እጅ ከገባ 26 አመት ያለፈው ስለሆነ ይህንን ጉዳይ እንደገና ተመልሶ ማየቱ አግባብነት እንደሌለው በየደረጃው የተሰጠውን ውሳኔ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

ይግባኝ ባይ፡---------- ወ/ሮ ዘሪቱ ዋዳ

ተጠሪ ፡---------- አርባ ምንጭ ግብርና ምርምር ማዕከል

. **<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>**

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ25/11/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም ፍ/ቤቱ የወጭ እና ኪሳራ እንዲሁም የሞራል ካሳ ክፍያ ሳይወስንልኝ በመቅረቱ የሕገ መንግስት ጥሰት ስለተፈጸመብኝ ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት ለምክር ቤቱ በይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በአርባ ምንጭ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ጉዳዩም የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነትን የሚመለከት ነው፡፡የጉዳዩ መነሻም የአሁን ይግባኝ ባይ የስር አመልካች በ08/08/2010 ዓ.ም የተሰጣቸውን የሥራ ስንብት ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ይህ4ን የስንብት ደብዳቤ በመቃወም ይግባኝ ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ለፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በ25/03/2010 ዓ.ም ለአስተዳደር ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ በገዛ ፈቃዴ ስራየን መልቀቄን ሳላቀርብ ሴት በመሆኔ ብቻ በቂም በቀል በሰራተኛ የሥዓት መቆጣጠሪያ እንዳልፈርም ከመስሪያ ቤቱ ግቢ በዘበኛ እንድወጣ በማድረግ ከስራየ አሰናብተውኛል፡፡

በዚህ ምካንያት ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ጥቅማጥቅም ያላገኘሁ ስለሆነ እንዲሁም ከ01/06/2010 ዓ.ም ጀምሮ ያላንዳች ምክንያት ደሞወዝ ተከልክያለሁ ደሞወዜም እንዲከፈለኝ ወደ ስራየም እንድመለስ ብጠይቅ ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ ነገር ግን ዝም ብለሽ ቢሮ ግቢ ባሉኝ መሰረት ቢሮ እየገባሁ ነበር፡፡ችግሩ ተፈቶ ወደ ስራየ እንድመለስ ለሕዝ ዕንባ ጠባቂ አቅርቤ ወደ ስራየ እንድመለስ ቢወስንልኝ መ/ቤቱ ሊመልሰኝ

አልቻለም፡፡ስለሆነም ፍ/ቤቱ ወደ ስራየ እንድመለስና የተቋረጠ ደሞወዜ እንዲከፈለኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መልስ ሲሰጥ በስር ፍ/ቤት አመልክታ ወደ ስራዋ እንድትመለስ ተወስኖላት ሰነድ ያቫር ተመድባ ነበር ነገር ግን ቀርባ ስራውን መስራት ባለመፈለግ ወደ መ/ቤት አልተመለሰችም እንዲሁም ከመ/ቤቱ በመጥፋት የስዓት መቆጣጠሪያ ላይ አልፈረመችመው፡፡ ስለሆነም ከመ/ቤቱ በመጥፋቷ በሕግ አግባብ የተሰናበተች እንጂ እናዳትፈርም የከለከላት የለም ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ እንዲያጠናልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ እና ክርክር ከመረመረ በኋላ መ/ቤቱ የአሁን ይግባኝ ባይን ያሰናበታት ሕጉ በሚፈቅደው የመጥሪያ ማስታወቂያን የጠበቀ አይደለም በተግቢው ቀኖቹ ተቆጥረው ሲሰሉ በሕጉ ላይ የተቀመጠውን ጊዜ አያሟላም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡በተጨማሪም የተቋረጠ ደሞወዝ እና ጥቅማጥቅም በፋይናንስ ሕግ መሰረት ይከፈላት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በከፊል ቅሬታ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ የይግባኝ አቤቱታ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን በችሎት ሲጠየቁ አሁንም አልመለሰኝም በማለት አመልክተው እንደነበረ እና ፍ/ቤቱም የአስተዳድሩ ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቶ ይስር አመልካች የአሁን ይግባኝ ባይ አልተፈጸመልኝ ያሉት አቤቱታ በአፈጻጸም ጊዜ ሊቀርብ የሚገባ ነው በማለት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ የስር አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ እና ለፌደራሉ ጠ/ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት ዘግተውታል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተው፡፡ የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩን ተመልክቶ ወደስራ እንዲመለሱ አመልክተው እንዲመለሱ የተወሰነላቸው ስለሆነ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ ትርጉም እንዲሰጣቸው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር የአሁን ይግባኝ ባይ ወደ ስራዋ እንድትመለስ ተወስኖላት ሰነድ ያዥ ተመድባ ነበር ነገር ግን ቀርባ ስራውን መስራት ባለመፈለግ ወደ መ/ቤት አልተመለሰችም እንዲሁም ከመ/ቤቱ በመጥፋት የስዓት መቆጣጠሪያ ላይ እንዳልፈረመች እና በሕግ አግባብ የተሰናበተች እንደሆነ ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ እና ክርክር ከመረመረ በኋላ መ/ቤቱ የአሁን ይግባኝ ባይን ያሰናበታት ሕጉ በሚፈቅደው የመጥሪያ ማስታወቂያን የጠበቀ አይደለም በተገቢው ቀኖቹ ተቆጥረው ሲሰሉ በሕጉ ላይ የተቀመጠውን ጊዜ አያሟላም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡በተጨማሪም የተቋረጠ ደሞወዝ እና ጥቅማጥቅም በፋይናንስ ሕግ መሰረት ይከፈላት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በከፊል ያቀረቡት ቅሬታ ግን ሥነስርዓት ያጠበቀ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔ እንደተሰተ ማወቅ ተችሏል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 741/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ጌታቸው ሁሴን

ተጠሪ ፡---------- ደቡብ ወሎ ዞን ዐ/ህግ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፤</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ18/11/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በሐሰት በቀረበ የአዲት ሪፖርት አላግባብ ተወስኖብኝ ለትርጉም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርቤ በደንብ ሳያጣራ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሰረት ፍትህ

የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቴ በትርጉም እንዲያስከብርልኝ በማለት ለምክር ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብ/ክ/መ/ በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች እና ያልማዘር አሊ ተከሳሾች ሆነው የተጀመረ በአዲት የተገኘ ገንዘብ ጉድለትን የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ክስ አመልካች በአልብኮ ወረዳ ገንዘብ እና ኢ/ል/ቅ/ጽ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ ሆኖ ሲሰራ ከታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም የሰራው አዲት ሲደረግ የብር 366825.96 ጉድለት ተገኝቶበታል፡፡

ተከሳሽም ለብር 80,000.00 ጉድለት የአድነት እና የነጠላ የዋስትና ግዴታ ገብቷል፡፡ስለሆነም በጉድለቱ የተረጋገጠውን የገንዘብ መጠን የአዲት ስራው ከተጠናቀቀበት ግንቦት 2011 እስከ 2007 ዓ.ም የሚታሰብ ወለድ እና የክርክር ወጪዎችን እንዲከፍሉ እንዲሁም ተከሳሽ ብር 80,000.00 እንዲከፍል እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የአሁን ይግባኝ ባይ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መልስ ሲሰጥ የነበረብኝ ጉድለት ብር 2,054.00 ብቻ መሆኑ ተረጋግጦ ከፍየለሁ፡፡ሌላ ጉድለት የሌለብኝ ስለመሆኑ በወረዳው ም/ቤት እና በሌሎች ተቋማት ቀርቦ ተረጋግጧል ነገር ግን መተማመኛ ያልፈረምሁበት የአዲት ምርመራ ላይ የቀረበው ክስ ሙሉ በሙሉ ሃሰት ነው፡፡የስራ መደቡን ለቅቄ በግዥ ስራ ላይ ተመድቤ እየሰራሁ ሁኔታ ጉድለት አለ ሊባል አይገባም በመንግስት ወጪ የአዲት ስራው በክልል አዲተሮች ይጣራልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ መዝገቡን መርመሮ የቀረቡትን ማስረጃወችንም አጣርቶ የአሁን ይግባኝ ባይ የተጠቀሰውን ዋና ገንዘብ የአዲት ስራው ከተጠናቀቀበት ግንቦት 11 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብበት 9% ወለድ ጋር ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በአማራ ክልል እስከ ሰበር ሰሚ በየደረጃው አመልክተው ተቀባይነት አላገኙም እንዲሁም ለፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ቀርቦም መሰራታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት መዝገቡ በመዘጋቱ ለሕገ መንግስት

ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አቅርበው የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር የአሁን ይግባኝ ባይ የተጠቀሰውን ዋና ገንዘብ የአዲት ስራው ከተጠናቀቀበት ግንቦት 11 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብበት 9% ወለድ ጋር ሊከፍል ይገባል በማለት እንደተወሰነባቸው ፣ በዚህም ውሳኔ ቅሬታ ደረጃውን ጠብቀው እስከ ሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ተቀባይነት እንዳላገኙ ከመዝገቡ መረዳት እለናል፡፡

በቀረበ የሀሰት አዲት ሪፖርት መሰረት ተደርጎ ተወሰነብኝ በማለት ያቀረቡ ቢሆንም በሀሰት የቀረበውን ሪፖርት ለማስተባበል የቻሉበት ነጥብ ከመዝገቡ ላይ ማግኘት አልቻልነም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 750/15

ይግባኝ ባይ፡--------- አቶ ዘላለም ሌጂሳ ሰሚ

ተጠሪዎች፡---------- እነ ዮሐንስ ተሾመ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ16/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአቤቱታቸው ይዘትም በውርስ ንብረት ክርክር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ ትርጉም እንዲሰጠኝ ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ አቅርቤ በደንብ ሳያጣሩ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የተሰጠው

ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 መሰረት ንብረት የማፍራት ሕገ መንግስታዊ መብቴን እንዲያስከብርልኝ በማለት ለምክር ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሳሽ የአሁን ይግባኝ ባይ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ነበር፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በውርስ ንብረት ክርክር ላይ የተመሰረተ ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታቸው አቶ ተሾመ ከተማ እና እናታቸው ወ/ሮ ፊለቀች አገኘሁ በሕጋዊ ጋብቻ ተጋብተው ሲኖሩ አባታቸው ጥቅምት 1986 ዓ.ም እናታቸው ደግሞ በ1988 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፡፡

ወላጆቻቸው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 27 ቀበሌ 11 ውስጥ 400 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት እና ይዞታ አፍርተዋል፡፡በወቅቱ ልጆች ለአቅመ አዳም ስላልደረሱ በአያታቸው ወ/ሮ ወርቅነሽ አለምነህ ሞግዚታቸው ሆነው ሲተዳደሩ ቆይተዋል፡፡ቤቱ በአጎታቸው እጅ ሆኖ ሲጠቀሙበት ቆይተው በኋላ እንዲያስረክቡአቸው ሲጠይቁ ፍቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ፍ/ቤቱ እንዲያስለቅቅላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት ክስ ላይ መልስ እንዲሰጡ ታዝዘው በተጠሪዎች በኩል በመ/ቁ 1976 በ03/04/94 ዓ.ም የተፈረደ ፍርድ ተብሎ በማስረጃነት ቀረበው ሰነድ ፍርዱ ከተሰጠ 16 ዓመት ከ7 ወር በኋላ የቀረበ ማስረጃ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር አንቀጽ 384 መሰረት በይርጋ የታገደ ነው በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

በፍሬ ነገር ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ በፍርድ ላይ አለ የተባለው ቤት የለም፡፡ በስሜ የተመዘገበው ካርታ ላይ ያለው ቤት የራሴ ነው፡፡ ቦታውም የመንግስት ነው ተብሎ መንግስት ለ99 አመት በሊዝ አስተላልፎልኛል፡፡የሊዙንም ገንዘብ ለመንግስት ከፍየአለሁ፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ በነጻ ያሰናብተኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ መቀወሚያውን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት መጋቢት 28 ቀን 1991 ዓ.ም አቶ አሚር መሐመድ የተባሉ ግለሰብ በከሳሽነት በስር ፍ/ቤት አመልካች ደግሞ በተከሳሽነት ቀርበው ያላግባብ በጉልበት መያዛቸውን በመግለጽ

ቤቱን እንዲለቁላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ነበር፡፡ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ቤቱ የአቶ አሚር መሀመድም ሆነ የአመልካች እንዳልሆነ እና ይልቁን ቤቱ የተጠሪዎች የውርስ ሀብት መሆኑ ተረጋግጦ ለተጠሪዎች ሞግዚት እንዲሰጥ መወሰኑን ፍ/ቤቱ በቀን 03/04/94 ዓ.ም በመቁጥር 1975/91 ውሳኔ መግንዘብ ይቻላል፡፡ምስክሮችም ቤቱ የሚኞ አቶ ተሸመ ከተማ እና ወ/ሮ ፈለቀች አገኘሁ ንብረት እንደሆ እና የአሁን ይግባኝ ባይ ምስክሮች ግን እንዳልመሰከሩ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ሕግን ባልተከተለ መንገድ የያዙትን ቤት ለስር ከሳሾች ለአሁን ተጠሪዎች እንዲያስረክብ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ይግባኝ ባይ ለፌደራል ጠ/ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ አቅርበው ውድቅ ተደርጓል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አመልክተዋል፡፡አጣሪ ጉባኤው በስልጣኑ ተጠቅሞ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴሬሽን ም/ቤት የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸውመ ይግባኝ ብለዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር ወላጆቻቸው በሕይወት ስላልነበሩ የተጠቀሰው ቤት እና ይዞታ በወቅቱ ልጆች ለአቅመ አዳም ስላልደረሱ በአያታቸው ወ/ሮ ወርቅነሽ አለምነህ ሞግዚታቸው ሆነው ሲተዳደሩ እንደበር እንዲሁም ቤቱ በአጎታቸው እጅ ሆኖ ሲጠቀሙበት ቆይተው በኋላ እንዲያስረክቡአቸው ሲጠይቁ ፍቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸውን እና ወደ ክስ እንዳመሩ ከመዝገቡ መረዳት እለናል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ቤቱ የአቶ አሚር መሀመድም ሆነ የአመልካች እንዳልሆነ ባጠቃላይ ቤቱ የሚኞ አቶ ተሾመ ከተማ እና ወ/ሮ ፈለቀች አገኘሁ ንብረት እንደሆ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ደረጃውን ጠብቆ እስከ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ደርሶ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው

ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 751/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ሲሳይ አዲ

ተጠሪ፡----------ትራንስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ16/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር የፍርድ ባለመብት በመሆን የተረጋገጠልኝን መብት ተግባራዊ እንዳይሆን በሐሰት በቀረበ የኦዲት ሪፖርት አላግባብ ተወስኖብኝ ይህንንም ትርጉም እንዲሰጠኝ ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ አቅርቤ በደንብ ሳያጣራ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሰረት ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቴን በትርጉም እንዲያስከብርልኝ በማለት ለምክር ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በስር ፍ/ቤተ ይግባኝ ባይ አመልካች ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ላይ የቀረበ ክርክር ነው፡፡የአሁን ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የሆኑ በአሁን ተጠሪ ድርጅት ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለ አላግባብ ከስራ ተሰናብቼአለሁ በማለት የተደረገ ክርክር ነው፡፡

የክሱ ይዘትም በአጭሩ በተጠሪ መ/ቤት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥሬ እያገለገልሁ እያለሁ ከአዲስ አበባ ወደ ሁመራ እንድዛወር አድርጎ ከ10 አመት በላይ አገልግየ ዝውውር ስጠይቅ ተከልክየአለሁ፡፡ በሕብረት ስምምነቱ መሰረት አንድ 3 አመት ያገለገለ ሰራተኛ ዝውውር የማግኘት መብት አለውው፡፡ነገር ግን ተጠሪ ያለ አግባብ ሰኔ 2013 ዓ.ም ወደ መቀሌ እንድዛወር አሳውቆኛል፡፡

ነገር ግን በወቅቱ መቀሌ የፀትታ ችግር በመሆሩ ወደ መቀሌ መሄድ ባለመቻሌ የስራ ውለን እንዲቋረጥ አድርጓል፡፡ ስለሆነም ስንብቱ አላግባብ ስለሆነ የበረሃ አበል ክፍያ፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ የካሳ ክፍያ፣ ለዘገየበት እና የትርፍ ስዓት ክፍያ እንዲከፈለኝ ሲሌ ዳኝነት ጠየረቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመለካቸ ለተከታታይ 5 ቀናት በስራ ገበታቸው ባለመገኘት ውሌ በሕጋዊ መንገድ የተቋርጠ መሆኑን፣ መቀሌ በወቅቱ የጸጥታ ችግር ያልነበረ መሆኑን፣ ሌሎች ሰራተኞች ወደ መቀሌ ተዛውረው በስራ ገበታቸው ላይ መሆኑን፣ ሶስት አመት የሚለው በሕብረት ስምምነት ውስጥ የሌለ መሆኑን፣ ነገር ግን በራሱ ፍላጎት ሁመራ የቆየ መሆኑን፣ የአበል ክፍያ በይርጋ የሚታገድ ስለሆነ ሊጠይቁ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረመ በኋላ የስራ ውሌ የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው ስለሆነም ብር 90,000.00 (ዘጠና ሽህ ብር ይከፈለው የአበል ክፍያ በይርጋ የተቋረጠ ነው፡፡የበረሃ አበል ደግሞ የሕብረት ስምምነቱ ካለቀ በኋላ አይሰራም ሊከፈል አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ውሳኔ እስከ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ድርሶ ፀንቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አቅርበው ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴሬሽን ም/ቤት በይግባኝ እንዲታረምላቸው ይግባኝ ብለዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር የስራ ውሌ የተቋረጠው ከሕግ ውጭ እንደሆ ለዚህም ብር 90,000.00 (ዘጠና ሽህ ብር) ይከፈል እንደተባለ የአበል ክፍያ በይርጋ የተቋረጠ መሆኑን ፣የበረሃ አበል ደግሞ የሕብረት ስምምነቱ ካለቀ በኋላ ሊከፈል እንደማይገባ ከመዝገቡ መረዳት ችለናል፡፡

በየደረጃው ያለ ፍ/ቤቶችም ሆኑ የሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የአሁን ይግባኝ ባይን አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርገዋል፡፡ተጠቃሎ ሲታይ ሕግን መሰረት ተደርጎ የተሰጠ ውሳኔ የይግባኝ ባይን መብት የጣሰነው ማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 758/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ኡስማን ቡሴር

ተጠሪ፡--------- አቶ ታሪኩ ገነቴ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ26/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በመሬት ጉዳይ ክርክር የሁከት ይወገድልኝ ሲሆን አከራካሪው ካርታ እንዲመክን በአፈጻጸም የተገድድሁ ስለሆነ በማለት አመልክቸ አላግባብ ተወስኖብኝ ይህንንም ትርጉም እንዲሰጠኝ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርቤ በደንብ ሳያጣራ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 መሰረት የንብረት ሕገ መንግስታዊ መብቴን በትርጉም እንዲያስከብርልኝ በማለት ለምክር ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 7ኛ የፍተሐብሔር ችሎት የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሲሆን ጉዳዩ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ክርክር ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ይዘት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ቁጥር አዲስ የሆነው በ175 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ባለ ሁለት ፎቅ ቤት ሰርቼ በ1996 ዓ.ም ጀምሮ እየኖርሁ እያለ ከዚህ ይዞታ ጋር ኩታ ገጠም እና ስፋቱ 175 ካ.ሜ የሆነ መሬትን በቆር ቆሮ አጥሮ ሰርቪስ ቤት ሰርቶበት የከተማ መስተዳደር ባወጣው መመሪያ መሰረት ወደ ህጋዊ ይዞታ እንዲካተትለት በ2001 ዓ.ም ጥያቄ አቅርቧል፡፡

2ኛ ተከሳሽም ይዞታው እንደሚካተትልኝ ገለልጸልኝ በመጠባበቅ ላይ ነኝ፡፡ ይሁን እንጅ 2ኛ ተከሳሽ እኔ የያዝኩትን እና ሰርቪስ ቤት በሰራሁበት በዚህ ይዞታ ላይ ለአሁን አመልካች ከህግ ውጪ ካርታ ሰርቶለት ለመስጠት ወደ ይዞታየ እየተመላለሱ ሁከት እየፈጠሩብኝ ስለሆነ ሁከቱ እንዲወገድልኝ በማለት አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዞ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ በካርታ ቁጥር ቦሌ 8/10216/3/8673/236071/01 በስሜ ተመዝግቧል፡፡ ይዞታውን ከወ/ሮ ሃዋ መሐመድ ሐምሌ 7 ቀን 1998 ዓ.ም በተጻፈ የቤት ሽያጭ ውል የገዛሁት ነው፡፡

ውሉም በውል እና ማስረጃ ተመዝግቦ በክ/ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ቤቱ በስሜ ተመዝግቧል፡፡ግብሩን እየከፈልኩበት ነው፡፡አካራካሪው ይዞታ 175 ካ.ሜ የሆነ እራሱን ችሎ ሊለማ የሚችል ሆኖ ሳለ ተጠሪ ወደ ራሱ ይዞታ እንዲከታተልለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም በማል ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ቤቱን ገዛሁ የሚለው ከወ/ሮ ሃዋ መሐመድ ተወካይ አቶ ሙባረክ ፈታህ ነው፡፡ወ/ሮ ሃዋ መሀመድ በሃሰት ያገኙትን ማስረጃ መሰረት አድርገው ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ይህንኑ ውል መሰረት ተደርጎ ወደ አመልካች የሚዞር የባለይዞታነት ማረጋገጫም ተቀባይነት የለውም፡፡

ይልቁንም አከራካሪው ቤት እና ይዞታ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ሰርቪስ ቤት ሰርቸበት እየኖርኩበት ያለሁት እኔ ነኝ፡፡አመልካች ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ይዞታው የመጣው ከ2012 ዓ.ም ሲሆን የሁከቱ ይወገድልኝ ክስ ስለቀረበበት እርሱ ደግሞ የመፋለም ክስ ያቀረበ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አከራካሪው ይዞታ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ እጅ ያለ መሆኑን፣በይዞታው ላይ ተጠሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ሰርቶ ያለ ምንም ተቃውሞ እየተጠቀመ መሆኑን፣ ቤቱን ለአመልካች ሸጠዋል የተባሉት ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ ወደ ይዞታው መጥተው የማያውቁ ነገር ግን ይዞታው በሊዝ፣ በእጣ እንደደረሳቸው ተደርጎ፣ ሐሰተኛ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ፣ ሐሰተኛ ፋይል ተከፍቶ እና ሐሰተኛ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው መሆኑን የፌደራል የፖሊስ ወንጀ ምርመራ ባደረገው ምርመራ አጣርቶ እንዲሁም የክ/ከተማ መሬት አስተዳደርም ለወ/ሮ ሃዋ መሐመድ የሰጠው ካርታ አለመኖሩ እና ካርታው የተጫበረበረ ስለሆነ በቤቱ

ላይ ባለቤት ሊያደርጋቸው የሚችል መብት ስለሌላቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ከተመረመረ በኋላ አያስቀርብም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን መርምሮ ያስቀርባል ካለ በኋላ አከራክሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽድቋል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሕገ መንግስቱ በተሰጠው ስልጣን ተጠቅሞ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው ለፌዴሬሽን ም/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር አከራካሪው ይዞታ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ እጅ ያለ መሆኑን፣በይዞታው ላይ ተጠሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ሰርቶ ያለ ምንም ተቃውሞ እየተጠቀመ እንደኖረ፣ ቤቱን ለአመልካች ሸጠዋል የተባሉት ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ ወደ ይዞታው መጥተው የማያውቁ ነገር ግን ይዞታው በሊዝ፣ በእጣ እንደደረሳቸው ተደርጎ፣ ሐሰተኛ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ፣ ሐሰተኛ ፋይል ተከፍቶ እና ሐሰተኛ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው መሆኑን የፌደራል የፖሊስ ወንጀ ምርመራ ባደረገው ምርመራ አጣርቶ እንዲሁም የክ/ከተማ መሬት አስተዳደርም ለወ/ሮ ሃዋ መሐመድ የሰጠው ካርታ አለመኖሩ እና ካርታው የተጫበረበረ ስለሆነ በቤቱ ላይ ባለቤት ሊያደርጋቸው የሚችል መብት እንደሌላቸው ከፋይሉ መረዳት እንደቻልኝ፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ወርቁ ታደሰ

ተጠሪ፡---------- የኢትዮጵያ አይር መንገድ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ24/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል በተደረገ የስራ ውል ክርክር ፍ/ቤቱ አላግባብ ተወስኖብኝ ትርጉም እንዲሰጠኝ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርቤ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ ሕገ መንግስታዊ መብቴን በትርጉም እንዲያስከብርልኝ በማለት ለምክር ቤቱ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በስር ፍ/ቤተ ይግባኝ ባይ አመልካች ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ላይ የቀረበ ክርክር ነው፡፡የአሁን ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የሆኑ በተጠሪ ድርጅት ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለ አላግባብ ከስራ ተሰናብቼአለሁ በማለት የተደረገ ክርክር ነው፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ የስር አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረው በPSGE ኦፕሬተርነት ሲሰሩ ቆይተው በ2000 ዓ.ም በቀረበባቸው የወንጀል ክስ ለ7 አመት ከ9ወር ሲከራከሩ መቆየታቸውን በቀን 19/05/2008 ዓ.ም ከወንጀል ክሱ በነጻ መሰናበታቸውን ፍርዱ በይግባኝ ምክንያት መዘግየቱን ከተጠረጠሩበት ወንጀል ነጻ መውጣታቸውን ነገር ግን ወደ ስራ እንዲመለሱ ተጠሪን ቢጠይቁም ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ እንዳልሆነ ገልጿል፡፡

በመሆኑም ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወደ ስራ ካልተመለሱም ደግሞ የ2 አመት የአመት እረፍታቸው ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ያልተከፈላቸው የ7 አመት ከ9 ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የዘገየበት የስራ ስንብት የካሳ ክፍያዎች ከነወለዱ እንዲከፈላቸው የስራ ልምድ እንዲሰጣቸው እንዲወሰንላቸው አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ታዘው ከስራ የተሰናበቱት በወንጀል ተጠርጥረው በእስር ምክንያት ከ6 ወር በላይ ከስራ ስለቀሩ በድርጅቱ ህብረት ስምምነት መሰረት በህጋዊ መንገድ ተሰናብተዋል፡፡ወደ ስራ ልመለስ የሚለውም ሆነ የክፍያ ጥያቄው ከረጅም አመታት በኋላ የቀረበ በተለይም በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ ከተቀመጠው ጊዜ በኋላ ቀረበ ነው፡፡

እስሩ ክስ እንዳያቀርቡ ምክንያት አይሆንም፣ በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ በእስር ላይ አልነበሩም፣ እስሩ በቂ ምክንያት ነው ሊባል እንኳን በዋስትና ከእስር ተፈተው በነበሩበት ጊዜ መጠየቅ ይችሉ ነበር፣ ከወንጀል ክሱ በነጻ ከተሰናበቱ ከጥር 19/2008 ዓ.ም በኋላ በ10 ቀን ውስጥ ማቅረብ አልቻሉም በማለት ክሱ በይርጋ ውድቅ እንዲደረግላቸው አመልክተዋል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ አመልካች ከእስር ከተፈቱ በኋላ መጠየቅ ይችሉ ነበር፡፡ በወንጀል መዝገቡ ውሳኔ ከተሰጣቸው ቀን ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠርም 3 ወር ያለፈው በመሆኑ ወደ ስራ ልመለስ ብለው ያቀረቡት ክስ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 (2) መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ክፍያዎችን በሚመለከትም የቀረበው ጥያቄም መቅረብ ካለበት ከ6 ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 162 (3) መሰረት ጥያቄያቸው በይርጋ ያታገዳል ሲል የስራ ልምዳቸው እንዲሰጥ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ይግባባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፤፡ይግባኙን የመረመረው ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ምክንያት ጠቅሶ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽድቋል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት አመልክተው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚህ የሰበር ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም እንዲሰጣቸው አመልክተው፣ ጉባኤው በተሰጠው ሕገ መንግስታዊ ስልጣን መሰረት መርምሮ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴሬሽን ምክር ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ገዳዩ ሲመረመር አመልካች ከእስር ከተፈቱ በኋላ ማንሳት የነበረባቸውን መብቶች ወዲያውኑ ጊዜው ሳያልፍ አንስተው መጠየቅ ለምን እንዳልቻሉ ማወቅ አልተቻለም፡፡

በወንጀል መዝገቡ ውሳኔ ከተሰጣቸው ቀን ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር 3 ወር ያለፈው በመሆኑ ወደ ስራ ልመለስ ብለው ያቀረቡት ክስ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 (2) መሰረት በይርጋ ቀሪ እንደሚደረግ፡፡

ክፍያዎችን በሚመለከትም የቀረበው ጥያቄም መቅረብ ካለበት በ6 ወር ውስጥ ቀርበው መብታቸው እንዲከበር መጠየቅ ነበረባቸው ነገር ግን በአዋጁ አንቀጽ 162 (3) መሰረት ጥያቄያቸው በይርጋ እንዲታገድ መሆኑ በሌላ በኩል ግን የስራ ልምዳቸው እንዲሰጥ እንደተወሰነ፡፡ ይህንን ውሳኔ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች እና የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም እያፀደቁት እንደመጡ ተገንዝበናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 761/15

ይግባኝ ባይ፡- ---------- እነ አቶ በላቸው ሙላት በየነ

ተጠሪ፡---------- አንበሳ የከተማ አውቶቢስ አገልግሎት ድርጅት

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ29/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለፌደሬሽን ምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል በተደረገ የስራ ውል ክርክር ፍ/ቤቱ አላግባብ ወስኖብኝ ይህንንም ትርጉም እንዲሰጠኝ ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርቤ በደንብ ሳያጣራ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስላልሆነ ሕገ መንግስታዊ መብቴን በትርጉም እንዲያስከብርልኝ በማለት ለምክር ቤቱ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የአሰሪ እና ሰራተኛ የሥራ ውል ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን የቀረበ ነበር፡፡ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የአሁን ይ/ባይ በአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ተከሻሽ ጋር በየዓመቱ የሚታደስ ከሐምሌ 01 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ የስራ ውል ተፈራርመናል፡፡

ተጠሪ በዚህ ጊዜ የሚያገለግል ነጻ የአውቶቢስ ትኬት ሰጥቶናል እንዲሁም በየወሩ እየታደሰ የሚያገለግል ውል ይዘን ስንሰራ ከቆየን በኋላ ያላንዳች ማስጠንቀቂያ ነሐሴ 01 ቀን 2010 ዓ.ም ስራውን አቋርጦብናል፡፡ አሰሪው ያደረገው የስራ ማቋረጥ ከሕግ ውጪ ተደረገ ስለሆነ የ6 ወር ደሞወዝ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ የሁለት ወር ደሞወዝ፣ ከሐምሌ 2010 ዓ.ም እስከ ሰኔ ወር 2011 ዓ.ም ድረስ የነጻ ትኬት በሚያስከፍለው ዋጋ መሰርት የ11 ወር ብር 6,600 00 ፣ በሕብረት ስምምነት መሰረት የአመልካች 3 ቤተሰብ አባላት የነጻ መጓጓዣ ትኬት የ11 ወር ለየአንዳንዱ አመልካች ብር 19,600.00 የስንብት ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎችን በመዘርዘር ተጠሪ እንዲከፍለኝ በማለት ክስ መስርተዋል፡፡

ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ታዝዘው የአሁን ይግባኝ ባይ የስር ከሳሽ በሕግ አግባብ በጥሮታ ተሰናብተው በነበረበት ጊዜ በኮንትራት ተቀጥረው ውሉም በየ3 ወሩ የሚታደስ መሆኑን፣ በውላቸው መሰረት ያለማስጠንቀቂያ እንደተቋረጠ፣ የአሁን ይ/ባይ የጡረታ ተጠቃሚ እና ውሉም በሕጋዊ መንገድ የተቋረጠ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ እና የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፡፡የነጻ ትኬት ክፍያም በስራ ላይ ላለ ሰራተኛ እና ለጡረታ ተጠቃሚ የሚሰጥ እንጂ ለኮንትራት ሰራተኛ ውሉ ሲቋረጥ የሚሰጥ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክር፣ማስረጃ እንዲሁም የሕብረት ስምምነቱን በማጣመር መርምሮ የስራ ውሉን በተመለከተ ለተወሰነ ጊዜ በኮንትራት መቅጠር እንደሚቻላ እና የነጻ ትኬቱን በተመለከተም የሚያስገድድ የውል ሆነ የሕግ መሰረት ስለሌለ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውስኗል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚያም ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንደገናም ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለሕገ

መንግስት ትርጉም ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በዚህም ተቀባይነት በማጣት ለፌደሬሽን ም/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር የስራ ውሉን በተመለከተ ለተወሰነ ጊዜ በኮንትራት መቅጠር እንደሚቻል እና የነጻ ትኬቱን በተመለከተም ደግሞ የሚያስገድድ የውል ሆነ የሕግ መሰረት የሌለ መሆኑን ተረድተናል፡፡ይግባኝ ባይ የሌለ መብት ለመጠቀም ያቀረቡት ይግባኝ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም ሆነ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን ይግባኝ ተቀባይነት የለውም በማለት ጥለውታል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ. 693/15

ይግባኝ ባይ፡-..... ወ/ሮ ገነት ገ/እየሱስ

ተጠሪ፡-..... አቶ ሰለሞን ከተማ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የካቲት 01 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም... የሰበር ችሎቱም ሆነ የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ፍሬ ጉዳይን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው በስርፍ /ቤቶች ግራ ቀኞችን ከ1967 ዓ.ምእስከ 2008 ዓ.ም ድረስ እንደ ባልና ሚስት እንደኖርን በማስረጃ ያረጋገጡትን ሀቅ ወደ ጎን በማድረግ በተለይም ደግሞ ጉባዔው እንደ ባልና ሚስት ያለግንኙነት ቀጥሏል ለማለት በአካል አብሮ መኖር ግድ ይላል በሚል በሕግ ያልተቀመጠን መስፈርት በመጠቀም ግራቀኙ በ1986 ዓ.ም በአካል ሲለያዩ ግንኙነታቸው ተቋርጧል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 84 ስር ሕገመንግሥትን ለመተርጎም ብቻ ከተሰጠው ስልጣን ውጪ የመደበኛ ፍ/ቤትን ሥራ የሰራበት በአንፃሩም የሰበር ሰሚ ችሎቱም በኢፌዲሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 80 /3/ /ሀ/ ተለይቶ የተሰጠውን የሕግ ስህተት የማረም

ስልጣን በማለፍና የማስረጃ ምዘና ውስጥ በመግባት የሰጠው እጅግ ኢ-ፍትሐዊ ውሳኔ የእኩልነት ፣የንብረት እና ፍትሕ የማግኘት መብቴን የጣሰነው፡፡

በመሆኑም የተከበረው ምክር ቤት ግራ ቀኛችን እንደ ባልና ሚስት ያለንን ግንኙነትና የጋራ ንብረት በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲሁም የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሰጡት ውሳኔዎች የይግባኝ ባይን ሕገመንግሥታዊ መብቶች የጣሰ መሆኑንና ጥሰቱ ምየሕገመንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ መብቶቼ የሚከበሩበትን የሕገመንግሥት ትርጉም ውሳኔ እንዲሰጠኝ ስል አመለክታለሁ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ክርክሩየ ተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ይግባኝባይ (ከሳሽ) በተጠሪ (በተከሳሽ) ላይካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ይግባኝ ባይና ተጠሪ ከጥር 1967 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥርወር 2012 ዓ.ም ድረስ ለ45 ዓመታት እንደ ባልና ሚስት ስንኖር 4 ልጆችን አፍርተናል፡፡

በ1986 ዓ.ም ቤተሰባችንን ይዘን ወደ አሜሪካን ሀገር ከሄድን በኋላ ተጠሪ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል፡፡ ተጠሪ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ ግንኙነታችን ሳይቋረጥ በስራና በኑሮ ምክንያት ተለያይተን የምንኖር ቢሆንም ተጠሪ ለይግባኝ ባይና ለልጆቹ ገንዘብ በመላክና ድጋፍ በማድረግ በመሀልም በየጊዜው በመምጣት ሲጎበኘንና አብሮን በማሳለፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ንብረቶችን ለማፍራትና ስራዎች ለማከናወን ወደ አዲስ አበባና የተለያ ዩሀገራት እየተንቀሳቀሰ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ይግባኝ ባይ ጥር 2014 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ ተጠሪ እኔ ሳላውቅ ከሌሎች ሴቶች ጋር ግንኙነት እነንዳለውና ልጅ እንደወለደ የደረስኩበት ስለሆነከጥር 30 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ባልና ሚስት ያለን የነበረን ግንኙነት ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም ግንኙነት እስከተቋረጠበት ዕለት ለ45 ዓመታት እን ደባልና ሚስት አብረን ስንኖር በጋራ ያፈራናቸው ናቸው ያሏቸውን በክሱ ላይ የተዘረዘሩትን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመዘርዘር ተጠሪ እንዲያካፍሏቸው እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያቸው ለክሱ በሰጡት ምላሽ ከይግባኝ ባይ ጋር የነበረን እንደ ባልናሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የተቋረጠው ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ከ16 ዓመት በመፊት ስለሆነ ከዚህ ግንኙነት መቋረጥ በኋላ በተጠሪ የግል ጥረት የተፈራውን ንብረት ለመካፈል ይግባኝ ባይ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም ጥያቄውም በይርጋ ይቋረጣል የሚል ነው፡፡

ዋናውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ይግባኝ ባይና ተጠሪ ከ1986 ዓ.ም በኋላ ተለያይተን የምንኖር ሲሆን ህጉ የግድ የሚለው አብሮ የመኖር ግዴታ ባልተሟላበትና ሕግ ጥበቃ የሚያደርግለት ግንኙነት በሌለበት የቀረበ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ተቀባይነት የለውም:: የግራ ቀኙችን ግንኙነት ጋበቻ ሳይፈፀም እንደ ባልናሚስት አብሮ ለመኖር የሚያደርስ አይደለም፡፡

ከ1986 ዓ.ም በፊት እንደ ባልናሚስት አብረን ስንኖር ያፈራነውን ብረት የለም፡፡ ከጋብቻ ውጭ በግብረስጋግንኙነት መኖር በፌ/ብ/ሕግቁጥር 712 ድንጋጌ መሠረት በንብረት ረገድ ውጤት የሌለው በመሆኑ የይግባኝ ባይ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ነው፡፡ በግራ ቀኙችን መካከል እንደ ባልናሚስት የነበረው ግንኙነት በተለያየ ሀገር ተለያይተን ከመኖራችን በተጨማሪ ከ1986 ዓ.ም በኋላ ተጠሪ ከሌሎች ሁለት ሴቶች ጋር ሌላ ግንኙነት በመመስረቴ ግንኙነቱ ተቋረጧል፡፡ ይህ ግንኙነት ከተቋረጠና ተለያይተን መኖር ከጀመርን በኋላ በተጠሪ የግል ጥረት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ የተፈራ ንብረት ለመካፈል አመልካች መብት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በዋና ፍሬ ነገር ክርክር በግራ ቀኙ መካከል ያለው ግንኙነት ከ1986 ዓ.ም በኋላ ተቋርጧል ወይስ አልተቋረጠም የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ መዝገቡን መርምሯል::

እንደመረመረውም በግራ ቀኙ በቀረቡ ምስክሮች የተሰጠውን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኋላ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 98-107 በተመለከቱትና እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነትን የሚገዙ ድንጋጌዎች ያስቀመጠ ሲሆን በግንኙነት ውስጥ የሚኖሩ ወንድና ሴት ተለያይተው መኖር አይችሉም ተለያይተው መኖር ከጀምሩ ግንኙነቱ እንደተቋረጠ ይገመታል የሚል መስፈርት አላስቀመጠም፡፡

ይልቁንም ከዚህ ግንኙነት የበለጠ የመተማመንና እየተጋገዙ እየተረዳዱ የመኖር ግዴታ የሚጥለውን ጋብቻን የሚገዛው የሕጉ ክፍል በአንቀጽ 53 ስር ባለትዳሮች አብሮ የመኖር ግዴታ እንዳለባቸው ግዴታ ከጣለ በኋላ በአንቀጽ 55 ስረወ ባልና ሚስቱለ ተወሰነወ ይምላል ተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር ሊስማሙ እንደሚችሉ ደንግጓል ስለዚህ እነደባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ይህንን ማድረግ አይችሉም ሊባል አይቻልም።።

ሕጉ በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በስምምነት ተለያይተው ለመኖር ሊስማሙ እንደሚችሉ ከፈቀደ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እነደባልና ሚስት አብሮ የሚኖሩ ሰዎች ተለያይተው እንዳይኖሩ የሚከለክልበት ህጋዊ ምክን ት አለ ብሎ ስለማያምን ድንጋጌው ለበለጠ ምክንያት ወይም ለተመሳሳ ተመሳሳ ይድንጋጌ መተግበርም አመሳስሎ መተርጎም አግባብ መታየት አለበት የሚልና ሌሎችም የሕግ እና የፍሬ ጉዳይ ትንታኔዎችን በመስጠት ግራ ቀኙ በተለያየ ሀገር ለመኖር ከተስማሙበ ተለያየ ሀገር በመኖራቸው ብቻ ግንኙነቱ ተቋርጧል ሊባልአይችልም።።

ስለሆነም ግራ ቀኙ በግንኙነት ወቅት ያፈሩት ንብረት የተጠሪ የግል ንብረት ስለመሆናቸው በማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም በማለት እስከ 2008 ዓ.ም በነበረው ግንኙነት ውስጥ የተፈሩ ንብረቶች የጋራ ናቸው በማለት እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል።።

ተጠሪ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል።።

የሰበር ማመልከቻ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 28 ዓመታት ተለያይተው በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ መሆኑን፣ ይግባኝ ባይ ከ1967 ዓ.ም - 1986 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር አንደባልና ሚስት ሲኖሩ ያላደረጉትን ከሌሎች ሴቶች ጋር ጋብቻ በመመስረት እንደባልናሚስት አብሮ በመኖር ልጆችን መውለዳቸው አስቀድሞ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው እንደባልና ሚስት ግንኙነት ለመቋረጡግልጽ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው።።

ይግባኝ ባይ እንደባልና ሚስት ግንኙነት ቀጥሏል ወይንም በ1986 ዓ.ም አለተቋረጠም የሚለውን ክርክራቸውን የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ቢሆንም ቀርበው የተሰሙት

ምስክሮቻቸው ያስረዱት ተጠሪ ለይግባኝ ባይ ገንዘብ መላካቸውም ሆነ ከይግባኝ ባይ ጋር በተለያዩየ መገናኛ ዘዴዎች መጠያየቃቸው እንደ ባልናሚስት ግንኙነት መቀጠሉን አያመለክትም፡፡

በግራ ቀኙ መካከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በ1986 ዓ.ም ተቋርጦ እያለ ግንኙነት ቀጥሏል ተብሎ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ በተጠሪ የተፈራው ንብረት ከይግባኝ ባይ እኩል ይካፈሉ ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ስለሆነም በግራ ቀኙ መካከል የነበረው እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በ1986 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ ግራቀኙ እስከ 1986 ዓ.ም ድረስ በጋራ ያፈሩት ንብረት ካለ ይካፈሉ ነገር ግን ጠጠሪ ከይግባኝ ባይ ጋር የነበራቸው ግንኙነት በ1986 ዓ.ም የተቋረጠ በመሆኑ ግንኙነቱ ከተቋረጠ በኋላ ተጠሪ በግል ያፈሩትን ንብረት ለመካፈል ይግባኝ ባይ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ የሰበር ችሎቱን ውሳኔ በመቃወም ባቀረቡት ዝርዝር አቤቱታ ውሳኔው የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት መብት እንዲሁም የእኩልነት እና ንብረት የማፍራት ሕገ መንግሥታዊ መብቶቼን የጣሱ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት ጠይቀዋል፡፡

ጉባዔውም የይግባኝ ባይን አቤቱታ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤተችን ውሳኔ እና ይግባኝ ባይ ተጣሰበኝ ካሉት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር ከመረመረ በኋላ፣ የይግባኝ ባይና የተጠሪ እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ የተፈራው በተጠሪ በግል ጥረት ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር እንደተፈራ የሚቆጠር ነው፡፡

በዚህ መልኩ በተፈራ ንብረት ላይ ሕገ መንግሥታዊና ሕጋዊ ጥበቃ የሚደረገውም ንብረቱን ላፈራው ለተጠሪ ወይም ለባለንብረቱ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጪ ይግባኝ ባይ በጥረታቸው እና ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ በሌላ ሰው ጥረት በተፈራ ንብረት ላይ የሚያቀርቡት ሕገ መንግሥታዊ የንብረት መብት ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ ያቀረቡት የትርጉም ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላው ይግባኝ ባይ ተጣሰብኝ በማለት ያቀረቡት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚመለከት ሲሆን በዚህም ጉባዔው ጥያቄውን በዝርዝር ከተመለከተ በኋላ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ይግባኝ

ባይ እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ከ1986 ዓ.ም በኋላ መቀጠሉን አላሰረዱም ማለቱ በሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን የሚወድቅ በመሆኑ የይግባኝ ባይን ፍትህ የማግኘት የሚጥስ ሆኖ አለማግኘቱን፣ ስለሆነም ይግባኝ ባይ ከዚህ አንፃር ያነሱት የትርጉም ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሌላው ይግባኝ ባይ የእኩልነትን መብት በተመለከተ ያነሱትን የትርጉም ጥያቄ በተመለከተ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የይግባኝ ባይን ጉዳይ ከሌሎች ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ በሕገ መንግሥቱ ስር በተደነገጉት ምክንያቶች አድሎ በማድረግ ማየቱን የሚያመላክት ነገር የለም በማለትና ሌሎችም የፍሬ ጉዳዮችን በመዘርዘር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ባይን ሕገ መንግሥታዊ መብት የማይጥስ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ሲል በሙሉ ድምጽ ውሳኔ መስጠቱን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

እኛም ይግባኝ ባይ በሰበር ችሎቱና በአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጣቸው ለምክር ቤቱ ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ከሕገ መነግሥቱ እና ከፍ/ቤቱ ውሳኔ ጋር በማነፃፀር መርምረናል፤ እንደመረመርነውም ጉዳዩ ከጋብቻ ውጪ አብሮ ከመኖር ጋር ተያይዞ የተፈሩ ንብረቶች የጋራ ናቸው ክፍፍል ሊደረግ ይገባል አይገባም በሚል የተደረገ ክረክር ሲሆን በዚሁም በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን መርምረው የግራቀኙን አከራክረው ምስክር ሰምተው የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት ለአሁን ይግባኝ ባይ የወሰኑ መሆኑን፤ የሰበር ማመልከቻ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል በማለት ከመረመረ በኋላ ጉዳዮ በሰበር ተመልክቶ መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ሕገ መንግሥታዊ ስልጣኑን መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ባይን ሕገ መንግሥታዊ መብት ያልጣሰ መሆኑን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

ይግባኝ ባይ ፡-..... ወ/ት የሺመቤት ወ/ዮሀንስ

ተጠሪዎች ፡-..... እነ ወ/ሮ ትዕግስት ደሬሳ (3ሰዎች)

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሰኔ 16 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በፍ/ቤት ትዕዛዝ መሠረት የውርስ ሀብቱ በጨረታ እንዲሸጥ ሲባል የቀዳሚነት መብት እንዲሰጠኝ ያመለከትኩ ቢሆንም የቀዳሚነት መብቴን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የከለከለኝ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር የተመለከቱት ፍ/ቤቶች እና አጣሪጉባዔው የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማፅናታቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 እና 37 ላይ የተደነገጉት መብቶቼ የተገፈፉብኝ በመሆኑ ይግባኝ ባይ በዚህ ቤት መኖር እንድችል የቀዳሚነት መብቴ ተከብሮ ቤቱን ማስቀረት እንድችል የስር ፍ/ቤቶችና የአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ እንዲሻርልኝ እጠይቃለሁ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የውርስ ሀብትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪዎች በመሰረቱት ክስ ሲሆን የክሱ ይዘትም እናታችን ወ/ሮ ካሰች ወ/ዮሀንስ ከአያታችን ከወ/ሮ አፀደ አይችለሁም ቀድመው ስለሞቱ እናታችንን ተክተን የአያታችን የወ/ሮ አፀደ አይችለሁም ንብረት ሽጠን 1/4ኛ ድርሻችንን እንድንወስድ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ባይም ተጠሪዎች የእናታቸውን ድርሻ 1_4ኛ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 219 የሆነውን ተጠሪዎች እናታቸውን ተክተው 2ኛ ደረጃ ወራሽ በመሆን 1_4ኛየቤቱን የውርስ ድርሻ እንዲወስዱ፡፡ ይግባኝ ባይና ሁለቱ ተከሳሾች ደግሞ 1ኛ ደረጃ ወራሽ ሆነው እያንዳንዳቸው የቤቱን ድርሻ 1_4ኛ እንዲወስዱ፣የቤቱን ክፍፍል በተመለከተ ከተቻለ በአይነት ካልተቻለ አንዱ ለአንዱ ግምት በመስጠት፣ በዚህም ካልተቻለ በስምምነት በመሸጥ፣በዚህም ካልተቻለ በሀራጅ በመሸጥ እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች የፍርድ ባለመብት በመሆን ይግባኝ ባይና ወ/ሮ ገነት እና ወ/ሮ ታሪኳ ወ/ዮሀንስ የፍ/ባለዕዳ በማድረግ የአፈፃፀም ክስ በፌ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ከፍተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከተመለከተ በኋላ 1ኛ/ የፍርድ ባለዕዳ / ይግባኝ ባይ / ያቀረቡትን በቀዳሚነት ቤቱን የመግዛት መብት፣ 2ኛ እና 3ኛ የፍርድ ባለዕዳዎች እንደማይቃወሙ የቀዳሚነት መብት የገለፁ ቢሆንም የፍርድ ባለመብት /ተጠሪዎች/ እደሚቃወሙና የቀዳሚነት መብት ለእነሱ ሊሰጥ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ በግራ ቀኙ በሽያጩ የቀዳሚነት መብት እንዲሰጣቸው ፍላጎት ያሳዩ ስለሆነ የይግባኝ ባይ አቤቱታ ውድቅ ተደረጓል፡፡

2ኛ/ በግራ ቀኙ በሽያጭ ጨረታው ለመሳተፍ ፍላጎት ያሳዩ ስለሆነ በጨረታው ከሚሳተፉ በስተቀር ለግራ ቀኙ የቀዳሚነት መብት መስጠት የሚከለክል ሕግ የለም፡፡

3ኛ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ችሎት በ26/07/ 2013 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሀራጅ ሽያጩ ይቀጠል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ ቤቱን የመግዛት የቀዳሚት መብት ለተጠሪዎች ሳይሆን ለይግባኝ ባይ መሆን አለበት በማለት ቅሬታቸውን ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት፣ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተጠሪዎች ሳይጠሩ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ተፈጽሞበታል ሲሉ ለአጣሪ ጉባዔው አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉባዔው ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ይግባኝ ባይና ተጠሪዎች 1ኛ ደረጃ ወራሽ መሆናቸውን በዚሁም የውርስ ሀብቱን በተመለከተ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሁለቱም ወገኖች በጫረታ እንዲሳተፉ መብት የሰጠ ትዕዛዝ እንጂ ለተጠሪዎች ንብረቱን በቀዳሚነት የመግዛት መብት የሰጠ መሆኑን በግልፅ አያሳይም በመሆኑም የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 እና 37 እንዲሁም በሌሎች በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ስር የተዘረዘሩትን የአመልካችን መብት ይጥሳል ለማለት አይቻልም ስለዚህ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የህገ መንግሥትቬርጉም አየስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ይግባኝ ባይ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝና በጉባዔው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል እኛም ያቀረቡትን አቤቱታ ከፍ/ቤቱ ትዕዛዝ፣ ከጉባዔው ውሳኔ

እንዲሁም ተጥሰዋል ከተባሉ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር መርምረናል እንደመረመረነውም ጉዳዩ የሚያተኩረው የውርስ ሀብት ይገባናል ጥያቄን መሰረት አድርጎ የተሰጠን ውሳኔ ተከትሎ የቀረበ የአፈፃፀም ክስን የሚመለከት ሆኖ የቀዳሚነት መብት ላይ የተደረገ ክርክር ሲሆን በዚሁም መደበኛ ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን አከራክረው የሁለቱንም ወገኖች መብት ያስጠበቀ ጥዕላዝ የሰጡ መሆኑን፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ. 732/15

ይግባኝባይ፡-..... አቶ ዓለም በጎይሉ አሰፋ

ተጠሪ፡-..... ኢኳቶሪያል ዴልታ ኢንጂነሪንግ

<u>የይግባኝአቤቱታውባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሰኔ 29ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ይግባኝ ባይ የጠየኩትን ክፍያዎች ተጠሪ ከነወለዱ እንዲከፍል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በተጠሪ ይግባኝ ባይነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ጉዳዩ በሕጉ አግባብ የያዛቸውን ጭብጦች ወደጎን በመተው ባልተያዙ ጭብጦች ላይ ትችት በማድረግ የስር ፍ/ቤት ውሳኔውን ሽሮታል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ጉዳዩን ባግባቡ ሳይመረምር ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩትን ማስረጃዎች ሳይመለከት ውሳኔውን በማሻሻል የወሰነ ሲሆን ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማመልከቻ ያቀረብኩ ቢሆንም ችሎቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥኝ ሳያስቀርበኝ (ሳልጠራ)ያቀረብኩት አቤቱታ አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡

በፍ/ቤቱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጠኝ ለአጣሪ ጉባዔው አቤቱታ ባቀርብም በደፈናው የፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ቅሬታዬን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የፍ/ቤቱ እና የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 33(2)፣37(2) እንዲሁም አንቀጽ 40(1) እና (2) መሠረት የማገኘውን ጥቅምና መብት ያሳጣኝ ስለሆነ ውሳኔው የህገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ ይሄው ታርሞ ይግባኝ ባይ ባቀረብኩት ማስረጃ እና በውላችን መሰረት ያልተከፈለኝ ቀሪ ክፍያ ከነሕጋዊ ወለዱ እንዲከፈለኝ እጠይቃለሁ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን ይግባኝ ባይ ባይ በተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሲሆን የክሱ ጭብጥም ይግባኝ ባይ ከተጠሪ ጋር የተሻሻለ የሽርክና ስምምነት ማድረጋቸውንና ከኦሮሚያ የውሃ ስራዎች ግንባታ ድርጅት ጋር ባለው የአቅርቦት ውል የባለሙያነት አገልግሎት ለመስጠት፣ ተጠሪ ደግሞ ዕቃዎቹ ከቻይና የሚመጡ በመሆኑ ከዕቃ ላኪ ከሚያገኘው ኮሚሽን ክፍያ እና በአቅርቦት ውሉ መሠረት ከሚሠራው የአቅርቦትና ተከላ ስራ ከሚያገኘው ክፍያ ላይ 37% ሊሰጠንግዴታ ተገብቷል፡፡

ይግባኝ ባይ ዕቃዎቹን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት አስፈለላጊ የሆኑ አጠቃላይ ስራዎችን በመስራትና ቻይና ሃገር ከሚገኝ ድርጅት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ዕቃዎቹ ተገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት እንዲረከብ አድርጊያለሁ፡፡ ከቻይናው ድርጅት በድርድር ካስገኘሁት 88,888.30/ሰማኒያ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ስምንት ከ30/100 /የአሜሪካ ዶላር ላይ 50,000 / ሃምሳ ሺህ /ብር ሰጥቶኛል ፡፡ ነገር ግን የዕቃዎቹን ተከላ ስራ እንዳልሳተፍ፡፡

ስለዚህ በሽርክና ውል ስምምነታችን መሠረት ከውጪ ድርጅት ከተቀበለው ብር 348,104.91 /ሶስት አርባ ስምንት ሺህ አንድ መቶ አራት ከ91/100/ እና ከኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት ለተከላ ከሚከፈለው ብር 320,490.00/ሦስት መቶ ሃያ ሺህ አራት መቶ ዘጠና / ላይ 37% በአጠቃላይ 425,181.76 ብር እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ በመካከላችን ያለው የሙያ አገልግሎት ስምምነት እንጂ ከዚህ በፊት የተፈፀመና በ03/01/2005 ዓ.ም የተሻሻለ ህጋዊና የሽርካና ውል መመዘኛን የሚያሟላ ውል አልተደረገም ፡፡ ለሥራው መዋጮ አዋጥተን የጀመርነው የሽርክና ውል የለም፣ ስለውሉም ቢሆን ውሉን የተቀበለ አካል ስለመቀበሉ መግለጽ ስላለበት ተጠሪ ውሉን ስለመቀበሌ የተገለፀ ነገር የለም፡፡

የተሻሻለ አለ ለማለት አስቀድሞ የነበረ ውል ስለመኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል፤ቢኖር እንኳን በውል አፃፃፍ ስርዓት መፈፀም እንዳለበት በሕግ የተደነገገ ቢሆንም ይግባኝ ባይ አስቀድሞ ስለነበረው ውል አላስረዱም በተጨማሪም ይግባኝ ባይ የድረጅቱን ሚስጥር በማውጣት በጨረታ ውድድር ሆነ ብሎ እንዲሸነፍ በማድረጋቸው የሙያ ውሉን በማቋራጠቻው ከውጪ የመጡ ማሽኖች በሌላ ግለሰብ እንዲተከሉ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ከቻይናው ድርጅት ያገኘሁት ክፍያ በሌለበት ሁኔታ ለይግባኝ ባይ የሚከፈል ክፍያ የለም፡፡ክፍያ ቢኖር እንኳን 37% ክፍያው ለህግና ሞራል ተቃራኒ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተቀናሽ ሊያደርገው የሚገባ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በቃል ካከራከረ፣ የምስክሮችን ቃል ከሰማና የሰነድ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት በፅሁፍ ወይም በተለየ ፎርም መደረግ ያለበት ስለመሆኑ በሕግ አልተደነገገም እንዲያውም ተጠሪ ለይግባኝ ባይ የውል ፍላጎቱን የገለፀበትና ክሱም የተሻሻለ ውል መሆኑን የሚገልጽ ነው፤ ይግባኝ ባይም የውሉን ሃሳብ እንዲሁም ማሻሻያውን በዝምታ መቀበላቸውን የሚያሳይ ስለሆነ በመካከላቸው ውል መኖሩን ያሳያል የሚልና ሌሎች የህግና የፍሬ ነገሮችን በመዘርዘር ተጠሪ አስቀድመው የከፈሉት ልዩነት ታስቦ ከኮሚሽኑ የሚቀራቸውን እና ከኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት ከሚከፈለው 37% ክፍያ እንዲሁም ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የእነዚህን ክፍያዎች 9% ወለድ ለይግባኝ ባይ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ይግባኝ ካሳ ሊከፈላቸው የሚገባው ሥራ ኖሮ በሚለው ሳይሆን ውሉ በመቋረጡ ምክንያት በርትዕ መልኩ መሆን እንዳለበት ክሱ ያስረዳል በማለት ለደረሰው ጉዳት በኪሳራ መልክ በርትዕ ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) ብር እንዲከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡

የከፍ/ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ባይ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የስር የመጀመሪያ ደረጃ እና የከፍ/ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መታረም አለበት በማለት በፍሬ ጉዳይ ላይ ትንታኔ በማድረግ በይግባኝ ለደረሰው የጉዳት ካሳ በርትዕ የተወሰነው ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ) ከዚህ በፊት የተከፈለውን ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ)ብር በመቀነስ ለይግባኝ ባይ እንዲከፈል ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ ባይ በግንዘብ አሰላሉና ተቀናሽ ወጪዎች ላይ ለፌዴራል ሰበር ችሎት ቅሬታ ቢያቀርቡም ችሎቱ አያስቀርብም ብሎ ዘግቶታል፡፡

ይግባኝ ባይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎቶች የሰጡት ውሳኔ ለውጭ ሀገር መንግሥት ታክስ እንድከፍል የሚያደርግና የዜግነት መብቴን የሚጥስ እንዲሁም አንቀጽ 31፣ 33(2) እና 37(2)(ለ)አንቀጽ 79(3) በመተላለፍ ስለወሰነብኝ ጉባዔው ይህንን እንዲመረምርልኝ እና እነዲያርምልኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ጉባዔው አቤቱታውን ይግባኝ ባይ ከጠቀሷቸው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎችና ከፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ በይግባኝ ባይ ላይ ለደረሰው የጉዳት በርትዕ መወሰናቸውን ስንመለከት ፍ/ቤቶች በሕግ የተሰጣቸውን ሕግን የመተርጎም እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የወሰኑት መሆኑን በመጥቀስና ሌለችንም ድንጋጌዎች በመተንተን ፍ/ቤቶች ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ፈፅመዋል የሚያስብል አይደለም በማለት የፍ/ቤቶች ውሳኔ የህገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ የወሰነ መሆኑን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ይግባኝ ባይ በፍ/ቤቶች እና በጉባዔው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ ሲመረመር ክርክሩ የገዳት ካሳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን መደበኛ ፍ/ቤቶች በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የግራ ቀኙን አከራክረው ማስረጃ መዝነው የሰጡት ውሳኔ የትኛውንም የሕገ መንግሥት ድንጋጌ

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

ይግባኝ ባዮች ፡-..... እነ ወ/ሪት አዱኛ /ማሜ/ አየለ (2 ሰዎች)

ተጠሪ ፡-..... እነ ወ/ሮ ተለልቱ ወልዴ (2 ሰዎች)

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 6 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ላይ በግልጽ የተረጋገጠው የንብረት መብትን እጅጉን በሚደፈጥጥ መልኩ 1ኛ ይግባኝ ባይ በሕጋዊ የስጦታ ውል ያገኘሁትን እና ያለኝን ሀብት ሁሉ በማፍሰስ በርካታ ግንባታዎችን ያካሄድኩበትን እንዲሁም የህልውናዬ መሠረት የሆነው ጠቅላላ የግል ሀብቴን በግፍ እንድቀማ የሚያደርግ ውሳኔ መስጠቱም ሆነ ጉባዔው ይህንን ሳያርም ማለፉ ፍፁም የተሳሳተ እና የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መርሆዎች የሚቃረን እንዲሁም ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያላስገባ እና ግዙፍ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ምክር ቤቱ ጉዳዩን በአግባቡ በመመርመር እና በማጣራት ሕገ መንግሥታዊ መብቴ ተከብሮ ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት አመለክታለሁ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በደቡብ ክልል ሰገን ህዝቦች ከፍ/ፍ/ቤት የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ 2ኛ ይግባኝ ባይ ጣልቃ ገብ በመሆን ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በኮንሶ ወረዳ ካራት ከተማ ግምቱ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ብር የሚገመት የንግድ ድርጅት ቤት በሕጋዊ ስጦታ በ2ኛ ይግባኝ ባይ ተሰጥቶኝ በቦታው ላይ የነበረውን አሮጌ ቤት አፍርሼ እና ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቼ የገነባሁትን የንግድ ድረጅት 1ኛ ተጠሪ መብት ሳይኖራቸው ከሕግ ውጪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የሸያጭ ውል የፈፀሙ ስለሆነ ይህም በ1ኛ ይግባኝ ባይ መብትና ጥቅም ላይ የተደረገ ውል ሕገ ወጥ በመሆኑ በተጠሪዎች መካከል የተፈፀመው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ክሱ ደርሷቸው እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን መልስ አቅርበዋል በመልሳቸውም በ1ኛ ተጠሪና በ1ኛ ይግባኝ ባይ መካካል በሕግ ፊት ሊፀና የሚችል የስጦታ ውል የለም፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2423፣881፣883 እና 1721/1/ መሠረት 1ኛ ይግባኝ ባይ ያቀረባቸው ሰነዶች ረቂቅ እንጂ የስጦታ ውል አይደለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ባይ የጠየቁት ዳኝነት የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ከክሱ በነፃ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የመሸጥም ሆነ የመለወጥ ስልጣን ያላቸው መሆናቸውን አረጋግጬ የገዛሁት ስለሆነ ይግባኝ ባይ ሊጠይቁኝ አይገባም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

2ኛ ይግባኝ ባይ ጣልቃ ለመግባት ክሳቸውን አቅርበው ተፈቅዶላቸው ወደ ክርክሩ ገብተው ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት ክስ የሚች አባቴ የአቶ አየለ ሃ/ጊዮርጊስ ወራሽ ስለሆንኩ በጋራ ስናስተዳድር የቆየነውን ቤት በ2ኛ ይግባኝ ባይ አማካይነት እየተከራየ በየወሩ የሚገኘውንም የኪራይ ገቢ በጋራ ስንጠቀም ቆይተናል የውርስ ድርሻ ያለበት ስለሆነ ሽያጩ ይፍረስልን በማለት መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሰገን አካባቢ ህዝቦች ከፍ/ፍ/ቤት የቀረበውን ክስ የሰውና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የሚች አቶ አየለ ሃ/ጊዮርጊስ መሆኑን አረጋግጦ 1ኛ ተጠሪ የሚች ልጆች እናትና አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሞግዚትነት ማስረጃ በመያዝ ለ2ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በብር 500,000.00 (በአምስት መቶ ሺህ ብር) የሸጠች ስለሆነ ይህም ከሶስት ዓመት በፊት 2ኛ ተጠሪ በቅን ልቦና ገዝተው የተለያየ ግንባታ ፈጽማ ስመሀብቱን ወደራሷ አዛውራ የምትገኝ በመሆኑ ይግባኝ ባዮች የውርስ ድርሻቸውን ከሽያጭ የሚደርሳቸውን በሌላ ክስ ከመጠየቅ ውጪ ውሉ ሊፈርስ አይገባም የድርሻ ጥያቄ ከእናታቸው ከ1ኛ ተጠሪ መጠየቅ ይችላሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባዮች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ችሎቱ ይግባኙን መርምሮ 1ኛ ይግባኝ ባይን ጨምሮ ወራሾች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ወስደው 1ኛ ተጠሪም ሞግዚት በመሆን ቤቱን ሳይከፋፈሉ ሲጠቀሙበት እንደነበረ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ 1ኛ ተጠሪ ቤቱ በስማቸው የሚገኝ መሆኑን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በሽያጭ ማስተላለፋቸው ተቀባይነት ስለሌለው የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት 2ኛ ይግባኝ ባይ ከቤቱ ግማሽ የውርስ ድርሻቸውን ከ1ኛ ተጠሪ የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት ወስኗል፡፡

በመቀጠል ይግባኝ ባይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው ችሎቱም አስቀርቦ የግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔን በማፅናት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ማመልከቻ አቅርበው ችሎቱም ያስቀርባል በማለት መርምሮ የሰገን አካባቢ ህዝቦች ከፍ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመፅናት እና የ2ኛ ይግባኝ ባይን የውርስ ድርሻ አስመልክቶ የውርስ ድርሻቸው በስጦታ ውል ምክንያት መብታቸው እንደተቋረጠ የሚቆጠር ሲሆን የስጦታ ውሉን በሕግ አግባብ ባላስፈረሱበት ሁኔታ ከንብረቱ የውርስ ድርሻ አለኝ በሚል መነሻ የሺ.ያሜጭ ውል እንዲፈርስ የቀረበው ዳኝነት ተቀባይነት የለውም በማለት በማሻሻልና በማፅናት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ የፍ/ቤቱን ውሳኔ በመቃወም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀት 37 ላይ በግልጽ የተረጋገጠው ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ በመሆኑ ሊታረመረ ይገባል ሲሉ ለጉባዔው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ጉባዔው የይግባኝ ባዮችን አቤቱታ ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ የፍ/ቤቶች ውሳኔ የይግባኝ ባዮችን ፍትሕ የማግኘትም ሆነ የንብረት መብታቸውን የሚጥስ ውሳኔ አይደለም በማለት በውሳኔው ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም ሲል ውሳኔ ያስተላለፈ መሆኑን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ይግባኝ ባዮች በፍ/ቤቶች እና በጉባዔው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን እኛም ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ከፍ/ቤቶች ውሳኔ፤ከሕገ መንግሥቱናተጥሰዋል ካሉት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር በማጣመር መርምረናል እንደመረመርነውም ክርክሩ የሚያተኩረው የማይንቀሳቀስ ንበረት ላይ ሆኖ የስጦታ ውልንመሠረት በማድረግ የተከናወነ የሽያጭ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ክስ ሲሆን፤ከስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያሉ ፍ/ቤቶች በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክርና ያቀረቡትን ማስረጃ መርምረው የሰጡት ውሰኔ ይግባኝ ባይ ተጥሰዋል ያሏቸውን ፍትህ የማግኘትም ሆነ የንብረት መብት ጋር የማይጣረሱ መሆናቸውን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ. 742/15

ይግባኝ ባይ ፡-..... ወ/ሮ ኤልሳቤት ባልቻ

ተጠሪ ፡-..... ቀስተ ደመና ስፖንጅ ፋብሪካ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ተጠሪ ድርጅት የሕግ የበላይነትን ባለመቀበል ባልጠፋ ብር፤እርስ በርሱ የሚጣረስ ሀሰተኛ ኦዲት ሪፖርት፣ አግባብነት የሌለው የሽያጭ ማስረጃ እና ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ለፍ/ቤት በማቅረብ ከ3 ዓመት በላይ በየደረጃው ለሚገኙ ፍ/ቤቶች የተጣሰው ሕገ መንግሥታዊ መብቴ እንዲከበርልኝ ፍትህ ብጠይቅም በፍ/ቤቶች ፍትህ ማግኘት ባለመቻሌ ነሀሴ 25 ቀን 2013 ዓ.ም ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የስር ፍ/ቤቶች ውሰኔ ሕገ መንግሥታዊ የጣሱ ስለሆነ እንዲሻርልኝ አቤቱታ ባቀርብም ጉባዔው ባግባቡ ሳይመረምር የሕግ የበላይነትን ያላከበረውን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔን ብቻ በማየት የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን ያሳጣኝ በመሆኑ በፌ/ም/ቤት እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የሥራ ክርክር ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በሆነበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው ፡፡ የክሱ ይዘትም ይግባኝ ባይ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በፍተሻ ሰራተኝነት ተቀጥሬ በየግዜው የደረጃ ዕድገት እያገኘሁ ከታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም ጀምሮ አሸዋ ሜዳ በሚገኘው የድርጅቱ መሸጫ ቅርንጫፍ ቢሮ በቅርንጫፍ ሱፐርቫይዘር ll በወር ብር 5,672 (አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰባሁለት ብር) እየተከፈለኝ ስሰራ ቆይቻለሁ፤ሆኖም ተጠሪ ባላጠፋሁት ጥፋት ከሚያዚያ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለ15 የስራ ቀናት ታግደሻል በሚል ደብዳቤውን እንዳላነብ አድርጎ አዋክቦኝ

አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚቃረን የእግድ ደብዳቤ በእጄ በቀን 15/08/2012 ዓ.ም ሰጥቶኛል፡፡

ይግባኝ ባይም ይህን የዕግድ ጊዜዬን ጨርሼ ግንቦት 5 ቀን 2012 ዓ.ም ወደ መ/ቤቱ ሄጄ ስራዬን ልጀምር ስል የስራ ውልሽ ስለተቋረጠ ሚያዚያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ የስራ ውል ማቋረጫ ማስታወቂያ ለጥፈንልሻል በማለት ተጠሪ በይግባኝ ባይ ላይ ሕገ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ አድረጎብኛል፡፡

ስለሆነም ስንብቱ ሕገ ወጥ ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደስራዬ እንድመለስእንዲወሰንልኝ፤ የማልመለስበት ምክንያት ካለም የካሳ ክፍያ፤ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤ከመጋቢት እስከ ሚያዚያ 14 የሰራሁበት የአንድ ወር ደመወዝ፤የ86 ቀናት ያልተጠቀምኩበት የዓመት እረፍት ክፍያ፤የስንብት ክፍያ፤ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ላይ ሆኜ ያሰናበተኝ ስለሆነ የ180 ቀናት ደመወዝ እንዲከፈለኝ እና የስራ ልምድ እንዲሰጠኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ በሰጠው መልስ የይግባኝ ባይ የስራ ውል ሊቋረጥ የቻለው በ2 ቀን ሽያጭ የተሰበሰበ ገንዘብ ብር 46,100.00 (አርባ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ብር) ከሌላ የስራ ባልደረባቸው ጋር በመመሳጠር ያጎደሉ በመሆኑ ስንብቱ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1) (ሐ) መሠረት የተፈፀመ ነው በማለት ይግባኝ ባይ የጠየቋቸው ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተገቢነት የሌላቸው መሆኑን የዓመት ዕረፍት ፍቃድን በተመለከተ የ43 ቀናት የዓመት ዕረፍት እና የ10 ቀን ደመወዝ ለመክፈል ፍቃደኛ እንደሆነ በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(1) (መ) መሠረት የራስን ወይም የሌላን ሰው ብልፅግና በመሻት በአሰሪው ንብረት ወይም ገንዘብ አላግባብ መጠቀም ያለማስጠንቀቂ የሚያሰናብት ጥፋት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.42292 የአሰሪውን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት መሆኑን እና ከላይ ከተጠቀሰው አንቀጽ አኳያ የሚታይ በመሆኑ ይግባኝ ባይ የተጠሪን ገንዘብ ማጉደላቸው በኦዲትና በምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት የወሰነ መሆኑን፣ ሌሎች ጥያቄዎችን

ማለትም ኮቪድ 19ን የቀረበ ጥያቄን በተመለከተ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በተመለከተ ተጠሪ የይግባኝ ባይን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጋዊ መንገድስለሆነ ሊከፍል አይገባም ነገር ግን ተጠሪ ለይግባኝ ባይ የ10 ቀን ደሞዝ ብር 1,890.66 (አንድ ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ከ66/100) የ45 ቀናት ክፍያ ብር 8,508.00 (ስምንት ሺህ አምስት ስምንት ብር) በድምሩ ብር 10,398.66 (አስር ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከ66/100) ተገቢውን ግብር ተቀናሽ በማድረግ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝና የሰበር አቤቱቱታ በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶች ቢያቀርቡም በስር ፍ/ቤት የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት አለተፈፀመም በማለት አቤቱታውን ዘግተውታል፡፡

ይግባኝ ባይ በፍ/ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 ስር የተደነገገው የእኩልነት መብቴ ተጥሷል ሲሉ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን ጉባዔውም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ይግባኝ ባይ በፍ/ቤት ክርክር ሂደት ምስክሮቻቸውን እና ያላቸውን ማስረጃ በማቅረብ ክርክር ያከሄዱ ስለመሆኑ መዝገቡ የሚያስረዳ መሆኑን በመግንዘብ ከዚህ አንፃር ፍ/ቤቶች በክርክር ሂደት ላይ መሠረታዊ የማስረጃ ምዘናን መርህን በመከተልና በማረጋገጥ ውሳኔ መስጠታቸው ሲታይ የይግባኝ ባይ የእኩልነት መብት ተጥሷል ለማለት አይቻልም በማለት የፍ/ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ የመሰነ መሆኑን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ይግባኝ ባይ በፍ/ቤቶች እና በጉባዔው የተላለፈው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን የሚጥስ በመሆኑ ምክር ቤቱ እንዲሽርልኝ ሲሉ ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ከፍ/ቤቶችና ከሕገ መነግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ውሳኔ እንዲሁም ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል እንደመረመርነውም ጉዳዩ የሚያተኩረው የአሰሪና ሠራተኛ ክርክር ላይ ሲሆን በዚሁም ፍ/ቤቶች በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው የማከራከርና ማስረጃ የመመዘን ስልጣናቸው መሠረት የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገን በሕጉ መሠረት አከራክረው፣ ማስረጃ መዝነው የሰጡት ውሳኔ ይግባኝ ባይ የጠቀሱትን ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን የማይጥስ መሆኑን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ. 743/15

ይግባኝ ባይ፡-..... አቶ ጥላሁን ነጋሳ

ተጠሪ፡-..... የቅዱ ስማቲያስ አንጀሊካን ቤተክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 3 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በይግባኝ ባይና በተጠሪ መካከል ያለው የሥራ ግንኙነት መብት ክርክር ላይ ያቀረብኩት የሕገ መንግሥት መብት ጥሰቶችን አጣሪ ጉባዔ ውበጥ ንቃቄ አልተመለከተልኝም እንዲሁም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጠየቅሁትን የ19 ዓመታት የአገልግሎት ክፍያ ያልተወሰነልኝ በመሆኑ ምክር ቤቱ እንዲያርምልኝ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በሆኑበት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ይግባኝ ባይ በተሻሻለ ክሳቸው በተጠሪ ተቋም ውስጥ ከየካቲት 01 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በመጋቢነት (ፓስተርነት) የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው በአስተማሪነትና በአሰተባባሪነት በወር ብር 4,368.09 (አራት ሺህ ስስት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከ09/100) እየተከፈላቸው በመስራት ላይ የነበሩ መሆኑን ገልፀው ነገር ግን ተጠሪ ሕገ ወጥ ስልጠና ካልወሰድክ በሚል ምክንያት ነሐሴ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ከስራ አግዶኛል ስለሆነም ይህ ዕግድ ከሕግ ውጪ በመሆኑ ወደ ስራ ተመልሼ እንድሰራ እንዲወሰንልኝ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ግን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ተጠሪ ለይግባኝ ባይ እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ በሕግ ያልተመዘገበ በመሆኑ የሕግ ሰውነት የለውም ስለሆነም ክስ ሊቀርብበት አይገባም ይግባኝ ባይ የስራ መሪ ናቸው ስለዚህ ጉዳያቸው በዚህ ችሎት ሊታይ አይችልም፤ በግራቀኙ በኩል ያለው ግንኙነት የግል የሃይማኖት ወይም በጎአድራጎት አገልግሎት በመሆኑ ጉዳዩ በዚህ ፍ/ቤት ሊታይ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በተጠሪ የቀረቡ ሌሎች መቃወሚያዎችን ባለመቀበል አልፎ ይግባኝ ባይ በክሳቸው ላይ በግልጽ እንዳስቀመጡት በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩ የነበረው በፓስተርነት ወይም በመጋቢነት የስራ መደብ ላይ ሲሆን ስራቸውም ወንጌል ማስተማርና መንፈሳዊ የምክር አገልግሎት መስጠት መሆኑንም በክስ መስማት ወቅት ገልፀው መከራከራቸውን፡፡ ይግባኝ ባይ በተጠሪ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለመስራት የተስማሙት እና እየሰሩ ያሉት ስራ ከሃይማኖት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የሚመደብ ስለመሆኑ እሙን ነው፡፡

ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለውን የስራ ቅጥር ውልን መሠረት አድርጎ የሚያቀርበውን ክርክር ደግሞ ይህ የስራ ክርክር ችሎት ተቀብሎ አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የስረነገር የዳኝነት ስልጣን እንደሌለው በአዋጁ አንቀጽ 3 (3) (ለ) ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት የሚያስችል ስረ ነገር ስልጣን የለውም በሚል ብይን ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በተሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት የይግባኝ በአቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት፤ የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይግባኝ ባይ በፍ/ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጣቸው ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን ጉባዔው ያቀረቡትን ማመልከቻ ከፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ከሕገ መንግሥቱ ጋር በማጣመር ከመረመረ በኋላ ከሕገ መንግሥቱ መርሆዎች አንዱ የሆነውን በአንቀጽ 11 ስር የተደነገገውን የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት መርህን በመጥቀስ አንዱ በሌላው ጉዳይ ጣልቃ አይገባም በማለት ይግባኝ ባይ በፓስተርነት ወይም በመጋቢነት የስራ መደብ ላይ የሚሰሩ መሆኑንና ይህ የማስተማርና መንፈሳዊ ምክር አገልግሎት የመስጠት ስራ ከሃይማኖት ጋር በቀጥታ

ግንኙነት ያለው መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የሚመደብ መሆኑን ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አረጋግጧል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በመንፈሳዊ ሥራ ግንኙነት መሠረት በማድረግ የሚቀርብ አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስር የሚወድቅ ባለመሆኑ እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን ፍ/ቤቶች ተቀብለው የሚያስተናግዱ አለመሆኑን ያስገነዝባል ከዚህ አንፃር ሲታይ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥቱን ያከበረ ነው በማለት ውሳኔው ይግባኝ ባይ የጠቀሷቸውን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች የጣሰ ሆኖ ባለመገኘቱ ውሳኔው የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም ሲል ጉባዔው በሙሉ ድምፅ የወሰነ መሆኑን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

እኛም ይግባኝ ባይ በፍ/ቤቱ እና በጉባዔው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ከፍ/ቤቱ እና ከጉባዔው ውሳኔ እንዲሁም ተጥሰዋል ከተባሉ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡ አንደመረመርነውም፤ የጉዳዩ መነሻ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በዚሁም ይግባኝ ባይ በመጋቢነት (ፓስተርነት) የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው በአስተማሪነትና በአሰተባባሪነት በመስራት ላይ እንደነበሩና ተጠሪ ከሕግ ውጪ ከስራ ያገዳቸው በመሆኑ ዕግዱን በመቃወም ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የሕግና የፍሬ ነገር ክርክር በማንሳት ተከራክሯል ጉዳዩን የተመለከቱት በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶችም ይግባኝ ባይ በተጠሪ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለመስራት የተስማሙት እና እየሰሩ ያሉት ስራ ከሃይማኖት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለው መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የሚመደብ መሆኑን በማረጋገጥ ችሎቱ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያለውን የስራ ቅጥር ውልን መሠረት አድርጎ የሚቀርበውን ክርክር ተቀብሎ አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን እንደሌለው በአዋጅቁ.1156 አንቀጽ 3 (3) (ለ) መደንገጉን በመግለጽ ችሎቱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት የሚያስችል ስረነገር ስልጣን የለውም በሚል ብይን መስጠቱን ይህ ብይን አስከ ሰበር ችሎት ቀርቦ መፅናቱ ፍ/ቤቶች በሕገ መንግቱ የተሰጣቸውን ስልጣን መሠረት ያደረገ ውሳኔ መሆኑን፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ተጥሰዋል ከተባሉ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር መርምሮ ከሕገ መንግሥቱ መርሆዎች አንዱ የሆነውን በአንቀጽ 11 ስር የተደነገገውን የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት መርህን በመጥቀስ አንዱ በሌላው ጉዳይ ጣልቃ አይገባም በማለት የፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው ነው፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ. 749/15

ይግባኝ ባይ፡-..... አቶ ተረፈ መርግነህ

ተጠሪ፡-..... አቶ ጌትወይ ደርብ

<u>የይግባኝ አቤቱታ ውባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 15 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም እኔ ያልሰጠሁትን የኮንትራት ውል እንዲጨርስ መወሰኑ ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ አይደለም በማለትተቃውሞዬንአቅርቢያለሁ፡፡ እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 40(1) ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤትነት መብቱ እንደሚከበርለት ደንግጓል፡፡

በተለይ አርሶ አደሮች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) መሠረት መሬት በነፃ የማግኘትና ከይዞታቸው ያለመነቀል መብት እንዳላቸው እና ዝርዝር አፈፃፀሙ በሕግ እንደሚወሰን ተደንግጓል ይሁን እንጂ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በመ/ቁጥር 4044/11 ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ይህን የሚፃረር እና ይግባኝ ባይ በንብረቱ እንዳልጠቀም የሚያደርግ በመሆኑ ውሳኔው ትርጉም እንዲሰእንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በመርሀቤቴ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ይግባኝ ባይ በአሁን ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ሲሆን የክሱ ዝርዝርም በመርሀቤቴ ወረዳ ግሬትዋቾዋሪን ቀበሌ ስሙ ገባሜዳ በተባለ ቦታ የሚገኘው 0.0824 ሄክታር የገጠር ይዞታ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በድልድል ተሰጥቶኛል፡፡

ሆኖም በከባድ ችግር ምክንያት ሌላ ቦታ ሂጄ የመኪና አደጋ ስለደረሰብኝ በሕክምና ላይ እንዳለሁ ተጠሪ በጉልበት ይዞታውን ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ የቆርቆሮ ቤት ሰርቶ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም የሶስት ዓመት አላባ ግምትብር 3,000.00 (ሶስት ሺህ ብር) ከፍለው ይዞታውን እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ የሚልነው፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው መጋቢት 10 ቀን 2010 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ይግባኝ ባይ የአላባ ጥያቄ የጠየቁበት ዓመተ ምህረት በክሳቸው አልጠቀሱም ፣ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት የመጀመሪ ያደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡በፍሬ ጉዳዩ ዙሪያ ላይ ባቀረቡት መልስ አከራካሪው ይዞታ ያገኘሁት የይግባኝ ባይ ልጅ ከሆኑት ከአቶ ሻምበል ተረፈ በቀን 10/10/2003 ዓ.ምለ24 ዓመት በተደረገ የኪራይ ውል ነው፤ውሉም በሚመለከተው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መ/ቤት ቀርቦ በቀን 23/12/2003 ዓ.ም የፀደቀ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የቀረበውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ አጣረቷል፣ በዚሁም አከራካሪው ይዞታ የይግባኝ ባይ መሆኑን ፤ይግባኝ ባይ ከሚኖሩበት አካባቢ በመጥፋታቸው ልጃቸው አቶ ሻምበል ተረፈ የመጥፋት ውሳኔ በማስወሰን ይዞታውን መውረሱን እና በመቀጠል ይዞታውን ለአሁን ተጠሪ ለ24 ዓመት ማከራየቱን አረጋግጧል፡፡

ሆኖም ተጠሪ አከራካሪውን ይዞታ በኪራይ ውል መያዛቸው የተረጋገጠ ቢሆንም በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 171 መሠረት ጠፋ የተባለው ሰው ከተመለሰን ብረቶቹን የማስመለስ መብት ያለው በመሆኑ ተጠሪ ይዞታውን ለይግባኝ ባይ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ይዞታውን ለመከራየት ያወጡት ወጪ ከአቶ ሻምበል ተረፈ የመጠየቅ መብት አላቸው ብሏል፡፡

ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው መዝገቡ ያስቀርባል በማለት መርምሮ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 171(1) መሠረት ጠፋ የተባለው ሰው ቢመለስ ያለው መብት ንብረቶቹን ባለበት ሁኔታ የሚረከብ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ክርክር የቀረበበት ይዞታ በተመለከተ ይግባኝ ባይ ሲመለሱ ያገኙበት ሁኔታ ተከራይቶ በመሆኑ ይዞታውን ካከራየው ሰው የኪራዩን ዋጋ በመጠየቅ መቀበል እንጂ ውሉን በማፍረስ ይዞታውን የመረከብ መብት የላቸውም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ይዞታውን ለማከራየት መብት ካለው ሰው የተከራዩ መሆኑ በመረጋገጡ የኪራይ ውሉ ከመጠናቀቁ በፊት ይዞታውን ለይግባኝ ባይ መልቀቅ የለባቸውም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ በእኔ ላይ የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑ ሳይረጋገጥ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ይዞታውን የኪራይ ውሉ ከመጠናቀቁ በፊት ለይግባኝ ባይ የማስረከብ ግዴታ የለባቸውም ማለቱ አግባብነት የለውም በማለታቸው ፍ/ቤቱ ያስቀርባል ሲል መዝገቡን መርምሮ በይግባኝ ባይ ላይ የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ በማስቀረብ ተመልክቶ የይግባኝ ባይ ልጅ አቶ ሻመበል ተረፈ ወራሽ መባላቸውን አረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከወረዳው የአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በተላከው ማስረጃ አቶ ሻምበል ተረፈ ይዞታውን ለ24 ዓመት በኪራይ ውል ለተጠሪ ሲያስተላልፍ በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ ወረቀት ተሰጥቷቸው እንደነበር በማረጋገጥ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው አያስቀርብም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ይግባኝ ባይ የፍ /ቤቶች ውሳኔ በሕ ገመንግሥቱ አንቀጽ 37 እና 40 ላይ የተደነገጉ መብቶቼን የሚጥስ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ ሲሉ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አመልክተዋል፡፡ ጉባዔውም አቤቱታውን ከፍ/ቤቱ ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕገመንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር በጥልቀት ከመረመረ በኋላ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1) እና 40(4)ን በመተንተን እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር

ተያያዥነት ያለውን የአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅቁ. 133/1998 አንቀጽ 18(1) እና (6)ን በመፈተሽ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 40 የገጠር መሬት ማከራየት እንደማይቻል ክልከላ ያላደረገ መሆኑን በመጥቀስ አከራካሪው ይዞታ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የተከራየ በመሆኑ ይግባኝ ባይ የኪራይ ውሉ ሲጠናቀቅ ይዞታውን መረከብ ይችላሉ ተብሎ መወሰኑ የይግባኝ ባይን የንብረት መብት የማይጥስ መሆኑን፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ፍትህ የማግኘት መብቱ ተጥሷል በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ ይግባኝ ባይ አከራካሪውን ይዞታ በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሥልጣን ላላቸው ፍ/ቤቶች ክስ አቅርበው በየደረጃው አለኝ ያሉትን ማስረጃ አቅርበው ክርክር ያደረጉና በመጨረሻም ውሳኔ ያገኙ በመሆኑ በዚህ ረገድ የፍ/ቤቱ ውሳኔ የይግባኝ ባይን ፍትሕ የማግኘት መብት አይጥስም በማለት በአጠቃላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ውሳኔው የሕገመንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምፅ ውሳኔ መስጠቱን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

እኛም ይግባኝ ባይ በፍ/ቤት እና በአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ንብረት የማፍራት ሕገመንግሥታዊ መብቱ ተጥሷል ሲሉ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎችና ከፍ/ቤቱ ውሳኔ እነዲሁም ከጉባዔው ውሳኔ ጋር በማጣመር መርምረናል እንደመረመርነውም ጉዳዩ የሚያተኩረው የይዞታ ክርክር ላይ ሲሆን በዚሁም ፍ/ቤቶች መደበኛ ሕጎችን መሰረት በማድረግ በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት የግራ ቀኙን አከራክረው በክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ መሠረት የሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ባይን ንብረት የማፍራት መብት የማይጥስ ውሳኔ መሆኑን ተረድተናል

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ. 752/15

ይግባኝ ባይ፡-..... አቶ ሲሳይ ኦዲ

ተጠሪ፡-..... ትራንስ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 16 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ አቤቱታ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም ይግባኝ ባይ ያልተጠቀምኩበት የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈለኝ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎች እንደ የፕሮቪደንት ፈንድ ያሉ ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ በአፈፃፀም ብጠይቅም አጣሪ ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ ንብረት የማፍራት መብት፣ ፍትሕ የማግኘት የእኩልነት መብትና የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሕገ መንግሥታዊ መብቶቼን የሚጥስ ስለሆነ በውሳኔው ላይ ሕገመንግሥታዊ ትርጉም እንዲሰጥልኝ ምክር ቤቱን እጠይቃለሁ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በስር በፌ/መ/ደ/ፍ/ ቤት የአሁን ይግባኝ ባይ የፍርድ ባለመብት ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለ እዳ በመሆን ነው፡፡ ይግባኝ ባይ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ ብር 288,086.40 (ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ሰማኒያ ስድስት ብርከ 40%) በአፈፃፀም እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት የገንዘብ መጠን በዋና መዝገብ ላይ በክርክሩ ጊዜ ስለማቅረባቸው ሆነ በፍርድ ስለመወሰኑ በማስረጃ አላረጋገጡም እንዲሁም ይግባኝ ባይ አዲስ መብት ነው ያነሱት በማለት አቤቱታቸውን ውድቅ በማደድረግ ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት በየደረጃው ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የይግባኝና የሰበር አቤቱታ አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአጣሪ ጉባዔው ባቀረቡት አቤቱታ የስራ ውሉ በሕገወጥ መንግድ ስለተቋረጠ ወደ ስራ እንድመለስ ፍርድ ቤቱ ሊወስንልኝ ሲገባ ይህን ባለማድረጉ የበርሃ አበል ክፍያ መከልከሉ፣ ያልተከፈለኝ የዓባይ ግድብ የቦንድ ዋጋ ብር 28,000 (ሃያ ስምንት ሺህ ብር)፣ አልተሰጠኝም፣ የተወሰነልኝ ወጪ በጣም ያነሰ ሆኖ እያለ ያልተጠቀምኩበት የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈለኝ እና

ፕሮቪደንት ፈንድ መጠን ግልፅነት የሌለው ሆኖ እያለ የተሰጠው ውሳኔ ንብረት የማፍራት፣ ፍትሕ የማግኘት፣ የፅኩልነት፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕገ መንግስታዊ መብቶቼን የሚጥስ ስለሆነ በውሳኔው ላይ ሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጠኝ ሲሉ አመለክተዋል፡፡

ጉባዔው የይግባኝ ባይን አቤቱታ ከፍ/ቤቱ ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል በዚሁም ይግባኝ ባይ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት የአፈፃፀም ጥያቄ መሰረት ፍርድ ቤቱ ጥያቄው በዋና መዝገብ ላይ ይግባኝ ባይ ጠይቀው ያልተወሰነላቸው መሆኑን በመግለጽ እንዲሁም ፍርድ ባልተሰጣቸው ጉዳይ ላይ አፈፃፀም መጠየቅ አይችሉም በማለት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ መወሰኑን፡፡ ይግባኝ ባይ ያቀረቡት ጉዳይ አዲስ መብት ስለመሆኑ በተጨማሪነት ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ገልጾ ይግባኝ ባይን አሰናብቷል፡፡

ይግባኝ ባይ ለአፈፃፀም ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችሉት በዋና መዝገብ የተወሰነላቸውን እንዲፈፀምላቸው እንጂ ከዚህ ውጪ ለጥያቂያቸው መሰረት ያደረጉት ውሳኔ ውስጥ ባልተሸነፉ አዲስ ክርክር ማቅረብ አይችሉም በመሆኑም ይግባኝ ባይ በአፈፃፀም ችሎት ላይ በዋና መዝገብ ላይ እንዲፈፀምላቸው ያልተወሰነላቸውን ጉዳዮችንና አዲስ መብት ማቅረባቸው አግባብነት ስለሌለው በዚህ ረገድ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይ ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ባይን ፍትሕ የማግኘት፣ ንብረት የማፍራት፣ የእኩልነት መብት እና የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብታቸውን የሚጥስ አይደለም በማለት ውሳኔው የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ የወሰነ መሆኑን ከቀረበው መዝገብ መረዳት ተችሏል፡፡

ጉዳዩ የሚያተኩረው ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የሚከፈሉ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ የቀረቡ የአፈፃፀም ጥያቄዎችን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሥልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን መርምረው ይግባኝ ባይ በዋናው መዝገብ ላይ እንዲፈፀምላቸው ያልተወሰነላቸውን ውሳኔ በአዲስ መልክ እንዲወሰንላቸው ማቅረባቸው አግባብነት የለውም በማለት ሕጉን ተከትለው መወሰናቸው የይግባኝ ባይን የትኛውንም ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ አለመሆኑን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 735/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ከበደ ለሜቻ

ተጠሪ ፡---------- እነ ወ/ሮ ወርቂቱ ለሜቻ (3 ሰዎች)

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 13/11/2015 ዓም የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም

1ኛ ኮርቻ የሚባል ቦታ የሚገኝ ሁለት ቀረጥ መሬት፣ 2ኛ የባህር ዛፍ ንብረት 15 ሜትር በ9 ሜትር በሆነ ቦታ ላይ የተከልኩት 176 ግንድና መኖሪያ ቤት ያለበት ግማሽ ቀርጥ የእርሻ መሬት ያለበት በአጠቃላይ 2 ከግማሽ መሬት፣ እናቴ ወ/ሮ ዲባቤ ዴሲሳ እና አባቴ አቶ ለሜቻ ሆርዶፋ በጋራ በ1995 ዓ.ም በስጦታ ሰጥተውኝ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ቤት ሰርቼበት ለ24 ዓመት ስጠቀምበት የኖርኩት የግሌ ንብረት ሆኖ እያለ የውርስ ሀብት አካል ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴን የሚጥስ ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል።

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን 1ኛ እና 2ተኛ ተጠሪዎች ከሳሽ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ የአሁን ይግባኝ ባይ ጣልቃ ገብ በመሆን የጀመሩት ክርክር ሲሆን 1ኛ እና 2ተኛ ተጠሪዎች በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ለኤጀርሳ ለፎ ወረዳ ፍ/ቤት ፅፈው ባቀረቡት ክስ አቶ ለሜቻ ሆርዶፋ በቀን 21/02/2010 ዓ/ም የሞቱ ሲሆን በክሱ ከ1ኛ ተራ ቁጥር እስከ 17 ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት የአባታችን ሀብት ንብረቶች እናታችን በሆኑት 3ተኛ ተጠሪ እጅ ላይ ስለሚገኝ በአጠቃላይ ለ9 ወራሾች 3ተኛ ተጠሪ የአባታችን የውርስ ድርሻችን ታካፍለን በማለት ክስ አቅርበዋል።

3ተኛ ተጠሪ ደግሞ በቀን 15/05/2010 ዓም በሰጡት መልስ በ1ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ንብረት የግል ንብረቴ ነው 3ተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ከብት ያረድኩት እና አንድ ዳለቻ ላም ግምቱ ብር 3600 የምታወጣ ሽጨ ብሩን ለቀብር ሥነ ሥርዓት ከአቶ ነጌ ለሜቻ ተበድሬ የነበረውን እዳ የከፈልኩ ስለሆነ ይህ ስለሚመለከታቸው 2ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ንብረት የኔ ነው፡፡

3ተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰውን ሽጨ አባታቸውን ቀብሬበታለሁ 4ተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ሚች በሕይዎት እያለ በጋራ ሆነን ወ/ሮ ገላኔ ለሜቻ ለተባለችው ሰጥተናል፤ በ5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ባህር ዛፍ በ9ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው መሬት ግማሹን 1/2ኛ ቀረጥ መሬት ሚች እያለ በጋራ ሆነን ለአቶ አቦምሳ ለሜቻ ሰጥተነው እሱም ለ21 ዓመት ተጠቅምበታል በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል።

ይግባኝ ባይ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ በመሆን በቀን 24/05/2010 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ ፅፈው ባቀረቡት የጣልቃ ገብ አቤቱታ ተጠሪዎች እየተከራከሩባቸው ባሉት ንብረቶች ውስጥ በክሱ ተራ ቁጥር 13ኛ ላይ የተጠቀሰው 1 /አንድ/ ቀረጥ መሬት እና በ14ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው 2 /ሁለት/ ቀረጥ መሬት ውስጥ 1 ቀረጥ የእኔ ነው፡፡ 3ተኛ በ16ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው አንድ ቀረጥ መሬት ሚች አባቴ እና እናቴ 3ኛ ተጠሪ በጋራ ሆነው በ1996 የሰጡኝ እና እየተጠቀምኩበት ያለ ይዞታ ነው፡፡

4ተኛ በክሱ ተራ ቁጥር 8ኛ ላይ የተጠቀሰው የባህር ዛፍ ንብረት፣ በ9ኛ ተራ ቁጥር ውስጥ የተጠቀሰው በምስራቅ አቅጣጫ በአካባቢው መስፈሪያ ብትር 11 ከግማሽ ሜትር የሆነ ላይ ባህር ዛፍ ተክሎ በ1986 ጀምሮ ለ24 ዓመት ተጠቅሜበት እንዲሁም በሰሜን አቅጣጫ በአካባቢው መስፈሪያ ብትር 4 ሜትር ላይ የሚገኘውን ደግሞ በ1996 ዓም ጀምሮ ባህር ዛፍ ተተክሎ ለ14 ዓመት ሙሉ ተጠቅሜበት ፣ በአካባቢው መስፈሪያ ብትር 13 ሜትር ላይ የሚገኘውን በአሁን ሰዓት አንቡጥ /ለጋ/ ሆኖ በደቡብ አቅጣጫ የሚገኘውን ሚች አባቴ አቶ ለሜቻ ሆርዶፋ በ2009 ውስጥ ተጠቀምበት ብሎ ሰጥቶኛል፡፡

በአጠቃላይ 176 የሚሆን ባህር ዛፍ የሚኝበት መሬት የመኖሪያ ቤት፣ የሳር መሬት አውድማ እና የእርሻ መሬት ግማሽ ቀረጥ ጨምሮ 2 ከግማሽ መሬት ሰጥቶኝ

እየተጠቀምኩበት ያለውን ንብረት ተጠሪዎች እየተከራከሩበት ስለሆነ እነዚህ ንብረቶች ከክርክሩ ውስጥ እንዲወጡልኝ በማለት የጣልቃ ገብ አቤቱታ አቅርበዋል።

ተጠሪዎችም ለጣልቃ ገብ አቤቱታ ፅፈው ባቀረቡት መልስ ጣልቃ ገብ እና 3ተኛ ተጠሪ የእኛ ነው ብለው ያቀረቡት ይዞታም ሆነ ንብረት የግላቸው አይደለም ያቀረቡት ማስረጃ የሐሰት ማስረጃ ነው፡፡ በዚህ ይዞታ አላስለኩበትም ፤ ባህር ዛፉም ቢሆን ሚች አባታችን ነው የተክለው ፤ የተባለው ስጦታም የለም፤ አንድ ስጦታ ሊገኝ የሚችለው በምን ውስጥ አልፎ እንደሆነ በግጠር መሬት አዋጅ ላይ ስለተገለፀ ስጦታው የሐሰት ነው ብለዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ባይ ይዞታ በክሱ ውስጥ ተካቶ ቀርቧል ወይስ አልቀረበም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ የቀበሌ አስተዳደር እና የመሬት አስተዳደር በጋራ አጣርተው በደብዳቤ ቁጥር 766/2019 በቀን 04/11/2010 ዓም በተፃፈ ደብዳቤ የአመልካች የአቶ ከበደ ለሜቻ የሆነው ይዞታ በክርክሩ ተካቶበታል የተባለው 1ኛ በአንዶዴ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው አዋሳኙ በምስራቅ ጉተማ ለታ ፤ በምዕራብ አዋሽ ወንዝ፣ በሰሜን ለታ በቀለ፣ በደቡብ ቦይጉ ጉተማ የሚዋሰነውን 1 /አንድ/ ቀረጥ መሬት መሆኑ ስለታወቀ ይህ መሬት ከክርክሩ እንዲወጣለት ሌሎች ንብረቶች ግን የውርስ ሀብት ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት አስክ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ፀንቷል፡፡
ይግባኝ ባይ ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን መርምሮ የህገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶታል።

ከቀረበው አቤቱታ እና የመዝገብ ግልባጭ መረዳት የሚቻለው ይግባኝ ባይ በተጠሪዎች ክርክር ጣልቃ በመግባት ከክርክሩ እንዲወጡለት ከጠየቃቸው ንብረቶች ውስጥ ፍርድ ቤቱ በአጠቃላይ 2 ከግማሽ ቀርጥ መሬት 176 ግንድ ባሕር ዛፍ፤ የሳር መሬትና መኖሪያ ቤት ያለበት ቤት፣ ወሰኖች በክሱ ላይ የተጠቀሰው መሬት ፍ/ቤቱ የውርስ መሬት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ይህ ንብረት የይግባኝ ባይ የግል ንብረት ሳይሆን የውርስ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ የሰጠበት ዋናው ምክንያት ከቀበሌ አስተዳደር እና ከመሬት አስተዳደር በቀረበ ማስረጃ የይግባኝ ባይ ንብረት ሆነው በክስ ውስጥ የተካተቱት ከታአዶዴ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ያሉት አንድ አንድ ቀርጥ በጠቅላላው ሁለት ቀርጥ ከሆኑት መሬቶች በስተቀር ሌሎቹ ይግባኝ ባይ ከክርክሩ እንዲወጡ የጠየቃቸው ንብረቶች የይግባኝ ባይ የግል ንብረት አለመሆናቸውን በማረጋገጡ ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባይ የግል ንብረቶቹ ናቸው በማለት የጣልቃ ገብ አቤቱታ ያቀረበባቸው ንብረቶች የይግባኝ ባይ የግል ንብቶቹ አለመሆናቸውን በማስረጃ አረጋግጦ የሰጠው ውሳኔን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 734/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ከበደ ሙለታ

ተጠሪ፡---------- እነ አቶ ማስረሻ ሙለታ (5 ሰዎች)

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 07/11/2015 ዓም **የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም**

በ 160 ካሜ ባለው ይዞታ በገንዘቤ የሰራሁት ቤት የግል መሆን ሲገባው የውርስ ሃብት ነው መባሉ ለ 30 ዓመታት የኖርኩበትን ቤት እንድለቅ መወሰኑ በህገ መንግስቱ ንብረት የማፍራት ህገ መንግስታዊ መብቴን የሚጥስ በመሆኑ የህገ መንግስት ትርጉም ይስጥልኝ በማለት አመልክተዋል።

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽ ይግባኝ ባይ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን የተጀመረ ክርክር ነው፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ የተጠሪዎችና የይግባኝ ባይ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ሙለታ ቱፋና ወላጅ እናታቸው ወ/ሮ አለምነሽ ወ/ገብርኤል ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ተከትሎ የውርስ ሀብት እንዲጣራ ተደርጎ የውርስ ማጣራት ሪፖርቱም በመዝገብ ቁጥር 53817 ጥቅምት 8 ቀን 2009 ዓም በተሰጠው ውሣኔ ፀድቋል። በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር 803 በሚል የሚታወቀውን ቤት የውርስ ሃብት መሆኑ ተረጋግጦ ተወስኗል፡፡

ይህንን ቤት ይግባኝ ባይ በብቸኝነት እየተገለገሉበት ስለሆነ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ በቀረበውና በፍ/ቤት በፀደቀው የውርስ አጣሪ መሰረት ቤቱን ወራሾች እኩል እንድንካፈል ፣ተጠሪዎች የውርስ ሀብት የሆነውን ቤት ካርታ ለማሰራት ያወጣነውን ብር 43331.9 ከውርስ ሀብቱ ላይ ተቀናሽ እንዲሆንና ለተጠሪዎች እንዲከፈል እንዲሁም ተጠሪዎች የይግባኝ ባይ ድርሻ የሆነውን የውርስ አጣሪ የአገልግሎት ክፍያ የይግባኝ ባይ ድርሻ ብር 5000 የከፈልን በመሆኑ ይግባኝ ባይ ብር 2500 እንዲከፍሉ እንዲወሰንልን ፣ ይግባኝ ባይ የውርስ ሃብት የሆነውን ንብረት ለብቻቸው እየተገለገሉበት ያለ በመሆኑ ቤቱ ቢከራይ የሚያስገኘውን ገንዘብ ቤቱን አስኪያስረክቡ ድረስ ያለው ተሰልቶ እንዲከፍሉ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ይግባኝ ባይም በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ በክሱ ላይ የተጠቀሰው ቤት እኔ አየኖርኩበት አይደለም በቤቱ የሚኖሩት የሚች ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ዘውዴ ሃ/ማርያም የተባሉ ግለሰብ ናቸው፡፡

እኔ የምኖረው ሚች ይኖሩበት ከነበረው መኖሪያ ውጭ 162 ካ/ሜ ይዞታ ላይ በሰራሁት ቤት ነው፡፡ የቤት ቁጥር 803 የሆነው ቤትም ያረፈው በ 300 ካ/ሜ ላይ እንጂ 644 ካ/ሜ ላይ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ካርታ ለማውጣት ብር ወጭአድርገናል ያሉትንም እኔ አላውቀውም እኔ ቤት ሰርቼ በምኖርበት 162 ካ/ሜ ይዞታ ላይ ካርታ ለማውጣት በሂደት ላይ ነኝ። ተጠሪዎች የቤት ኪራይ እንድከፍል ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት ያለው አይደለም ስለሆነም የተጠሪዎች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ክርክሩ በሂደት እያለ 1ኛ ወ/ሮ አስለፈች ዳዲ 2ተኛ አቶ አሸናፊ ሙለታ የተባሉት ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ፈቅዶላቸው ጣልቃ በመግባት ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ጣልቃ ገብ ያቀረቡት መከራከሪያ ከይግባኝ ባይ ጋር ጋብቻ መስርተን ወልደን በመኖር ላይ እንገኛለን ፤ ክርክር የተነሳበት የቤት ቁጥር 803 የሆነው ቤት ያረፈው በ 300 ካ/ሜ ይዞታ ላይ ነው።

ከዚህ ውጭ 162 ካ/ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው ቤት የይግባኝ ባይ እና የ1ኛ ጣልቃ ገብ የግል ሃብታችን ስለሆነ በውርስ ሃብት ውስጥ ሊካተት አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ጣልቃ ገብ የሚቾች ወራሽ መሆናቸውን በመጥቀስ አንደ ተጠሪዎች የውርስ ሃብት ክፍፍል ጥያቄ አቅርበዋል።

ፍ/ቤቱም የሚቾ አቶ ሙለታ ቱፋ የውርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲቀርብ በመዝገብ ቁጥር 53817 ትዕዛዝ መስጠቱን ተከትሎ የሚች ወራሾችና የውርስ ሃብቱ ተጣርቶ ሰኔ 9 ቀን 2008 ዓም የተፃፈ የውርስ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

በዚህ የውርስ ሃብት ሪፖርት ላይም የሚች ወራሾች የአሁን ተጠሪዎች፣ ይግባኝ ባይ ፣ 2ተኛ ጣልቃ ገብ እና ወ/ሪት የኋላሸት ሙላቱ የተባሉት ዘጠኝ ግለሰቦችን ያካተተ እንደሆነና በውርስ ሃብቱ ላይም እያንዳንዳቸው 1/9ኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ፤ የውርስ ሃብቱንም በተመለከተ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር 803 በሚል በሚታወቀው ግቢ ውስጥ ይግባኝ ባይ የሰሩት ቤት ግምት ብር 58097.24 ሌሎች ወራሾች ለአሁኑ አመልካቾች እንዲከፍሏቸው ሆኖ ሙሉ ይዞታው የውርስ ሃብት መሆኑ ተረጋግጦ የውርስ ማጣሪያ ሪፖርት ቀርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም ይህን ሪፖርት በማፅደቅ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር 803 የሆነውንና በ 644.38 ካ/ሜ ይዞታ ያለውን የውርስ ሃብት ቤት ዘጠኙም ወራሾች እኩል ይካፈሉት ፤ ተጠሪዎች ይግባኝ ባይ የቤት ቁጥር 803 በሆነው ግቢ ውስጥ ለሰራው ቤት ግምት 50782.64 ለይግባኝ ባይ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ደረጃውን ጠብቀው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለህገ

መንግሰት አጣሪ ጉባኤ የህገ መንግሰት ትርጉም አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን መርምሮ የህገመንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶል፡፡

ከቀረበው የይግባኝ አቤቱታ እና የመዝገብ ግልባጭ መረዳት የሚቻለው ክርክር የተነሳበት በ 160 ካሜ ላይ ባለው ይዞታ የተሰራው ቤት የግል መሆን ሲገባው የውርስ ሀብት ነው መባሉ የይግባኝ ባይ ንብረት የማፍራት ህገ መንግስታዊ መብትን ይጥሳል አይጥስም የሚለውን በተመለከተ ቀደም ሲል በውርስ ማጣራት ሪፖርት ላይም የሚች ወራሾች /ይግባኝ ባይን ጨምሮ/ ዘጠኝ ግለሰቦችን ያካተተ እንደሆነና በውርስ ሃብቱ ላይም እያንዳንዳቸው 1/9ኛ ድርሻ ያላቸው ሆኖ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር 803 በሚል በሚታወቀው ግቢ ውስጥ ይግባኝ ባይ የሰሩት ቤት ግምት ብር 58097.24 ሌሎች ወራሾች ለይግባኝ ባይ አንዲከፍሏቸው ሆኖ ሙሉ ይዞታው የውርስ ሃብት መሆኑ ተረጋግጦ ቀርቦ በፍ/ቤትም የፀደቀ መሆኑና ይዞታውም በ 644.38 ካ/ሜ ላይ ያረፈ መሆኑ ለፍ/ቤት ከሚመለከተው አካል በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

የይግባኝ ባይ ዋና ቅረታ የቤት ቁጥር 803 ያረፈው በ 300 ካሜ ላይ ሆኖ ቀሪው ይዞታ ላይያለው ቤት እኔ በገንዘቤ የሰራሁት የግል ንብረቴ ነው የሚል ሲሆን ከፍ/ቤቱ ውሳኔ መረዳት እንደሚቻለው ይግባኝ ባይ በውርስ ይዞታ ላይ ለገነቡት ቤት ዋጋው ተገምቶ በቀረበው መስረት ተጠሪዎች እና ሌሎች ወራሾች ለይግባኝ ባይ ገንዘቡን እንዲከፍሉ የተወሰነ በመሆኑን ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 725/15

ይግባኝ ባይ፤---------- አቶ ግዛው ያሚ

ተጠሪ ፡---------- አቶ ጃንቦ ሼ/ቃሲም ጃንቦ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፤</u>

ይግባኝ ባይ በህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 10/10/2015 ዓም **የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም** ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ከአባቴ በውርስ ያገኘሁትን የውርስ መሬት ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ በስሙ አድርጎ ግብር እየክፈለበት የሚጠቀም ሲሆን ይህም በፍርድ ቤቶች እንዲስተካከልልኝ እና በመልቀቅ እንዲያስረክበኝ ብጠይቅም ከወረዳ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ያሉ ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ውሳኔ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ላይ የተቀመጠውን ህገ መንግስታዊ መብቴን የጣሰ በመሆኑ የህገ መንግስት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ ይግባኝ ባይ ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በኦ/ብ/ክ/መንግስት አርሲ ዞን የሮቢ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 77624 የተጀመረ የመሬት ይዞታ ክርክር ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ይግባኝ ባይ ሶስት ጥማድ የሆነውን የእርሻ መሬት በ 1977 ከአባቴ በውርስ ተላልፎልኝ እስከ 1996 ዓም በእጄ የነበረውን በ1999 ዓም በተደረገ የቃል ውል ለተጠሪ በቀርጥ በብር 300 ሶስት መቶ ብር በዕዳ ከሰጠሁ በኋላ እንዲለቅልኝ ብንስማማም የገጠር መሬት ይዞታ ልኬት በሚደረግበት ወቅት ይዞታውን በራሱ ስም አስደርጎ ሀሰተኛ የባለይዞታ ማረጋገጫ ስለወሰደበት ይዞታዬን እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ ሲሉ ጠይቀዋል።

ተጠሪ በሰጡት መልስ ይግባኝ ባይ ክስ የመሰረተበት ይዞታ በ1977 ዓም ከአባቴ በውርስ ተላልፎልኛል ይበሉ እንጂ በውርስ መተላለፉን ማስረጃ አለማቅረባቸው ፣ ከ1977 ዓም እስከ 1996 ዓም ይዞታው በእጄ ነበረ ቢሉም ከ1996 ዓም እስከ 1999 ዓም ማን እጅ እንደ ነበረ የገለጹት ነገር አለመኖሩ፣ የገጠር መሬት ይዞታ ልኬት በአካባቢው የተለካዉ በ1996 ዓም ሲሆን አመልካች ግን በ1999 ዓም በእምነት ሰጥቼው ከለከለኝ ቢሉም በ1999 ዓም የመሬት ልኬታ አለመኖሩና በአጠቃላይ የቀረበብኝ ክስ የህግ ድጋፍ ስለሌለው ውድቅ ይደረግልኝ ሲሉ መቃወሚያ ያነሱ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይህን አልፎ የሚያከራክር ከሆነ የመሬት ይዞታው በ1981 ዓም በሀጋዊ መንገድ ተስጥቶኝ የመንግስት ግብር እየገበርኩበት ለ29 ዓመት ስጠቀም ቆይቼ በስሜ በማስለካት የባለይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ የወሰድኩበት ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ሲሉ መልስ ሰጥተዋል።

ፍ/ቤቱም በተጠሪ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኝ ክርክርና የሰው ምስክር በመስማት ክርክር ያስነሳው መሬት ከይግባኝ ባይ ምስክሮች ይልቅ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ይዞታውን በ1981 ዓም በህጋዊ መንገድ በመሬት ልኬት ተሰጥቶት ሲጠቀምበት እንደነበረ የመሰክሩ ሲሆን ተጠሪ ከክስ መልሱ ጋር አያይዞ ያቀረበው ማስረጃ ክርክር ያስነሳው መሬት በተጠሪ ስም ተለክቶ የባለይዞታ ወረቀት አንዳለው ስለሚገልፅ ተጠሪ ይዞታውን የያዘበት ሁኔታ በቃል ውል እዳ ስላልሆነ የእርሻ መሬቱን ለይግባኝ ባይ ሊለቅ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቶል፡፡

ይግባኝ ባይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ደረጃውን ጠብቆ ባለ ፍ/ቤቶች የይግባኝ አቤቱታ ቢያቀርብም ፍ/ቤቶቹ ውሳኔውን አፅንተዋል፡፡

ይግባኝ ባይ ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን ከመረመረ በሁዋላ የህገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶታል።

ከቀረበው የይግባኝ አቤቱታ እና የመዝገብ ግልባጭ መረዳት የሚቻለው ይግባኝ ባይ በ1977 ዓም ከወላጅ አባቱ በውርስ ያገኘሁትን የገጠር የእርሻ መሬት ተጠሪ ስለያዘበኝ ይልቀቅልኝ ማለታቸውን ተጠሪ ደግሞ ክስ የተመሰረተበትን የገጠር የእርሻ መሬት በድልድል ያገኘሁት ስለሆነ ልለቅ አይገባም በማለት መልስ መስጠቱን ሲሆን ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍ/ቤቶች ደግሞ ክርክር የተነሳበት የገጠር የእርሻ መሬት የተጠሪ ይዞታ ስለሆነ ሊለቅ አይገባም በማለት ውሳኔ መስጠታቸውን ነው፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 አርሶ አደሮች መሬት የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 130/99 የእርሻ መሬት የማግኘት መብት እንዳለ ሲደነግግ የሚገኝባቸውም መንገድ በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን በድልድል፣ በስጦታና በውርስ መሆናቸውን አስቀምጧል።

ከላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ንብረቱን በአጁ የያዘ አካል በፍ/ሕግ ቁጥር 1195 የማይንቀሳቀስን ብረት ባለሀብትነትን ለማስረዳት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት መያዝን ይጠይቃል፡፡

ነገር ግን ይግባኝ ባይ ከአባቴ ከ1977 ዓም በውርስ ያገኘሁት ነው ቢሉም በእጃቸው ምንም ዓይነት የባለቤትነት ማረጋገጫ አላቀረቡም፡፡ በተጠሪ በኩል የመሬት ይዞታውን በድልድል ማግኘታቸውን እና በእጃቸው የባለቤትነት ማረጋገጫ እንዳላቸው ለፍርድ ቤቱ በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 745/15

ይግባኝ ባይ፡---------- እነ ወ/ሮ ገነት ሃይሌ

ተጠሪዎች፡---------- እነ ወ/ሮ ብርቁ ጅማ (8 ሰዎች)

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 08/12/2015 ዓ.ም የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም ይግባኝ ባይ በ1ኛ ተጠሪ ቤት እንደ ሌሎች ከአብራካቸው በተገኙ ልጆች ሁኔታ በጉዲፈቻ ማደጌ በምስክሮቼ አረጋግጬ እያለ በፍርድ ቤት የፀና የጉዲፈቻ ውል የለም በማለት እንዲሁም በቤተሰብ አባልነቴ ላገኝ የሚገባኝን ጥቅሜን እና መብቴን በማሳጣት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መስጠታቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የተደነገገውን መብቴን የሚጥስ በመሆኑ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው ይግባኝ ባይ ከሳሽ ፣ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ እና ከ2ኛ እስከ 8ኛ ያሉ ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች በመሆን በአርሲ ዞን አዲገሉ እና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 30074 የተጀመረ የውርስ ክርክር ነው፡፡

የክሱ ይዘትም አባቴ አቶ ሃይሌ ደበሌ በቀን 18/02/2010 ዓ.ም ሞተው የቀብር ስነ ሰርዓት በቀን 20/02/2010 ዓ.ም በዲገሉ ቦራ ቀበሌ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተፈፅሟል፡፡ አባቴ

በህይወት እያለ ይዞታ እና ንብረት የነበረው ሲሆን አኔም ልጁና 1ኛ ደረጃ ወራሽ ስሆን አባቴ የነበረው ይዞታ 5 ሄክታር እና አንድ ጥማድ መሬት፥ የተለያዩ ተክሎች ማለትም 1,000 እግር የባህር ዛፍ አንጨት በግምት 30,000 ብር የሚያወጣ ፣ባለ 25 ሉክ ቆርቆሮ 3 ክፍል መኖሪያ ቤት ግምቱ 300,000 ብር እና የተለያዩ ከብቶች በአጠቃላይ ግምቱ ብር 362,000 ለወራሾች እኩል አንድንካፈል በማለት አመልክተዋል፡፡

1ኛ.ተጠሪ በሰጡት መልስ ይግባኝ ባይ የማይገባትን ጥቅም ለማግኘት ከሰሰችኝ እንጂ ሟች አቶ ሃይሌ ደበሌ የይግባኝ ባይ አባት አይደለም፡፡ የይግባኝ ባይ አባት አቶ አበበ የሚባል አና እናቷም አኔ ሳልሆን ወ/ሮ መዓዛ የተባለች ስለሆነች ይህ ህገ ወጥ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ይደረግልኝ ብለዋል፡፡

ከ2ኛ. እስከ 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች ጣልቃ በመግባት ባቀረቡት አቤቱታ ይግባኝ ባይ በክሷ ውሰጥ የጠቀሰችው ንብረትና ይዞታ በውርስ ሊደርሰን የሚገባው ለእኛ ለጣልቃ ገቦች ሲሆን ይግባኝ ባይ እህታችን ያልሆነች አና የአባታችን ንብረት መውረስ የማትችል ነች፡፡ ይግባኝ ባይ አበበ ከተባለ ግለሰብ ተወለደች እንጂ ከአባታችን አልተወለደችም ፤ በውርሰ ሊደርሰን ከሚገባው ንብረት አና ይዞታ ላይ መብት ሳይኖራት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ በመሆኑም እኛ ከ1ኛ.ተጠሪ እናታችን ጋር ግማሽ እንድንካፈል እና የእኛን ድርሻ ከውስጡ አንዲወጣልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ይግባኝ ባይ ለቀረበው የጣልቃ ገብነት አቤቱታ በሰጡት መልስ ቤተሰቦቼ በ2 አመቴ ለ1ኛ.ተጠሪና ለባለቤታቸው አቶ ሃይሌ ደበሌ ከሰጡኝ በኋላ ክርስትና አንስተውኝ ልጃችን ናት በማለት እንደ ልጃቸው አሳድገው አስተምረው ድረውኛል ፤ከእነሱ በስተቀር ሌላ ሰው አላውቅም፤ አሳዳጊዎቼን ለመወረስም ቀዳሚ መብት ያለኝ ስለሆነ ጣልቃ ገቦች አስከ አሁን ድረስ እህታችን ናት ሲሉ ቆይተው አሁን ንብረትና ይዞታውን ስጠይቅ የካዱኝ ስለሆነ ጣልቃ ገቦች ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ይደረግልኝ ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራቀኝ ምስክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 207 ስር ልጅ ለማሳደግ የጉዲፈቻ ውል በመፈፀም የልጅነት ዝምድና አንደሚመሰረት ተደንግጓል፡፡ ይህም ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው ወይም የተደረገው ውል ጉዲፈቻ አለ ለማለት የሚያሰችለው ውሉ በጉዲፈቻ ሰጪ እና ተቀባይ መካከል በፍ/ቤት ቀርቦ የፀና ከሆነ እንደሆነ በአንቀጽ 211(1) ስር ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በይግባኝ ባይ አና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በፍ/ቤት የፀና የጉዲፈቻ ውል አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ይግባኝ ባይ አግብታ ከወጣች አስራ ስምንት አመት ያለፈው መሆኑን በማረጋገጥ ይግባኝ ባይ ከተጠሪዎች ጋር የቤተሰብ አባል ወይም በጥገኝነት አብራ ያልኖረች መሆኗን ከኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ጋር በማገናዘብ የይግባኝ ባይን ክስ ውድቅ አድርጎ ተጠሪዎች ንብረቱን እኩል እንዲካፈሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ከፍ/ፍ/ቤቱም የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ አይደለም በማለት መዝገቡን ሲዘጋው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት ዘግተውታል፡፡

ይግባኝ ባይ ፍ/ቤቶቹ በሰጡት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን መርምሮ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶታል።

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የንብረት ባለቤትነት መብትን በግልፅ አስቀምጣል ፤ በዚህ በተቀመጠው ድንጋጌ መሰረትም የንብረት ባለቤትነት የሚከበረው ንብረቱ ህግን መሰረት በማድረግ ለጥቅም ሲውል እንደሆነ ሕገ መንግስቱ በግልፅ ደንግጓል፡፡

የክልሉ የቤተሰብ እና የፍትሐብሔር ህግ ማንኛውም የጉዲፈቻ ውል ሰጪና ተቀባይ የሚያደርገውን የጉዲፈቻ ውል በፍርድ ቤት አስቀርቦ ማፀደቅ እንዳለበት ይደነግጋሉ ፣ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ ይግባኝ ባይ ምንም እንኳ ከተጠሪዎች ጋር ያደጉ መሆኑን ምስክሮቻቸው ቢገልፁም በፍ/ቤት የፀደቀ የጉዲፈቻ ውል እንደሌለ አረጋግጠው ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ነው፡፡

የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 2(16) የቤተሰብ አባል ማለት ከባለይዞታው የተወለዱ ልጆች ወይም ሌሎች መተዳደርያ የሌላቸውና በቋሚነት ከባለይዞታው ጋር የሚኖሩ ሰዎች እንደሆነ ይደነግጋል ፤ ይግባኝ ባይ ትዳር መስርተው ከይዞታው ከለቀቁ ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው በመሆኑ እንደ ቤተሰብ አባል ወይም አብሮ የሚኖር ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም በማለት ውሳኔ መሰጠተሩ ተገቢ ነው፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 738/1

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ወርቅነህ ማኔ

ተጠሪ፡---------- ወ/ሮ ምሲፍ ጤና

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 21/11/2015 ዓ.ም የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80 (3(ለ) እና የአማራ ክልል ፍ/ቤቶች ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 መሰረት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር አይቶ ለመወሰን እንጂ ህግና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም።

ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በእኔ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ በግራ ቀኞች ያልተካደ ፍሬ ነገር ሆኖ እያለ ለተጠሪ ድርሻ እንዲካፈል መወሰኑ በፍ/ህ/ቁ 1196 ድንጋጌ አንፃር ተቀባይነት የለውም። ክርክር የተነሳበትን ቤት የሰራሁት እኔ እንጂ ሚች አባቴ እና ተጠሪ አይደሉም።

ተጠሪ እና ሚች አባቴ ሰርተውታል ቢባል እንኳን ተጠሪ ገንዘቡን ከመጠየቅ በቀር የቤት ባለሀብት መሆን እንደማይችሉ ከፍ/ብ/ሕጉ 1195 መረዳት ይቻላል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከስልጣን ውጭና ከፍ/ብ/ሕጉ 1195 ድንጋጌ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የሰጠው ውሣኔ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 37 ፣ 40/1/ ፤1 ፤2፤7/፤እና 79 ድንጋጌዎችን የሚጥስ ስለሆነ የህገ መንግስት ትርጉም ይስጠን በማለት አመልክተዋል።

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብ/ክ/መ/ ደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ በመሆን በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ 404 የሆነው ቤት ተጠሪ የአባቴ ሚስትና የእኔ የእንጀራ እናት ስለሆኑ ከአባቴ ሞት በኋላ በቤተሰባዊነት እንዲቀመጡበት አድርጌአለሁ፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪ ቤቱን ለመልቀቅ ፍቃደኛ ስላልሆኑ በመ/ቁ 22747 ላይ ቤቱን እንዲለቁልኝ ክስ መስርቼ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁልኝ ውሳኔ ሰጥቶል፡፡

ስለሆነም በውሳኔው መሰረት ተጠሪ በቤቱ አላግባብ የኖሩበትን የሁለት ዓመት ኪራይ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በሰጡት መልስ በመዝገብ ቁጥር 22747 ላይ በተሰጠው ውሣኔ መሰረት ኪራይ መክፈል ግዴታ የለብኝም። ቤቱን ከሚች ባለቤቴ ጋር የሰራሁት የጋራ ንብረት እንጂ ይግባኝ ባይ የግል ቤት አይደለም በማለት ተከራክረዋል።

የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ የሰማው የወረዳው ከተማ ፍ/ቤት ተጠሪ በቤቱ እንዲኖሩ የተደረገው በቤተሰባዊነት ስለሆነ የሁለት ዓመት የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ አይገደዱም በማለት ውሳኔ ሰጥቶል፡፡ ክርክሩ በይግባኝ ቅሬታ የቀረበላቸው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበላቸውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይና በመ/ቁ 22747 ላይ ከቤቱ ድርሻ የላቸውም ተብሎ የተወሰነው ውሳኔ በመቃወም በሰበር ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር እና ሁለቱን መዝገቦች በማጣመር ከመረመረ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኖሪያ ቤት የይግባኝ ባይ የግል ንብረት ሳይሆን ተጠሪና ሚች ባለቤታቸው በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት የጋራ ንብረት መሆኑን በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡

አከራካሪው ቤት የባልና ሚስት ሆኖ እያለ በይግባኝ ባይ ስም ሊመዘገብ የቻለው በደርግ ዘመን ሁለት ቤት በአንድ ሰው ስም ሊመዘገብ ስለማይቻል በህፃን ልጃቸው ወይም በይግባኝ ባይ ስም ቤቱን ያስመዘገቡ መሆኑን የተጠሪ ማስረጃ ከይግባኝ ባይ ማስረጃ

በተሻለ ሁኔታ አረጋግጧል። ስለሆነም የአሁን ተጠሪ የቤቱን ድርሻ ሊለቁ አይገባም ቤቱን በጋራ ይካፈሉት ሲል ወሳኔ ሰጥቶል፡፡

በመጨረሻ ክርክሩን በሰበር ሰሚ ችሎት የተመለከተው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት የተጠሪ እና የሟች ባለቤታቸው የጋራ ንብረት መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የክ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወሰነ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከስልጣኑ ውጪ ማስረጃ ምዘና ውስጥ ገብቷል ለሚለውም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤት ከቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ አንፃር የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ከመወሰን የሚያግደው አይደለም በማለት ውሳኔውን በማፅናት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ ለህገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን ከመረመረ በሁዋላ የህገመንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶታል።

ከቀረበው የይግባኝ አቤቱታ እና የመዝገብ ግልባጭ በመነሳት ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሮል፡፡

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 37(1) መሰረት በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ማንኛውንም ነገር ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ፍርድ ወይም ውሳኔ ማግኘት የሚቻል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቶች በህግ ሊዳኝ የሚችል ጉዳይን የሚዳኙት በህግ ነው፡፡ ይህን የዳኝነት ስራም በህገ መንግስቱ በተሰጣቸው ስልጣን ክልል ውስጥ በመሆን ይሰራሉ፡፡

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ለ) መሰረት የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እና መሰረትዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በህገ መንግስቱ በግልፅ የተደነገገው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለባቸውን ማረም እንደሚችል ነገር ግን መሰረታዊ የህግ ስህተት ምንን እንደሚጨምር በህግ ሊወጣ እንደሚችል ከህገ መንግስቱ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት ምንን ይጨምራል የሚለው ነጥብ በህግ የሚደነግግ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ክርክርም የህግ ክርክር ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ይህን ህግ በሚተረጉሙበት ወቅት በህገ መንግስቱ የተደነገገውን የሰበር ሰሚ ችሎቱን መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ሰልጣን ስለመጣሳቸው የሚያመለክት ነገር የለም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ሰበር ሰሚ ችሎትም ከዚህ አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት ምን እንደሆነና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ለመወሰን የሚያግደው ነገር የሌለ መሆኑን በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ ከዚህ አንፃር ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከህገ መንግስቱ ድንጋጌ ጋር በሚቃረን መልኩ ከመሰረታዊ ህግ ከማረም ስልጣኑ ውጪ ስለመስራቱ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንፃር ይግባኝ ባይ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም።

በሌላ በኩል ይግባኝ ባይ ከህገ መንግስቱ የንብረት መብት አንፃር ያነሱትን ክርክር በተመለከተም አከራካሪው ቤት ተጠሪ እና የሚች ባለቤታቸው በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ የተባለ ነው። ይግባኝ ባይ ግራ ቀኙ ቤቱ በስማቸው የተመዘገበ መሆኑን እንዳልተካካዱ ቢከራከሩም ተጠሪ ቤቱ በይግባኝ ባይ ስም ቢመዘገብም ንብረቱ የተፈራው ግን በጋብቻ ውስጥ መሆኑን ተከራክረዋል። በቤተሰብ ህጉ ድንጋጌ መሰረት የባልና ሚስት ንብረት በሌላ ሰው ስም የተመዘገበ ቢሆንም ንብረቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ መሆኑ አስከተረጋገጠ ድረስ የባልና ሚስቱ ይሆናል በማለት ይደነግጋል፡፡

ይህ መብት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይም ጭምር የሚተገበር እንደመሆኑ መጠን በፍ/ህጉ አንቀፅ 1195 ከማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ጋር ተያይዞ ያለው ድንጋጌም ከዚሁ ጋር እና ከህገ መንግስቱ ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎም ያለበት ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶችም በዚህ ጉዳይ ላይ ከላይ በተገለፀው አግባብ ህጉን ከህገ መንግስቱ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተግባራዊ አድርገዋል ከሚባል በቀር በውሳኔአቸው የይግባኝ ባይን ህገ መንግስታዊ መብት ስለመጣሳቸው የሚያመለክት ነገር የለም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው

ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 744/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ ጌታቸው ማሩ

ተጠሪ፡---------- ወ/ሮ አልማዝ ሙለታ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ በህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 03/12/2015 ዓም የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም (1) በአጨበር ጨፌ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘው 240 ካ.ሜ ይዞታና ሶስት ክፍል ቤት በአባቴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሆኖ ሟቹ ወንድሜ አቶ ተፈረደኝ ማሩ በቀን 09/08/2002 ዓ.ም በኑዛዜ አስተላልፎልኝ እያለ ፍ/ቤቱ ንብረቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው፡፡

(2) ከዚህ በፊት በሰዲን ሶዶ ወረዳ በመ/ቁ. 04103 ከተጠሪ ጋር በነበረን የባልና ሚስት ክርክር በእርቅ ስምምነት ቀሪ ሲደረግ በጠኖቻ ወንቻቸር ቀበሌ ልዩ ስሙ አቶዬና ጎሽደን በሚባል አከባቢ የሚገኘው የገጠር የእርሻ መሬትና 60 ሺ ባህር ዛፍ የውርስ ንብረት እንደሆነ ስምምነት አድርገን እያለ ፍ/ቤቱ ይዞታውና ባህርዛፉ የባልና ሚስት ንብረት ነው በማለት መወሰኑ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠልኝን ንብረት የማፍራት መብቴን ስለሚጥስ በውሳኔው ላይ የህገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ ብለዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው ተጠሪ ከሳሽ፣ ይግባኝ ባይ ተከሳሽ፣ ወ/ሮ ብርቄ ገላን ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን በኦሮሚያ ክልል ሰዲን ሶዶ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር ነው፡፡ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ከይግባኝ ባይ ጋር በህገር ባህል መሠረት በ1972 ዓ.ም ተጋብተን አንድ ልጅ ወልደናል፡፡

ሆናም ግን በመካከላችን በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት አብረን ለመኖር ስለማንችል ጋብቻችን ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ይደረግልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ የጋራ ንብረት ናቸው በማለት የንብረት ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ከእነዚህ ንብረቶች መካከል

አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውና በጠኖቻ ወንቻቸር ቀበሌ ልዩ ስሙ አቶዬና ጎሽደን በሚባል አካባቢ የሚገኘው የገጠር የእርሻ መሬትና 60 ሺ ባህርዛፍ እንዲሁም በአጨበር ጨፌ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘው 240 ካ.ሜ ይዞታና ሶስት ክፍል ቤት ይገኝበታል፡፡

ይግባኝ ባይም አሻሽለው ባቀረቡት መልስ በጠኖቻ ወንቻቸር ቀበሌ ልዩ ስሙ አቶዬና ጎሽደን በሚባለው አከባቢ የሚገኘው ይዞታና 60 ሺ ባህርዛፍ ከዚህ በፊት በነበረው የባልና ሚስት ክርክር በመ/ቁ 04103 ባደረግነው የእርቅ ስምምነት ተጠሪ የውርስ ንብረት እንዲሆን ተስማምተዋል፡፡ ስለሆነም አሁን እንደ ጋራ ንብረት በመቁጠር ያቀረቡት ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ እንዲደረግላቸው ተከራክረዋል፡፡

በአጨበር ጨፌ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘው 240 ካ.ሜ ይዞታ የሚች አባቴ የነበረ ነው፡፡ አባቴ ይዞታው ለወንድሜ አቶ ተፈረደኝ ማሩ ሰጥቶት ሶስት ክፍል ቤት ሰርቶበታል። ወንድሜ ከዚህ አለም በሞት ሲለይ በቀን 09/08/2002 ዓ.ም አከራካሪው ንብረት በኑዛዜ አስተላልፎልኛል ስለሆነም የግል ንብረቴ ነው ሌሎቹ ንብረቶች ከፊሎቹ የጋራ ንብረቶች ናቸው፣ ቀሪዎቹ የእናቴ ናቸው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ወ/ሮ ብርቄ ገላን ጠልቃ ገብ በመሆን ወደ ክርክሩ ገብተው በአጨበር ጨፌ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘው 240 ካ.ሜ ይዞታ ልጄ አቶ ተፈረደኝ ማሩ ከአባቱ አቶ ማሩ ቢርቢርሳ በስጦታ አግኝቶ ሶስት ቤት ከሰራ በኋላ ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል፡፡ እኔም የንብረቱ ወራሽ መሆኔ በዚህ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13019 ካስወሰንኩ በኋላ በራሴ ስም ካርታ የተሰጠኝ በመሆኑ ንብረቱ ከባልና ሚስት ንብረት ክርክር ሊወጣ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በአጨበር ጨፌ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘው 240 ካ.ሜ እና በላዩ ላይ ያረፈው ሶስት ክፍል ቤት ከአጨበር መሬት ልማትና ማኔጀመንት ጽ/ቤት በተፃፈው ደብዳቤ መሠረት ንብረቱ የጣልቃ ገብ ልጅ የሆነው የአቶ ተፋረደኝ ማሩ እንደነበር እና ጣልቃ ገብ በውርስ አግኝተው ሳይት ፕላንና ካርታ አንደተሰጣቸው ስለገለፀና ባቀረቡት የሰውና የሰነድ ማስረጃ አከራካሪው ቤትና ይዞታ የራሳቸው መሆኑ በማስረዳታቸው ከክርክሩ እንዲወጣ ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በጠኖቻ ወንቻቸር ቀበሌ ልዩ ስሙ አቶዬና ጎሽደን በሚባል አከባቢ የሚገኘው የገጠር የእርሻ መሬትና 60 ሺ ባህርዛፍ ከዚህ በፊት በመ/ቁ 04103 ከተጠሪ ጋር የነበረን የባልና ሚስት ክርክር በእርቅ ስንጨርስ የግል ንብረቴ እንደሆነ ተጠሪ ተስማምተዋል

የሚል ክርክር ቢያቀርቡም ችሎቱ ባደረገው ማጣራት ተደረገ የተባለው የእርቅ ስምምነት የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ለማድረግ ሳይሆን ባልና ሚስት ጋብቻቸውን ለማፍረስ ያቀረቡትን ክስ ለማቋረጥ ነው፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.55973 ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም በመጀመሪያ በቀረበ የክስ መከላከያ መልስ ላይ ያልተካተተውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልሴን ላሻሽል በሚል ምክንያት ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት አካትቶ ማቅረብ እንደማይቻል ጠቅሶ ውሳኔ ስለሰጠ የእርቅ ስምምነቱ እንደ መቃወሚያ መቅረቡ ተቀባይነት የለውም ብሏል።

በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ 69/95 መሠረት አንድ ንብረት የግሌ ነው የሚል ወገን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ሆኖ ይግባኝ ባይ አከራካሪው ንብረት የግላቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በየደረጃው ስልጣን ለተሰጣቸው ፍ/ቤቶች አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንተዋል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለህገ መንግሰት አጣሪ ጉባኤ የህገ መንግሰት ትርጉም አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን መርምሮ የህገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶል፡፡

ከቀረበው የይግባኝ አቤቱታ እና የመዝገብ ግልባጭ መረዳት የሚቻለው ይግባኝ ባይ በአጨበር ጨፌ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘው 240 ካ.ሜ ይዞታና ሶስት ክፍል ቤት ሟቹ ወንድሜ አቶ ተፈረደኝ ማሩ በኑዛዜ አስተላልፎልኛል በማለት ክርክር አቅርበው ነበር፡፡ ሆናም ግን ፍ/ቤቱ በግራቀኙ የቀረበው ማስረጃ መርምሮ አከራካሪው ቤት የሟች ወላጅ እናት (ጣልቃገብ) የውርስ ንብረት ሆኖ በስማቸው እንደሚገኝ በማረጋገጥ ወስኗል፡፡

ከዚህ አንፃር ይግባኝ ባይ ባቀረቡት አቤቱታ አከራካሪው ቤትና ይዞታ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተብሏል ማለታቸው ከቀረበው መዝገብ አንፃር ትክክል አይደለም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ባይ ንብረቱ ለሟች ወላጅ እናት መወሰኑን በመቃወም የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ያላቀረቡ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ይግባኝ ባይ በጠኖቻ ወንቻቸር ቀበሌ ልዩ ስሙ አቶዬና ጎሽደን በሚባል አከባቢ የሚገኘው የገጠር የእርሻ መሬትና 60 ሺ ባህርዛፍ በተመለከተ ከተጠሪ ጋር በፍ/ቤት ባደረግነው የእርቅ ስምምነት የውርስ ንብረት እንደሆነ ተስማምተናል የሚል ክርክር አቅርበው ተደረገ የተባለው የእርቅ ስምምነት ተጀምሮ የነበረውን የፍች ክርክር ለማስቀረት እንጂ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል የሚመለከት አለመሆኑ ፍ/ቤቱ አረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የክስ መልስ ሲያቀርቡ ተደረገ የተባለው የእርቅ ስምምነት እንደ መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጠቅሰው ሳያቀርቡ መልሴን ላሻሽል በማለት እንደመቃወሚያ ጠቅሰው ማቅረባቸው ስነስርዓቱ እንደማይፈቅድ የስር ፍ/ቤት ጠቅሶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 69/95 አንቀጽ 79 መሠረት ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ የሚያገኙት ንብረት የጋራ ሀብት እንደሆነ የህግ ግምት እንደሚወሰድ ተደንግጓል፡፡ ይግባኝ ባይ አከራካሪው ይዞታና ባህርዛፍ የውርስ ንብረት ነው በማለት ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ንብረቱን የወረሱ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡

ከዚህ አንፃር ይግባኝ ባይ የህግ ግምቱን የማስተባበል ግዴታ ያለባቸው ሆኖ ይዞታውና ባህርዛፉ የውርስ ንብረት ስለመሆኑ የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ባለማቅረባቸው የባል እና ሚስት የጋራ ንብረት ነው መባሉ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር ይግባኝ ባይን የንብረት መብት ጥሷል ለማለት አይቻልም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁ 755/15

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ አለማየሁ ደጉ

ተጠሪ፡---------- መርጌታ አለበል ደጉ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ይግባኝ ባይ በህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምክር ቤቱ በቀን 22/12/2015 ዓም የተፃፈ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። የአቤቱታው ይዘትም ለበርካታ ዓመታት ይገረው የነበረውን አንድ የእርሻ መሬትና በውርስ ያገኘሁት ሶስት የእርሻ መሬቶች በእኔ ይዞታ ስር ሆኖ ሳለ እኔ ባልነበርኩበት ወቅት ተጠሪ ያለ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በማስወጣት ይዞታዬን ነጥቆኝ ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ባቀርብም ክስህ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እና 40 የተቀመጠውን መብቴን የጣሰ በመሆኑ የህገ መንግስት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

ጉዳዩ የተጀመረው ይግባኝ ባይ ከሳሽ ፣ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን በደቡብ ጎንደር ዞን እስቴ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01/13164 የተጀመረ የእርሻ መሬት ክርክር ነው። የክሱ ይዘትም ከእናትና ከአባቴ በውርስ ያገኘሁትን አራት መሬቶችን (አዋሳኝ ጠቅሰው) ተጠሪ አበል እከፍልሀለሁ በሚል ተረክቦ አለቅልኝ ስላለ መሬቶቹን በመልቀቅ ያስረክበኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ በ1ኛ.ተራ ቁጥር የተጠቀሰው መሬት በ1983 ዓ.ም ጀምሮ በምሪት የያዝኩት ሲሆን ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 ያሉትን መሬቶች ደግሞ ወላጆቼ ሰጥተውኝ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ከ 24 ዓመት በላይ የያዝኮቸው ስለሆነ በወራሾች መካከል የሚነሳ ክርክር ደግሞ በሶስት ዓመት ውስጥ መጠየቅ የሚገባው በመሆኑ ይግባኝ ባይ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ብለዋል፡፡

የግራቀኙን ክርክርና የሰው ምስክር የሰማው ፍርድ ቤትም ከ2 አስከ 4ኛ የተጠቀሱት መሬቶችን በተመለከተ ይግባኝ ባይ ተጠቅመውበት አንደማያቁ አምነው የተከራከሩ በመሆኑ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ በይርጋ ቀሪ ነው ፣ ሲል አንደኛው መሬት ላይ ምስክሮችን በመስማት ተጠሪ መሬቱን አስለቀቀ ከተባለበት ከ1895 ዓ.ም አስከ አሁን ሲሰላ 15 ዓመት ሲሆን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 13 መ/ቁ 69302 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ከ10 ዓመት በላይ መብት የሚያሳጣ በመሆኑ

ክስ የቀረበበት መሬትን በተመለከተ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ብይን ሰጥቷል፡

ይግባኝ ባይም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአ/ብ/ክ/መ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 የመሬት ውርስን በሚመለካት በፍትሐብሄር በተደነገገው መሰረት የሚል በመሆኑ ይህ ጉዳይ ደግሞ አስር ዓመት ያለፈው ስለሆነ የስር ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን በመጥቀስ የሰጠው ብይን የሚነቀፍ አይደለም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል። ይግባኝ ባይ ሰበር አቤቱታቸውን ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም ሲሉ ዘግተውታል።

ይግባኝ ባይ ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ የህገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ጉባኤው አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የህገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሳኔ ሰጥቶታል።

ከቀረበው የይግባኝ አቤቱታ እና የመዝገብ ግልባጭ መረዳት የሚቻለው ይግባኝ ባይ አራት መሬቶችን በአዋሳኝ በመጥቀስ ተጠሪ እንዲለቅላቸው ክስ አቅርበው ተጠሪም ይግባኝ ባይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረው ፍርድ ቤቶቹም ይግባኝ ባይ ክስ ያቀረቡ ከ10 ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱ ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት ውሳኔ መስጠታቸውን ነው፡፡

ህገ መንግስቱ በአንቀጽ 37 ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይግባኝ ባይ በፍርድ ቤት ቀርበው ተጠሪ የእርሻ መሬቱን ይልቀቅልኝ በማለት ክርክራቸውን አካሂደው በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶችም ይግባኛቸውን አቅርበው መልስ የመስጠትና የመሰማት መብታቸውን ስለተጠቀሙ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብታቸው ተጥሶል ማለት አይቻልም፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ማንኛውም የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸውም ያለመፈናቀል መብት ያላቸው ቢሆንም ንብረት በጉልበት ፣ በመፍጠር ችሎታ ወይም በካፒታል ሊፈራ የሚችልበትን ህጋዊ አግባብነት ባለው መልኩ ነው፡፡

ፍርድ ቤቶቹ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ መሬቱ በተጠሪ እጅ መሆኑን በማጣራትና ይግባኝ ባይም በዚህ ወቅት ሌላ ሀገር የነበሩ እንደሆነ በምስክሮች አረጋግጠው እንዲሁም የክልሉን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ድንጋጌን ከፍትሐብሄር ህጉ ጋር በማገናኘትና የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ከግንዛቤ በማስገባት ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ውሳኔ ስለሰጡ የይግባኝ ባይን ከመሬት ያለ መፈናቀል መብት የሚጥስ አይደለም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁጥር፡- 726/2015

ይግባኝ ባይ፤---------- አቶ አማኖ ሐጂ

ተጠሪ ፡---------- ፋል ጠቅላላ የሥራ ተቋራጭ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፤</u>

ጉዳዩ ለም/ቤቱ ሊቀርብ የቻለው ይግባኝ ባይ ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት ይግባኝ ነው፡፡ ጉዳዩም ከአሰሪና ሰራተኛ ጋር በተያያዘ ከስራ የመሰናበት አግባብነት ላይ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ ከሳሽ በመሆን መልስ ሰጪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻ ነው፡፡

የክሱ መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ይግባኝ ባይ ተጠሪ ድርጅት ውስጥ በአሽከርካሪነት የሥራ መደብ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የወር ደመወዝ ብር 4,470(አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ) እየተከፈለኝ በሂዳ ሂሎ የመንገድ ፕሮጀክት ሥራ ላይ ሳገልግል ቆይቼ ከጥር ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ ባለብኝ የጤና ችግር ምክንያት እና እድሜዬ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ወደ ዋናው ቦሌ ቡልቡላ ሎት 2 ፕሮጀክት ተዘዋውሬ እንዳገለግል ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ከታህሳስ 22 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የወር ደመወዝ ብር 9,200 (ዘጠኝ ሺህ

ሁለት መቶ) ተደርጎ እየተከፈለኝ ወደ ጎዴ ሀርገሌ መንገድ ፕሮጀክት ተዘዋውሬ እንድሰራ የዝውውር ደብዳቤ ተሰጠኝ፡፡

እኔ ግን ያለብኝ የጤና ችግርና የእድሜ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ገብቶ ባለሁበት እንድሰራ ጥያቄ ያቀረብኩ ቢሆንም መልስ ሰጪ ጥያቄዬን ያልተቀበለና የጤና ችግርና የእድሜ ሁኔታ ከግምት ሳያስገባ ይግባኝ ባይን ለማሰናበት የወሰደው እርምጃ በመሆኑ በአዋጅ ቁ.1156/2011 አንቀፅ 42 መሠረት ድርጊቱ ሕገ ወጥ ስንብት ነው እንዲባልልኝ፣ የአገልግሎት ክፍያ፣ የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የ6 ወር የካሳ ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ እና የታህሳስ ወር ደመወዝ በአጠቃላይ ድምር ብር 125,733 (አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር) እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን ያሳያል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ፡- ይግባኝ ባይ ተመድበው ይሰሩበት የነበረው የሃያት ጨፌ መንገድ ፕሮጀክት ሥራ በመገባደድ ላይ ያለና የሥራው አፈፃፀም ከ80% በላይ በመሆኑ ወደ ጎዴ ሃርገሌ መንገድ ሥራ ተዘዋውረው እንዲሰሩና ከየካቲት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተመደቡበት ፕሮጀክት ተገኝተው ሪፖርት እንዲያደርጉ ቢደረግም ይግባኝ ባይ ግን በተመደቡበት ፕሮጀክት ሊገኙ ያልቻሉ እንጂ በእኛ በኩል ያቋረጥነው የሥራ ውል የለም፡፡

በአዋጅ ቁ. 1156/2011 አሰሪ ድርጅት ሥራ ባለበት ቦታ ሠራተኞችን መድቦ ማስራትና ሥራ መስጠት እንደሚችል በተደነገገው መሠረት ይግባኝ ባይ ቀደም ሲል ከሚያገኙት የጥቅማጥቅም እና ደመወዝ ጭማሪ በማድረግ ዝውውር ሲያደርግ በአዋጁ የተደነገጉትን የሰራተኛ መብቶች በጠበቀ መልኩ ያደረገው ዝውውር በመሆኑ ይግባኝ ባይ በዝውውሩ ላይ ቅሬታ ካላቸው በተመደቡበት ፕሮጀክት በመሄድ በመደበኛ ሥራቸው ላይ ሆነው ቅሬታ ማቅረብ ሲገባቸው የስራ ውላቸው በአሰሪው እንደተቋረጠ በማስመሰል ያቀረቡት ክስ የህግ መሠረት የለውም፡፡

የይግባኝ ባይ የሥራ ውል መቋረጥ ያልተደረገ በመሆኑም ከሰንብት ጋር በተያያዘ የጠየቁትን ክፍያዎች ልንከፍል አይገባም፡፡ የታህሳስና የጥር ወር ደመወዝ እንዲሁም የሥራ ልምዳቸውን በተመለከተ ግን በመልስ ሰጪ ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት ቀርበው መውሰድ ይችላሉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ባይ በክስ አቤቱታቸው መልስ ሰጪ በሕገ ወጥ መንገድ ከስራ አሰናብቶኛል ያሉ በመሆኑ ይህንን የማስረዳት ሸክም የሚወድቅባቸው ቢሆንም የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ አቅርበው መልስ ሰጪ ያሰናበታቸው ስለመሆኑ ለማስረዳት አልቻሉም፡፡

በአንፃሩ በመልስ ሰጪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ይግባኝ ባይ ተዘዋውረው እንዲሰሩ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ እራሳቸው የቀሩ ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡ በዚሁም መሠረት ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪ ያላግባብ አዘዋውሮኛል የሚሉ ከሆነ በሥራ ገበታቸው ላይ ሆነው መብታቸውን መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን በመልስ ሰጪ በኩል በይግባኝ ባይ ላይ የተደረገ የስራ ማሰናበት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በውሳኔው ላይ በስር ፍ/ቤት የተፈፀመ ስህተት የለም ተብሎ ውሳኔው ፀንቶባቸዋል፡፡ ይህንን ተከትሎም ይግባኝ ባይ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አቤቱታቸውን ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡ ቢሆንም ጉባኤው ጉዳዩን ተቀብሎ በመ/ቁጥር 7481/15 ላይ ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም መርምሮ የፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የይግባኝ ባይ ሕገ-መንግስታዊ የመስራት መብት ጥሰት ያልተፈፀመ በመሆኑ የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ይ/ባይ የዕድሜዬ ሁኔታና በህኪም የተረጋገጠ የጤና ችግሮቼ ታይቶ ከሂዳ ያለ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ወደ ቦሌ ቡልቡላ ሎት 1 የመንገድ ሥራ መዛወሬ እየታወቀና ፕሮጀክቱ ሳያልቅ እንደሚያልቅ በማስመሰል ዝውውር በሚል ሽፋን ሕገ-ወጥ የሆነ ስንብት በቁጥር ፋል/አስልፌ/00/05/552/14 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተጠሪ ከሥራ አሰናብቶኝ እያለ ነገር ግን ከሥራ አላሰናበትኩትም ዝውውር ነው የፈፀምኩት የሚል መከራከሪያ በማቅረቡ የስር ፍ/ቤት ክርክሩን በማመን የሥራ ስንብት አልተፈፀመም በማለት ክሴን ውድቅ ማድረጉና ተጠሪ ክርክሩ የሥራ ሰንብት አልፈፀምኩም የሚል

በሆነበት ሁኔታ ከላይ የተገለፀው ደብዳቤ ስንብቴን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና ሰበር ሰሚ ችሎት መፅናቱ እንዲሁም አጣሪ ጉባኤም ውሳኔውን ማፅደቁ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ. 1156/2011 አንቀፅ 41(1) መሠረት ሕገ-ወጥ ስንብት ከመሆኑም ባለፈ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 41(1) እና 41(2) የተመለከተውን የሥራ መብቴን የጣሰ ውሳኔ በመሆኑ ምክር ቤቱ ከነዚህ የሕገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ በጉዳይ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት በክሴ መሠረት የጠየቅኩት ገንዘብ እንዲከፈለኝ ይወስንልኝ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኙ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተጣሱ ከተባሉት የሕገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ከሚለው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ይግባኝ ባይ ለዚህ ም/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ላይ አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት መልስ ሰጪ ዝውውር በሚል ሽፋን ከስራ አላሰናበትኩም በሚል የሚከራከር ቢሆንም የካቲት 04 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሥራ አሰናብቶኝ እያለ ፍ/ቤቶች የስራ ስንብት አልተፈፀመም በማለት ክሴን ውድቅ ማድረጋቸው በአግባቡ አይደለም በማለት መሆኑን ከይግባኝ አቤቱታቸው ይዘት ለመገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

ከዚህ አንፃር መልስ ሰጪ ይግባኝ ባይን ከሥራው አሰናብቷቸዋል ወይስ አላሰናበታቸውም የሚለውን ነጥብ በቅድሚያ ስንመለከት ከአጣሪ ጉባኤ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ውስጥ መልስ ሰጪ በቁጥር ፋል/አስልመ/05/552/14 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ይግባኝ ባይ በዝውውር ወደ ተመደቡበት ጎዴ-ሀርገሌ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ተገኝተው ሥራቸውን ለመስራት ባለመቻላቸው መነሻ ከየካቲት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከድርጅቱ ጋር የነበራቸው የስራ ውል የተቋረጠ ስለመሆኑ አርዕስቱ ጭምር የሥራ ስንብት በሚል ደብዳቤ ለይግባኝ ባይ መግለፁን ለማየት ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ደብዳቤ በፍ/ቤት ደረጃ በነበረው ክርክር በይግባኝ ባይ በኩል በማስረጃነት ተያይዞ ቀርቦ ያልተመረመረ መሆኑን ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ ይዘት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይግባኝ ባይ ከሥራ ተሰናበትኩበት በማለት በዚህ ም/ቤት አጥብቀው

የሚከራከሩበት የሰነድ ማስረጃ ለፍ/ቤት ባለመቅረቡም በተሰሙት የሰው ምስክሮች ቃል መነሻ ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪ ይግባኝ ባይን ከሥራው አላሰናበተም የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠቃሽ ደብዳቤ በአጣሪ ጉባኤ መዝገብ ውስጥ ተያይዞ ኮፒው ለዚህ ም/ቤት ከተላከው የይግባኝ ግልባጭ ጋር የተላከ ቢሆንም በምን አይነት ሁኔታ ቀርቦ ከአጣሪ ጉባኤው መዝገብ ጋር እንዲያያዝ እንደተደረገና አግባብነቱንም አስመልክቶ በአጣሪ ጉባኤው ምንም አይነት ትችትና ትንታኔ ያልተሰጠበት መሆኑ ሲታይ የደብዳቤውን ተአማኒነት የሚያሳጣ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይግባኝ ባይ ከጅምሩ ክስ ሲያቀርቡም በግልፅ መልስ ሰጪ ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ክስ ያቀረቡ ሳይሆን መልስ ሰጪ የጤና ችግሬንና የእድሜዬ ሁኔታን ከግምት ሳያስገባ የስራ ቦታ ዝውውር ማድረጉ ይግባኝ ባይን ለማሰናበት የወሰደው እርምጃ በመሆኑ ሕገ-ወጥ ስንብት ነው ይባልልኝ በማለት ዝውውሩ እንደ ስንብት እንዲቆጠርላቸው የሚከራከሩ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪ የተወሰደው የዝውውር እርምጃ ያለአግባብ ከስራ የማሰናበት ተግባር ነው በማለት የሚከራከሩ እንደመሆናቸው የመልስ ሰጪ ድርጊት ስንብት ስለመሆኑ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የማስረዳት ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ለማስረዳት ባለመቻላቸው ክሳቸው በፍ/ቤት ውድቅ ተደርጓል፡፡

በመሠረቱ አንድ በፍ/ቤት በተያዘ ክርክር የማስረዳት ሸክም በሕግ የሚወድቅበት ወገን አግባብነትና ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ክርክሩን የማስረዳት ኃላፊነቱን ካልተወጣ ፍ/ቤት መብቱን የሚያስከብርበት ምንም ዓይነት አግባብ የሌለ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ስለዚህም ይግባኝ ባይ በክሳቸው መልስ ሰጪ የወሰደብኝ እርምጃ ከስራ ማሰናበት ነው የሚሉና በአንፃሩ መልስ ሰጪ አላሰናበትኩትም በማለት ክሱን የሚክድ እንደመሆኑ ይ/ባይ ከሰራ ስለመሰናበታቸው የማስረዳት ሸክም የሚወድቅባቸው ቢሆንም ስለመሰናበታቸው አስረጂ ባለመቅረባቸው በመልስ ሰጪ በኩል የሥራ ውል የማቋረጥ ተግባር አልተፈፀመም ተብሎ በፍ/ቤት መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈፀመበት የሕግ ስህተት የሌለ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይግባኝ ባይ ከሥራ የተሰናበቱ መሆን ያለመሆናቸውን ጭብጥ ሳይመረምር በማለፍ ይግባኝ ባይ በዝውውር ወደ ተመደቡበት ሥራ ቦታ የእድሜና ጤና ሁኔታቸውን ምክንያት በማድረግ ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ዝውውርን ለመቃወም ሕጋዊ ምክንያት ባለመሆኑና ለመስራት ፍላጎት ሳይኖራቸው ሕገ-መንግስታዊ የመስራት መብታቸው ተጥሷል ለማለት አይቻልም በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ አንፃር አጣሪ ጉባኤው ይግባኝ ባይ ከሥራ መሰናበታቸው በቅድሚያ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስንብታቸውን ሕጋዊነት ጭምር በመመርመር ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ከጅምሩ ይግባኝ ባይ ከሥራ መሰናበታቸው በራሱ ባልተረጋገጠበት የስንብታቸው ሕጋዊነት የሚመረመርበት ምንም ዓይነት የሕግ አግባብ ያልነበረ ነው፡፡

ስለዚህም አጣሪ ጉባኤው ይግባኝ ባይ ከሥራ መሰናበታቸው ሳይረጋገጥ ወይም ሳይታወቅ አልፎ የስንብታቸውን ሕጋዊነት በመመርመር ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ሊባል የማይችል ቢሆንም በሌላ በኩል ከስራ መሰናበቱ ያልተረጋገጠ ሰራተኛ ደግሞ ሕገ-መንግስታዊ የመስራት መብቱ ተጥሷል ሊባል የማይችል በመሆኑ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የሰጠው ውሳኔ በውጤት ረገድ በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም ይ/ባይ በመልስ ሰጪ ድርጅት ውስጥ ቀድም ሲል ከሚሰሩበት የመንገድ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ፕሮጀክት በዝውውር ከተመደቡ በኋላ የእድሜና ጤና ችግራቸውን ምክንያት በማድረግ በሥራ ገበታቸው ላይ አለመገኘታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም በዚህም ይሁን በሌላ ምክንያት መልስ ሰጪ ከሥራ ያሰናበታቸው ስለመሆኑ ይግባኝ ባይ ያላስረዱ በመሆኑ ከሥራ ያልተሰናበተ ሰራተኛ ደግሞ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 41(1) እና 41(2) ላይ የተመለከተው የመስራት መብቱ ተጥሷል ለማለት ስለማይቻል ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም የቀረበለት የኢፌዲሪ የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤም ምንም እንኳን ጉዳዩን ከስንብቱ ሕጋዊነት አንፃር የመረመረ ቢሆንም በውጤት ረገድ ውሳኔው የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው

ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

መ/ቁጥር፡- 746/2015

ይግባኝ ባይ፤---------- አቶ ገብረጻድቅ ገ/መድህን

ተጠሪ ፡---------- የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ</u>

ጉዳዩ ለም/ቤቱ ሊቀርብ የቻለው ይግባኝ ባይ ነሐሴ 11 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት ይግባኝ ነው፡፡ ጉዳዩም ለጡረታ መብት የትውልድ ዘመን ማስተካከያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪ መ/ቤት ህዳር 23 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ ነው፡፡

ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጪ ያቀረቡት አቤቱታም መሠረታዊ ይዘቱ ሲታይ፡- ከኢፌዲሪ ወሳኝ ኩነት ባቀረቡት የልደት ሰርተፊኬት ላይ ያስመዘገቡት የልደት ዘመን 23/09/1951 ዓ.ም በመሆኑ ይኸው የልደት ዘመን ተይዞ የጡረታ አበላቸው ተሻሽሎ እንዲወሰንላቸው መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡

ጥያቄው የቀረበለት መልስ ሰጪም አቤቱታውን መርምሮ ይግባኝ ባይ ካቀረቡት ማስረጃ በፊት መጀመሪያ ለሥራ ሲቀጠሩ በ1972 ዓ.ም በተሞላ የህይወት ታሪክ ፎርም ላይ የትውልድ ዘመናቸው 23/09/1940 ዓ.ም መሆኑን በፊርማቸው ያረጋገጡበት ማስረጃ በኤጀንሲው የሚገኝ በመሆኑ በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁ.1/2008 አንቀፅ 28/3 መሠረት ለሥራ ሲቀጠሩ ያስመዘገቡት የልደት ዘመን ተይዞ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ባቀረቡት አቤቱታ ይግባኝ ባይ የትውልድ ዘመኔ ግንቦት 23 ቀን 1940 ዓ.ም ተብሎ የተፃፈው በእኔ የእጅ ጽሁፍ ያልተጻፈና በወቅቱ ተቀጥሬ እሰራበት የነበረው የግለሰብ ዳቦ ቤት

በመንግስት ተወርሶ ወደ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ስር ሲደረግ የዳቦ ቤቱ ሠራተኞችም አብሮ የተካተቱ ቢሆንም እኔ በዳቦ ቤቱ በኮንትራት ሰራተኛነት ያገለገልኩበት ወደ ኋላ ያለው ጊዜ በመንግስት ሠራተኛነት ሊያስቀጥረኝ የሚችል ባለመሆኑ ዕድሜዬ ተጨምሮ በሌላ ሰው የእጅ ዕሁፍና በተለየ የብዕር ቀለም ዕድሜዬ የተሞላ ነው፡፡

ዕድሜዬ በትክክል አለመመዝገቡን በተረዳሁ ጊዜ እንዲስተካከልልኝ ወዲያውኑ ለጎንደር ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጥያቄ አቅርቤ ተቀባይነት አግኝቶ ትክክለኛው የትውልድ ዘመኔ ሐምሌ 16 ቀን 1951 ዓ.ም በሚል የግል ማህደሬ ላይ እንዲሰፍር የተደረገ እና የተስተካከለ የጡረታ ፎርም ጥቅምት 03 ቀን 1973 ዓ.ም እንድሞላ ተደርጎ የጡረታ መለያ ቁጥር የተሰጠኝ በመሆኑና በልደት የምስክር ወረቀት ላይ የትውልድ ዘመኔ ሐምሌ 16 ቀን 1951 ዓ.ም ስለመሆኑ ማረጋገጫ የተሰጠኝ በመሆኑ የትውልድ ዘመኔ ሐምሌ 16 ቀን 1951 ዓ.ም በሚል ተስተካክሎ ይወሰንልኝ በሚል የጠየቁ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ጉባኤም ጉዳዩን መርምሮ በጡረታ አዋጅ ቁ.714/2003 እና በአፈፃፀም መመሪያቁ. 1/2008 አንቀፅ 22/1 መሠረት ቀድሞ የተመዘገበ የትውልድ ዘመን እንደሚያዝ የተደነገገ በመሆኑ በኤጀንሲው የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት ውሳኔውን አፅንቷል፡፡

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤታታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ ይግባኝ ባይ ቀጥለውም የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ አይቀርብም ተብሎ በትዕዛዝ ተዘግቶባቸዋል፡፡

ይህንን ተከትሎም ይግባኝ ባይ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አቤቱታቸውን ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡ ቢሆንም ጉባኤው ጉዳዩን ተቀብሎ በመ/ቁጥር 7302/15 ላይ መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም መርምሮ በተጠሪ የተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ጉዳዩን ፍ/ቤቶች በይግባኝ ተመልክተው የሰጡት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ አግባብነት ካለው የጡረታ አዋጅና ይህንኑ ለማስፈፀም ከወጣው መመሪያ ድንጋጌዎች አንፃር በመመርመር የተሰጠ እንጂ የይግባኝ ባይ ሕገ-መንግስታዊ መብት መጣስ ያልተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ይግባኝ ባይ የትውልድ ዘመኔ በ1940 ዓ.ም በሚል በ1972 ዓ.ም የተሞላው በወቅቱ እስራበት የነበረው የግል ዳቦ ቤት በማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ስር እንዲተዳደር ሲደረግ ማረሚያ ቤቱ ውሌን ወደ ቋሚ ለመቀየር ሲል ዕድሜዬ የመንግስት ሠራተኛ ለመሆን ስለማያስችል ዕድሜዬን በመጨመር የእኔ እጅ ዕሁፍ ባልሆነና በተለየ የብዕር ቀለም የተሞላ ነው፡፡

ይግባኝ ባይ ይህንን ስህተት በተረዳሁ ጊዜ ወዲያውኑ ለጎንደር ክ/ሀገር ወይኒ ቤቶች አስተዳደር አመልክቼ ተቀባይነት አግኝቶ የተስተካከለ የህይወት ታሪክ የያዘ የጡረታ ፎርም እንድሞላ ተደርጎ የጡረታ መለያ ቁጥር ተሰጥቶኝ የተስተካከለው የትውልድ ጊዜዬ በዋናው መዝገብ እና በማህደሬ እንዲያዝ ተደርጎ በዚህ ሲፈፀም የቆዬ ስለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎችን ያቀረብኩና በትዕዛዝ ቀርበው እንዲታዩም ጠይቄ ነበር፡፡

የኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በይግባኝ ባይ ማህደር ያሉ ማስረጃዎችን እና ሌሎች የሚቀርቡትን ተጨማሪ ማስረጃዎች ሳያገናዝብ የሰጡት ውሳኔ ለተመሳሳይ አገልግሎት እና የሥራ ቦታ ከሌሎች ሠራተኞች እጅግ ያነሰ የጡረታ አበል እንዲከፈለኝ በማድረግ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 25፣ 41 እና 90 ላይ የተደነገጉትን የእኩልነት፣ የማህበራዊ ዋስትና እና የመኖር ሕገ-መንግስታዊ መብቶቼን የጣሰ በመሆኑ ምክር ቤቱ ይህንን መርምሮ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ይወስንልኝ የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኙ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተጣሱ ከተባሉት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ከሚለው ጭብጥ አንፃር ተመርምሯል፡፡

ይግባኝ ባይ ለዚህ ም/ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ላይ ሕገ-መንግስታዊ መብቱ ተጥሷል በማለት አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት በመጀመሪያው የሕይወት ታሪክ ማህደሬ ላይ የተመለከተው ዕድሜዬ የተሞላው የራሴ እጅ ዕሁፍ ባልሆነ የሌላ ሰው እጅ ዕሁፍና የተለየ የብዕር ቀለም ከመሆኑም ባለፈ ዕድሜዬ ላይ የተፈጠረውን ስህተት ባወቅኩ ጊዜ ወዲያው

አመልክቹ መረጃው የተስተካከለ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርቤ እያለሁና በትዕዛዝም ቀርቦ እንዲታይልኝ እየጠየቅኩ እያለሁ ታልፎ ውሳኔ መሰጠቱ ሕገ-መንግስታዊ የማህበራዊ ዋስትና መብቴን የጣሰ ነው በሚል ነው።

ከዚህ የይግባኝ ባይ ቅሬታ በራሱ ለመረዳት የሚቻለው ይግባኝ ባይ መጀመሪያ የመንግስት ሠራተኛ ሆነው ሲቀጠሩ የሕይወት ታሪካቸው የተሞላና በዛ የሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ የትውልድ ዘመናቸውም መመልከቱን ነው።

ይግባኝ ባይ መጀመሪያ ሲቀጠሩ በተሞላው የሕይወት ታሪካቸው ፎርም ላይ የትውልድ ዘመናቸው መመልከቱን ሳይክዱ ነገር ግን በፎርሙ ላይ የተመለከተው የትውልድ ጊዜ የእኔ እጅ ፅሁፍ ባልሆነና በሌላ የብዕር ቀለም ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ይግባኝ ባይ ፎርሙንና በፎርሙ ላይ ያሉትን ሌሎች ይዘቶችን ሳይክዱ የትውልድ ዘመንን ብቻ ነጥለው የእኔ እጅ ፅሁፍ አይደለም፣ ትክክለኛ የትውልድ ዘመኔም አይደለም በማለት መከራከራቸው ክርክራቸውን ተአማኒነት የሚያሳጣው ከመሆኑም ባለፈ በሌላ ሰው የተሞላ ነው ቢባል እንኳን ሌሎች ዘቶቹ ሙሉ ለሙሉ ትክክል እስከሆኑ ድረስ በፎርሙ ላይ የተመለከተው የትውልድ ዘመንም የይግባኝ ባይ ትክክለኛ መረጃ ከራሳቸው ተወስዶ የተሞላ ዕድሜ ነው ከሚባል በስተቀር የይግባኝ ባይን ዕድሜ በማሳሳት በሀሰት የተሞላ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም።

በሌላ በኩል ይግባኝ ባይ መጀመሪያ በተሞላው የሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ የትውልድ ዘመን ስህተት መኖሩ ተረጋግጦ ሌላ የተስተካከለ ፎርም ተሞልቶልኛል በማለት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም የይግባኝ ባይ የጡረታ ፎርም ላይ የምዝገባ መረጃ ለውጥ የተደረገ ስለመሆኑ ጉዳዩን በፍሬ ነገር ረገድ በተመለከቱት በኤጀንሲው፣ በኤጀንሲው ይግባኝ ሰሚም ሆኑ በፍ/ቤቶች በኩል በዚህ ረገድ የተረጋገጠ ነገር አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያሳያል።

ይልቁንም ይግባኝ ባይ ጉዳዩን ለኤጀንሲው ሲያቀርቡ ያመለከቱት ከወሳኝ ኩነት ባቀረቡት የልደት ሰርተፊኬት ላይ ያስመዘገቡት የልደት ዘመናቸው ተይዞ የጡረታ አበላቸው ተሻሽሎ እንዲወሰንላቸው በሚል ስለመሆኑ የቀረቡት የውሳኔ ግልባጭ ሰነዶች የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህ አንፃር ይግባኝ ባይ በቅሬታቸው ላይ እንደጠቀሱት የትውልድ ዘመን የምዘገባ መረጃ ለውጥ በወቅቱ የተደረገ ቢሆን ኖሮ ወይም ስለመደረጉ ማስረጃ ቢኖራቸው ከወሳኝ ኩነት የልደት ሰርተፊኬት ማቅረብና በዛ አግባብ ለመስተናገድ ጥያቄ ማቅረብ የማይጠበቅባቸው በመሆኑ ይህ

በራሱ መጀመሪያ በተሞላው የይግባኝ ባይ የትውልድ ዘመን ምዘገባ ላይ ስህተት መኖሩ ታምኖ የምዝገባ መረጃ ለውጥ አለመደረጉን የሚያስገነዝብ ነው።

ከዚህ አኳያ አከራካሪው የጡረታ መብትና የትውልድ ዘመን መረጃ ለውጥ ክርክር ጉዳይ እልባት የሚያገኝበት የሕግ ማዕቀፍ በክርክሩ ወቅት በሥራ ላይ የነበረው ስለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁ. 714/2003 ሲሆን በዚህ አዋጅ መሠረት የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሠራተኛው መጀመሪያ ሲቀጠር የመዘገበውን የልደት ዘመን መሠረት በማድረግ 60 ዓመት ስለመሆኑ በአንቀፅ 18/1(ሐ) ስር በግልፅ ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌም የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜን ለመወሰን መሠረታዊ መረጃ ተደርጎ የሚወሰደው ሠራተኛው መጀመሪያ ሲቀጠር የመዘገበው የልደት ዘመን ስለመሆኑ በግልፅ የሚያስገነዘብ ነው።

ሕጉ በዚህ አግባብ ግልፅ ድንጋጌ ያስቀመጠውም በጊዜ ሂደት አሁን የተያዘው ጉዳይ ዓይነት ከሠራተኞች የጡረታ መውጫ ዕድሜ ጋር በተያያዘ የሠራተኛውን የልደት ዘመን በሚመለከት ሊነሱ የሚችሉትን ክርክሮች ለማስቀረት ሲባል መሆኑንና በዚሁ መነሻም በቅድሚያ የተመዘገበው የመንግስት ሠራተኛ ዕድሜ ወይም የልደት ዘመን የማይቀየር ስለመሆኑ ከተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ይህንን አዋጅ በመሻር ስለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ ከወጣው አዋጅ ቁ. 1267/2014 አንቀፅ 6/7 ይዘት ለመገንዘብ የሚቻል ነው።

ከዚህ አንፃር በተያዘው ጉዳይ ይግባኝ ባይ መጀመሪያ የመንግስት ሠራተኛ ሆነው ሲቀጠሩ የሞሉት የልደት ዘመን መኖሩ ተረጋግጦ በዚሁ አግባብ የጡረታ መውጫቸውና የጡረታ አበላቸው መወሰኑ የጡረታ መብትን ለመደንገግ የወጣውን ሕግ ተከትሎ በአግባቡ የተሰጠ ውሳኔ ነው ከሚባል በስተቀር በይግባኝ ባይ የተጠቀሱትን በሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 25፣ 41 እና 91 ላይ የተደነገጉትን የእኩልነትና የማህበራዊ ዋስትና መብታቸውን የጣሰ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም።

በመሆኑም ይግባኝ ለዘህ ም/ቤት ቀረበበት ውሳኔ በክርክሩ ሂደት ተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ለጉዳዩ አግባበነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ሕግን ተከትሎ የተሰጠ እንጂ ይ/ባይ ተጣሱብኝ የሚሏቸውን ሕገ መንግስታዊ ደንጋጌዎችን የጣሰ አይደለም።

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

መ/ቁጥር፡- 748/2015

ይግባኝ ባይ፤---------- እነ አቶ አዳነ ተክለሃይማኖት (2 ሰዎች)

ተጠሪ ፡---------- ወ/ሮ ሰንሰለት ወንድይፍራ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ</u>

ጉዳዩ ለም/ቤቱ ሊቀርብ የቻለው ይግባኝ ባዮች ነሐሴ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በተባ፥ አቤቱታ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት ይግባኝ ነው፡፡ ጉዳዩም ከውርስ ንብረት ጋር በተያያዘ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆኑ የአሁን ይግባኝ ባዮችን ጨምሮ በ3 ሰዎች ላይ ባቀረበችው ክስ መነሻ ነው፡፡

የክሷ መሰረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ለከሳሽ አያት እንዲሁም ለተከሳሾች እናት የሆኑት ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የቤት ቁ 008፣ 008/09 እና 029 የሆኑትን ቤቶች ጥለው የሞቱ ሲሆን ከሞቱ በኋላ ከሳሽ በቤቶቹ ውስጥ እስከ ቀን 21/04/2006 ዓ.ም ድረስ የቆየሁ ቢሆንም ከዚህ ጊዜ በኋላ ተከሳሾች ለብቻቸው በመያዝ ክስ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ብር 258,000 የውርስ ገንዘብ የሰበሰቡ ሲሆን ሟች አያታችን 4 የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ያሏቸው ሆኖ ከነዚህ ወስጥ የከሳሽ አባት አቶ ወንድራድ አለማየሁ አምስት ልጆች ያሉት በመሆኑ ከንብረቶቹ የአባቱ ድርሻ ላይ 1/5ኛ እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ይግባኝ ባዮች ለክሱ በሰጡት መልስ፡- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሳት እና በፍሬ ነገር ክርክር ደግሞ ከሳሽ ክስ ባቀረቡበት የቤት ቁ. 008/09 እና 029 ውስጥ ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ከመሞታቸው በፊትም ሆነ በኋላ ኖራ አታውቅም፣ ከእናቷ ጋር የምትኖረው መንግስት በወረሰው የቤት ቁ 007 ውስጥ ነው፡፡

ቤት ቁ 029 ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ የ1ኛ ተከሳሽ(አሁን 1ኛ ይግባኝ ባይ) የግል ንብረት ሲሆን የቤት ቁ. 008/09 ደግሞ የኑዛዜ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በውርስ ያገኙት የግላቸው ንብረት ነው፡፡ ስለዚህም የከሳሽ ክስ ውድቅ ወቺ ኪሳራ ተከፍሎን በነፃ እንድንሰናበት ይወሰንልን በማለት መከራከረቸውን ያሳያል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የተነሳውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ አድርጎ በማለፍ የግራ ቀኙን ክስና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም ስለአከራካሪዎቹ ቤቶች በትዕዛዝ ከሚመለከተው ቤቶች አሰተዳደር አካል መረጃ ተጣርቶ እንዲቀርብ ካስደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ቤት ቁ. 029 በሚመለከት ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ በህይወት እያሉ ለ1ኛ ተከሳሽ በስጦታ በሰጡት ይዞታ ላይ በራሱ ወጪ ሰርቶ የሚኖርበት ቤት ስለመሆኑ የተከሳሾቹ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡

ሟች ጥቅምት 02 ቀን 1993 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ላይም የቤት ቁ 029 በስጦታ ሰጥተውት በራሱም ወጪ ቤቶቹን ሰርቶ እንደሚኖር የተመለከተ ሲሆን ይህም ኑዛዜው ላይ በስቶታ ተሰጥቶ ቤቶቹን ሰርቶ እንደሚኖር ሟች ፅውቅና የሰጡበት እንጂ እንደአዲስ ኑዛዜ 1ኛ ተከሳሽ የተሰጠው መብት የሌለ በመሆኑ የኑዛዘው ተሸሽሎ የሟች ወራሾቸረ እንዲካፈሉ በሚል ውሳኔ መሰጠት 1ኛ ተከሳሽ በስጦታ ያገኘውን ንብረት ወደውርስ ሃብት በማስገባት እንዲያካፈሉ የሚገደድበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ እንዲሁም በዚህ ቤት ላይ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር የሚከፈለው በ1ኛ ተከሳሽ ስም ስለመሆኑ ቀረቡት ስነዶች የሚያረጋግጡ በመሆኑ የቤት ቁ. 029 የውርስ ሃብት ሳይሆን የ1ኛ ተከሳሽ የግል ሃብት ነው፡፡

በሌላ በኩል ቤት ቁጥር 008 እና 008/009 በሚመለከት ቤቶቹ በ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ተይዘው ያሉት በኑዛዜ ውርስ መሆኑ የተረጋገጠና የታመነ ሲሆን የሟች ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በኩል ተሻሽሎ ከሳሽም አባቷን በመወከል ልትካፈል ይገባል በሚል የተወሰነ በመሆኑ የቤት ቁ. 008. 008/009 አንድ ላይ የቤት ቁ. 008 ተብሎ የሚጠራው የውርስ ሃብት በመሆኑ ወራሾች እንደይራሽነት ደረጃቸውና ብዛታቸው ድርሻቸውን ሊካፈሉ ይገባል፤ ከቤቱ ኪራይ የተሰበሰበውን ገቢን በተመለከተም ተጣርቶ በቀረበው ውጤት መሠረት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የሰበሰቡትንና ክስ ከቀረበበት ጊዜ በኋላ የንብረቱን ድርሻቸውን እስከሚከፋፈሉ ድረስ ያለውን የኪራይ ገቢ ለወራሾች የድርሻቸውን እንዲከፍሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባዮች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በውሳኔው ላይ በስር ፍ/ቤት የተፈፀመ ስህተት የለም ተብሎ ውሳኔው ፀንቶባቸዋል፡፡

ይህንን ተከትሎም ይግባኝ ባዮች ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አቤቱታቸውን ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርበው ጉባኤውም ጉዳዩን በመ/ቁጥር 3750/11 ላይ ተቀብሎ ሲመለከት ከቆዬ በኋላ ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም መርምሮ ፍ/ቤት በጉዳዩ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው መቼ ነው የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የአሁን ተጠሪ የመቃወሚያ አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን በመመዘንና ሕጉን በመተርጎም በተሰጠው ሥልጣን አግባብ የተሰጠ እንጂ ሕገ-መንግስታዊ ትርጉም የሚያስነሳ ባለመሆኑ የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- የአሁን ተጠሪ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ባቀረቡት የመቃወሚያ አቤቱታ ሚች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ጥቅምት 05 ቀን 1993 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜም ሆነ በመዝቡ ላይ ለአሁን ይግባኝ ባዮች የተሰጠው የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ዳኝነት ጥያቄን በተመለከተ የከተማው መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃመወሚያው በ3 ዓመት ይርጋ ታግዷል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔውም በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀና ቢሆንም ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን መልስ ሰጪ በአዋጅ የተወረሰ ቤት ይመለሳል በማለት ሲጠበቁ የቆዩ ስለሆነ ያቀረቡት የመብት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1856/2 ላይ ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋ ደንብን መከላከያ አድርገው ለመጥቀስ እንደማይችሉ እንዲሁም ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት እንደሌለው እና በስር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅድመ ተከተሉ በሰ/መ/ቁ.33945(ቅፅ 8) እና ሰ/መ/ቁ.37762 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶ እያለ እነዚህን በመጣስ ሰበር ችሎቱ በገዛ ስልጣኑ የይርጋ መቃወሚያ በማንሳት እና ባልተጠየቀ ዳኝነት የሰጠው ውሳኔ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት 37 ላይ ለዜጎች የተሰጠውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚጻረር ከመሆኑም ባለፈ የመልስ ሰጪ የውርስ መብት በይርጋ የታገደና ክርክር የተነሳበት

ንብረት የይግባኝ ባዮች የግል ሆኖ እያለ መብታችንን የሚያሳጣን በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር ከመልስ ሰጪ የቀረበን ክርክር በመቀበል የተሰጠው ውሳኔ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 40/1 የተመለከተውን የንብረት መብታችንን የሚፃረር በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው ስለማይገባ የሕገ-መንግስት ትርጉም ሊሰጥበት ሲገባ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ስለሌለው ም/ቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኙ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተጣሱ ከተባሉት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ከሚለው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ይግባኝ ባዮች ለዚህ ም/ቤት አሁን ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መሠረታዊ ነጥብም የአሁን ተጠሪ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ሟች እማሆይ ጥሩነሽ ድንበሩ ያደረጉት ኑዛዜና የይግባኝ ባዮች የኑዛዜ ወራሽነት ውሳኔ ይሻርልኝ ስትል ያቀረበችው የመቃወሚያ አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የይርጋ መቃወሚያን በራሱ በማንሳትና ባልተጠየቀ ዳኝነት ውሳኔ ሰጥቷል በሚል ሲሆን የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣራ ጉባኤም ጉዳዩን ከዚሁ የይግባኝ ባዮች የይርጋ መከራከሪያ አንጻር በመመርመር ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ሲል ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ፍ/ቤት ማስረጃን ለመመዘንና ሕግን ለመተርጎም በተሰጠው ሥልጣን አግባብ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት መወሰኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ አንጻር ይግባኝ ባዮች ምንም እንኳን የተጠሪ የመቃወሚያ አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ አይደለም ሲባል አስቀድሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም ከተሰጠው ውሳኔ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ይህ ውሳኔ የተሰጠው ይግባኝ ባዮች አሁን ተጠሪ እንድትካፈል ተወስኗል የሚሉት የውርስ ንብረቶች ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ላይ የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ከመጀመሩ በፊት ሟች እማሆይ ጥሩነሽ በቀን 05/02/1993 ዓ.ም አደረጉት የተባለው ኑዛዜና የይግባኝ ባዮች የኑዛዜ ወራሽነት

ማስረጃ እንዲሻርላት ተጠሪ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ያቀረበችው የመቃወሚያ አቤቱታ ላይ አቤቱታው በይርጋ ይታገዳል በሚል የስር ፍ/ቤቶች ወስነው ነበር፡፡

ነገር ግን በተጠሪ አመልካችነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁኗ ተጠሪ የመቃወሚያ አቤቱታ በይርጋ ቀሪ ያልሆነ በመሆኑ በፍሬ-ነገር ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን በነጥብ በመለሰው መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በድጋሚ በይግባኝ ጭምር አይተው አከራካሪው ኑዛዜ የተጠሪን መብት የመውረስ መብት የሚጋፋ በመሆኑ ተሽሮ ተጠሪም አባቷን ተክታ መወረስ አለባት በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት በተወሰነላት የወራሽነት መብት መነሻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የውርስ ንብረት ክፍፍል ክስ በይግባኝ ባዮች ላይ መስርታ ከተከራከሩበት በኋላ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የውርስ ሃብት የሆነትንና ንብረቶች ለይቶ ግራ ቀኙ የሚገባቸውን ድርሻ እንዲከፋፈሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቶ ይህ ውሳኔም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ መዕናቱን ከጉዳዩ አጠቃላይ ታሪክ ለመገንዘብ የተቻለ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተመለከተው የጉዳዩ ታሪክ ለመረዳት የሚቻለውም ይግባኝ ባዮች አሁን ሕገ-መንግስታዊ መብታችንን የጣሰ ነው የሚሉት በይርጋ ክርክር ላይ የተሰጠው ውሳኔ እና አሁን በበስተመጨረሻ ይግባኝ ባዮች ወደዚህ ም/ቤት ለሕገ-መንግስት ትርጉም እንዲመጡ ያደረጋቸው የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሁለት ተለያዩ ጉዳዮች ሲሆን የተለያዩ ከመሆናቸውም የተነሳ የተለያየ አደረጃጀት ላይ ባሉ ፍ/ቤቶች በኩል የታዩ ሆነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ሁለቱንም ጉዳዮች በተለያየ ጊዜ ተመልክቶ የተለያየ ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

በዚሁም መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይርጋን አስመልክቶ ውሳኔ ሰጥቶ የነበረው በመጀመሪያው ክርክር ማለትም ከአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጀመረው ወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝ ክርክር ጉዳይ ላይ ሲሆን ይህንን ውሳኔ ግራ ቀኙ ተቀብለው ወደ ስር ፍ/ቤት በመመለስ በፍሬ-ነገር ጉዳይ ላይ ባደረጉት ክርክር ተጠሪም ሟች

እማሆይ ጥሩነሽን አባቷን ተክታ መውረስ ትችላለች የሚል ውሳኔ ተሰጥቶ በኑዛዜውና የወራሽነት ሰርተፊኬት ላይ የነበረው ክርክር እልባት አግኝቶ ተቋጭቷል፡፡

የወራሽነት ሰርተፊኬቱ ላይ የነበረው ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ላይ መቋጨቱን ተከትሎ የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ጉዳይን ለመዳኘት ሥልጣን ላለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ቀርቦ ሊታይ ችሏል፡፡

ከዚህ አኳያ የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲደረግ በአዲስ አበባ ፍ/ቤት ላይ በወራሽነት ሰርተፊኬት ላይ ሲደረግ የነበረው የይርጋና ተያይዥነት ያላቸው ክርክሮች አስቀድሞ እልባት አግኝቶ የተቋጨ ጉዳይ ሲሆን ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውርስ ሃብቱ ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተለይተው የውርስ ሃብት የተባሉትን ንብረቶች ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ በሚል መወሰኑን ተከትሎ ይግባኝ ባዮች በውሳኔው ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች ይግባኝ አቀርበው ሲፀናባቸው አሁን ላይ አስቀድሞ ውሳኔ ተሰጥቶበት ተቀብለው በፍሬ-ነገር ጉዳይ ጭምር ክርክር አድርገው የተቋጨን የይርጋ ጉዳይ ለዚህ ይግባኝ መከራከሪያ አድርገው ማቅረባቸው አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚሁም መሠረት ይግባኝ ባዮች አሁን ወደዚህ ም/ቤት የሕገ-መንግስት ትርጉም ይግባኝ እንዲያቀርቡ ያስቻለቸውና በውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር ላይ የተሰጠው የመጨረሻው ውሳኔ ላይ የተጣሰባቸው ሕገ-መንግስታዊ መብት ስለመኖሩ ክርክር ሳያቀርቡ ከአሁኑ ውሳኔ በፊት በሌላ ፍ/ቤት አስቀድሞው ውሳኔ ሲሰጥበት የተቀበሉትና ተቋጭቶም ሌላ የክርክር ውጤት ያስከተለን የይርጋ ጉዳይን በመጥቀስ ያቀረቡት የሕገ-መንግስት ትርጉም ይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም የሚያስፈለገው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም የቀረበለት የኢፌዲሪ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ምንም እንኳን ጉዳዩን ይግባኝ ባዮች የቀድሞ ውሳኔን መሠረት አድርገው ካቀረቡት የቅሬታ ነጥብ አንፃር በመመርመር የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በሚል የወሰነ ቢሆንም ይግባኝ ባዮች ከጅምሩ የሕገ መንግስት ትርጉም የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡበት ጉዳይ አስቀድሞ ውሳኔ አግኝቶ የተቋጨና ሌላ ራሱን የቻለ አዲስ ክርክር በማስከተለ በአዲሱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን ተከትሎ ቀድሞ በውሳኔ ተቋጭቶ የተዘጋን ጉዳይ ወደኋላ ሄደው በማንሳት የቅሬታ ነጥብ አድርገው ማቅረባቸው ተቀባይነት የሌለው ጉዳዩ ነው፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

መ/ቁጥር፡- 736/2015

ይግባኝ ባዮች፡---------- እነ አቶ ዘላለም ወሀቤ (2 ሰዎች)

ተጠሪ፡---------- የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ጉዳዩ ለም/ቤቱ ሊቀርብ የቻለው ይግባኝ ባዮች ሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት ይግባኝ ነው፡፡ ጉዳዩም የተተኪ አርበኞች የድጎማ አበል ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይግባኝ ባዮች ከአሁን ይግባኝ ውጭ ከሆኑት አቶ መላከፍስሐ አፈወርቅ ከተባሉት ጋር ለሦስት ከሳሽ በመሆን በመልስ ሰጪ ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡

የክሳቸው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ከሳሾች የአርበኞች ልጆች መሆናቸው ተረጋግጦ የተከሳሽ ማህበር አባል እንዲሆኑ የተደረገ በመሆኑ በተተኪነታቸው የጡረታ አበል ሊከፈላቸው ስለሚገባ ተከሳሽ ለከሳሾች ለእያንዳንዳቸው ሊከፈል የሚገባውንና በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የተለያየ የገንዘብ መጠን በአንድ ጊዜ እንዲከፍላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ፡- 3ኛ ከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ ይግባኝ ባይ) ያቀረቡት መታወቂያ በፕሬዚዳንት መሰጠት ሲገባው በምክትል ፕሬዚዳንት የተሰጠ በመሆኑ እየተመረመረ የሚገኝ ሲሆን በማህበሩ ሕገ-ደንብ መሠረት ተተኪ የአርበኛ ልጅ የድጎማ ድጋፍ እንደማያገኝ የተደነገገ በመሆኑ ለከሳሾች ጡረታ ለመክፈል ግዴታ ስለሌለብን ክሳቸው ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ጭብጥ ከያዘ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሹ ማህበር በደንብ የተቋቋመ የመተዳደሪያ ደንብ ያለው መሆኑ

በግራ ቀኙ የታመነ በመሆኑ ደንቡ ቀርቦ ሲታይ በደንቡ አንቀፅ 2.2 ስር ተተኪ ለተተኪ አርበኛ የተሰጠ መብት የአርበኛ ሙሉ መብት ሆኖ መብቱ ድጎማን የማያካትት መሆኑ የተደነገገ ሲሆን ከሳሾች በተተኪ አርበኛነት የገቡ በመሆኑ በማህበሩ ሕገ-ደንብ መሠረት የሚገባቸው ድጎማ የለም በማለት ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባዮች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በደንቡ (ደንብ 2006) አንቀፅ 2.2 ላይ ቃላትና ሐረጎችን በመተርጎም ተተኪ አርበኛ ምን ማለት እንደሆነ ከገለፀ በኋላ ተተኪ አርበኛን የድጎማ መብት እንደማያካትት የደነገገ ቢሆንም ደንቡ በአንቀፅ 11 ላይ የማህበሩ አባላት የሚገባቸውን መብትና ጥቅም እንዲሁም ግዴታ የሚያስቀምጥ በመሆኑ እነዚህ ሁለቱ ድንጋጌዎችን ለማስታረቅ አንቀፅ 2 የትርጓሜ ድንጋጌ በመሆኑ በሰዎች መብትና ጥቅም እንዲሁም ግዴታ የሚጥስ ባለመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት የሚኖረው የደንቡ አንቀፅ 11 ከመሆኑም ባለፈ ለሌሎች ተመሳሳይ አባላት የድጎማ መብት የተከበረላቸው መሆኑ በይግባኝ ባዮች የተነሳውን ክርክር መልስ ሰጪም ያመነ በመሆኑ ደንብ የወጣበት ዋና ዓላማ ሁሉም አባላት ተመሳሳይ ድጎማ እንዲያገኙ ለማስቻል በመሆኑ ለተወሰኑ አባላት የድጎማ መብት አስከብሮ ሌሎችን አይመለከታችሁም ማለት አሰራሩን ሕገ-ወጥና የተዛባ ስለሚያደርግ ይግባኝ ባዮች የማህበሩ አባል ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በደንቡ አንቀፅ 11 መሠረት የድጎማ መብታቸው ሊከፈላቸው ይገባል ሲል የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን መልስ ሰጪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከሳሾች ክስ ሲያቀርቡ የጠየቁት ዳኝነት የተተኪ አርበኛ የጡረታ አበል ይከፈለን በማለት ሲሆን የስር ፍ/ቤት ውሳኔው የሰጠው ደግሞ ተተኪ አባል የድጎማ አበል አይመለከተውም በማለት ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ ሲሆን በሌላ በኩል በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ 2006 አንቀፅ 11 ላይ ለአባላት የሚከፈል ድጎማ አበል የተዘረዘረ ቢሆንም የጡረታ አበልን በተመለከተ ግን በመተደደሪያ ደንቡ ላይ ያልተመለከተና በሌላ በኩል ከሳሾች ዳኝነት የጠየቁበትን የጡረታ ክፍያ ፍ/ቤቱ ክርክር በሚሰማበት ወቅት ተከሳሽ ለሌሎች 355 ወራሾች ድጎማ እየሰጠ ያለ በመሆኑ ለእኛም ሊሰጠን ይገባል በማለት ጡረታ መብትና ድጎማን በተለዋዋጭነት ሲጠቀሙ የሚታይ በመሆኑ ከሳሾች ክስ ላይ የጡረታ አበል በማለት የገለፁት

ምንድነው?፣ የድጎማ አበል ነው ወይስ ሌላ?፣ የጡረታ አበል ለተተኪ አርበኛ ሊከፈል የሚገባ መብት ነው አይደለም?፣ ሊከፈል የሚገባ ከሆነስ በምን ያህል መጠን? የሚሉትንና ተያያዥነት ያላቸውን ነጥቦችን የስር ፍ/ቤት እንደገና ግራ ቀኙን አከራክሮ በማጥራት እንዲወስን ሲል ጉዳዩን በነጥብ ለስር ፍ/ቤት በመመለስ ውስኗል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት ጉዳዩን በድጋሚ የተመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክስ በሚሰማበት ወቅት ከሳሾች በክሳቸው የጡረታ አበል ብለው የጠየቁት የድጎማ አበል መሆኑን በማረጋገጥ ተከሳሽ ለሌለሎች ተተኪ አርበኞች የድጎማ አበል እየከፈለ የሚገኝ በመሆኑ ለእኛም እንደማንኛውም አባል ሊከፈለን ይገባል በማለት በመከራከራቸው ጉዳዩን በድጋሚ መርምሮ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 11 ላይ አባላት ተመሳሳይ ድጎማ እንዲያገኙ እንደሚደረግ የሚያስቀምጥ ሲሆን በአንቀፅ 2.2 ላይ ለተተኪ አርበኛ በተሰጠው ትርጓሜ ላይ ተተኪው አርበኛ የአርበኛውን ሙሉ የሚያዝ ቢሆንም ይህ መብት ድጎማን ግን እንደማያካትት ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር ደንቡ በአንቀጽ 11 አባላት ተመሳሳይ ድጎማ እንዲያገኙ እንደሚደረግ ቢደነግግም በአንቀፅ 2.2 ላይ ተተኪ አርበኛ የድጎማ መብት እንደማያገኝ መደንገጉ በአንቀፅ 11 መሠረት ተመሳሳይ ድጎማ እንዲያገኙ መብት የሚሰጣቸው ከተተኪ አርበኛ ውጭ ያሉ የማህሩን አባላት ስለመሆኑ የሚያስገነዘብ በመሆኑ ተተኪ አርበኛ የሆኑት ከሳሾች የድጎማ አበል ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ሊከፈላቸው የሚገባ የድጎማ ክፍያ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ይግባኝ ባዮች አሁንም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ አያስቀርብም ተብሎ በመሰረዙ የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በውሳኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ አቤቱታው ለሰበር ችሎት አያስቀርብም ተብሎ በትዕዛዝ ተዘግቶባቸዋል፡፡

ይህንን ተከትሎም ይግባኝ ባዮች ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አቤቱታቸውን ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡ ቢሆንም ጉባኤው ጉዳዩን ተቀብሎ በመ/ቁጥር 7587/15 ላይ ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ.ም መርምሮ በፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በማህበሩ ደንብ መሠረት ለተተኪ አርበኞች የድጎማ አበል እንዲከፈል የሚፈቅድ ድንጋጌ

አለመኖሩን በማረጋገጥ በመሆኑና በሕግ ያልተጠበቀ መብት ሊከበር የሚችልበት አግባብም ባለመኖሩ ውሳኔው የጣሰው ሕገ-መንግስታዊ መብት ስለሌለ ውሳኔው የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- በመልስ ሰጪ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ 2006 አንቀፅ 8.1 ላይ ተተኪ አርበኛ የማህበሩ አባል እንደሆነ የተደነገገ በመሆኑ እኛ ይግባኝ ባዮች የአርበኛ ልጆች መሆናችንን በወራሽነት ማስረጃ አረጋገጠን በደንቡ አንቀፅ 2.1. እና 2.2 መሠረት ተተኪ አርበኞች መሆናችንን ያረጋገጠን ሲሆን በደንቡ አንቀፅ 11 ላይ ድጎማን በሚመለከት ተተኪ አርበኞች አባላት የሚያገኙትን ድጎማ እንደሚያገኙ የተገለፀ በመሆኑ ለይግባኝ ባዮች ሌሎች የአርበኛ አባላት የሚያገኙት ድጎማ እንዲከፈለን ሊወሰን ሲገባ ለተተኪ አርበኞች ደጎማ አይከፈልም መባሉ በሕገ መንግስት አንቀፅ 25 ላይ ሁሉም ዜጋ እኩል የመዳኘትና መብቱ ሊከበርለት እንደሚገባ የተደነገገውን አንቀፅ የሚጥስ፤ የኢትዮጵያዊነትና የአገራዊ አርበኛነት መንፈስ ማስተማሪያ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ መቀጠል ስላለበትና ይህም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስና ባህል ሆኖ እንዲቀጥል ተተኪ አርበኞች በደንቡ እንዲካተቱ ተደርጎ ይህም የማይዳሰስ የታሪክ ቅርስን መጠበቂያ ዘዴ ሆኖ ባለበት ለተተኪ አርበኞች በደንቡ መሠረት ሊሰጥ የሚገባው ድጎማ ያለአድሎ በእኩልነት ለሁሉም አባላት አለመሰጠቱ ተተኪ አርበኞችን የማፍራት ሂደት በማቋረጥ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 91/2 ላይ የተመለከተውን የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግስትና የሁሉም ኢትዮጵያ ግዴታን የሚጥስ፣ እንዲሁም ክሳችንን አብራርተን ግልፅ በማድረግ አሻሽለን አቅርበን እንዲታይልን ጠይቀን በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አታሻሽሉም ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱና በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም ይህ አለመስተካከሉ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 37 ላይ የተገለፀውን ፍትህ የማግኘት መብታችንን የሚጥስ በመሆኑ ውሳኔው ሕገ-መንግስትን የሚቃረን ነው ተብሎ በምክር ቤቱ የሕገ-መንግስት ትርጉም ይሰጥልን የሚል ነው፡፡

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኙ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተጣሱ ከተባሉት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ከሚለው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ይ/ባዮች አጥብቀው ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ዋነኛ የቅረታ ነጥብ አድርገው የሚያነሱት ነጥብ በተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ 2006 ላይ ተተኪ አርበኛ የማህበሩ አባል መሆኑ ተደንግጎ እያለና ተጠሪ ለሌሎች ተተኪ አርበኞች ድጎማ እየሰጠ ያለ ሆኖ ለእኛ ግን መንፈጉ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 እና 91/2 ላይ የተመለከተውን የእኩልነት መብት እና የሀገሪቱን የታሪክ ቅርሶችን መንግስትና ሁሉም ዜጎች የመጠበቅ ግዴታን የሚጥስ ነው በማለት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ይ/ባዮች ሊከፈለን ይገባል በማለት የዳኝነት ጥያቄ ያቀረቡበት የድጎማ መብት በሕገ መንግስቱ ላይ የሀገር ታሪክ ቅርሶችን ከመጠበቅ ግዴታ ጋር በተያያዘ በግልፅ የተመለከተ ባለመሆኑ ይ/ባዮች መብቱን ያጎናፅፈናል በማለት በሚከራከሩበት የተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ድጎማ ለተተኪ አርበኞች በእርግጥም የተጠበቀ መብት ስለመሆኑ መመርመር የሚያስፈልግ ነው፡፡ በዚሁም መሠረት ጉዳዩን በፍሬ ነገር ረገድ ያጣሩት ፍ/ቤቶች አከራካሪው የተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ 2006 የተባለውን አስቀርቦ ሙሉ ይዘቱን ጭምር የተመለከቱ ሲሆን በይዘቱም ተተኪ አርበኞች ለአርበኛው የተሰጠው ሙሉ መብት የሚኖራቸው ቢሆንም መብቱ ግን ድጎማን የማያካትት ስለመሆኑ ከደንቡ አንቀፅ 2(2) ድንጋጌ አረጋግጠዋል፡፡

በመሠረቱ ለማንኛውም ሰው መብት ሊፈጠር የሚችለው ከሕግ አልያም ከውል መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በተያዘው ጉዳይ ይ/ባዮች መብት ይሰጠናል በማለት እየተከረከሩ ያሉት ሕግን ቢሆንም ይ/ባዮች መብት ይሰጠናል በማለት የሚያነሱት ሕግ ማለትም የተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ 2006 ለተተኪ አርበኞች አርበኛው የሚኖሩትን ሌሎች መብቶችን ቢያጎናፅፍም ድጎማን በተመለከተ ግን ቃል በቃል በግልፅ ከልክሏል፡፡ ስለዚህም መብት ይፈጥራል የተባለው ደንብ ለተተኪ አርበኞች ድጎማን በግልፅ የሚከለክል እስከሆነ ድረስ ለይ/ባዮች ከሕግ ውጭ መብቱ ሊከበር የሚችልበት አግባብ የማይኖር ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ይ/ባዮች ምንም እንኳን ተጠሪ ለሌሎች ተተኪ አርበኞች የድጎማ መብት ጠብቆ እያለ ለእኛ ግን ለይቶ መከልከሉ የእኩልነት መብታችንን ይጥሰሳል በማለት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪ ከይ/ባዮች ውጭ ላሉ ሌሎች ተተኪ አርበኞች ድጎማ የሚሰጥ ስለመሆኑ በግልፅ በፍሬ ነግር ካለመረጋገጡም ባለፈ እየሰጠ እንኳን ቢገኝ በሕግ ያልተፈቀደን መብት እያስፈፀመ ያለው አካል ከሕግ ውጭ በመስራቱ የሕግ ተጠያቂነትን ከሚያስከትልበት በስተቀር ከሕግ ውጭ የሆነውን አሰራሩን እንደ አስገዳጅ ሕግ በመቁጠር መከራከሪያ አድርጎ ለማንሳትና መጠቀሚያ ለማድረግ የሚቻልበት አግባብ የሌለ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ይ/ባዮች በተተኪ አርበኛነታቸው ድጎማ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከተጠሪ የመተዳደሪያ ደንብ አንፃር ሲታይ ደንቡ ድጎማን ለተተኪ አርበኞች የማይፈቅድ ሆኖ በመገኘቱ ጥያቄቸውን ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ሕግ ተከትሎ የተሰጠ ነው ከሚባል በስተቀር የይ/ባዮችን ሕገ መንግስታዊ የእኩልነት መብት እና የሀገሪቱን የታሪክ ቅርሶችን የመጠበቅ ግዴታ ድንጋጌዎችን የጣሰ ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ውሳኔው የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁጥር፡- 737/2015

ይግባኝ ባይ፡---------- አቶ መኮንን ግርማ

ተጠሪ፡---------- የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ጉዳዩ ለም/ቤቱ ሊቀርብ የቻለው ይግባኝ ባይ ሐምሌ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በተባፈ አቤቱታ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት ይግባኝ ነው፡፡ ጉዳዩም የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የጀመረው የይግባኝ ባይ አሰሪ መ/ቤት ለመልስ ሰጪው ኤጀንሲ በቀን 22/07/2008 ዓ.ም ባቀረቡት ጥያቄ መነሻ ሆኖ ይግባኝ ባይ በፌዴራል መንግስት ሰራተኛነት በቋሚነት ተቀጥረው በቀድሞ ሚቶ እርሻ ልማት ድርጅት ለ17 ዓመት ከ11 ወራት ያገለገሉበትን የረጅም ጊዜ የጡረታ መዋጮ መልስ ሰጪ እንዲመልሱላቸው ጠይቀው ተጠሪ ጥያቄውን ተመልክቶ የይግባኝ ባይ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል የሚል ውሳኔ በመስጠቱ ነው፡፡

ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጪን ውሳኔ በመቃወም ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ባቀረቡት አቤቱታ ይግባኝ ባይ በወቅቱ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ያልጠየቁት በሽተኛና የአልጋ ቁራኛ ሰለነበሩ እና የሚንቀሳቀሱበት ገንዘብ ስላልነበራቸው በመሆኑ በአላጌ ግብርና ኮሌጅ ለ10 ዓመት ከ1ወር ያህል ያገለገሉበትና የደከሙበት የጡረታ መብታቸው እንዲከበርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከመስሪያ ቤታቸው የቀረቡት ሰነዶች ይግባኝ ባይ አገልግሎታቸው ለ17 ዓመት ከ7 ወር ያህል ያገለገሉበት የቀድሞ ሚቶ የእርሻ ልማት ድርጅት ሲዘጋ የተሰናበቱ ሲሆን ይህም ከ20 ዓመት በታች በመሆኑ መብታቸው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ማድረግ ቢሆንም አመልካች ጥያቄ ያቀረቡት ከ10 ዓመት ጊዜ በኋላ ነው። ይህም በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀፅ 43/3 ላይ በተቀመጠው የ2 ዓመት ይርጋ ጊዜ የሚታገድ በመሆኑ ተመላሽ የሚደረግ ነገር የለም ሲሉ ተከራክረዋል።

ይግባኝ ሰሚው ጉባኤም የግራ ቀኙን ክስ ሰምቶና የይግባኝ ባይን ማህደር ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ባይ ቀድሞ በሞሉት ሕይወት ታሪክ ፎርም ላይ የትውልድ ዘመናቸው 18/8/37 ሲሆን በጡረታ የሚገለሉበት ጊዜ 09/09/1992 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ከአሰሪ መ/ቤታቸው የጡረታ መብት የተጠየቀላቸውም በ30/8/2007 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል። በመሆኑም ጥያቄው የቀረበው በአዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀፅ 43 ላይ ከተመለከተው የ2 ዓመት ጊዜ በኋላ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል በማለት መልስ ሰጪው ኤጀንሲ የሰጠው ውሳኔ በደንብና መመሪያ መሠረት ነው ሲል ውሳኔውን አፅንቷል።

ይግባኝ ባይ በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በውሳኔው ላይ የተፈፀመ ስህተት የለም ተብሎ በየደረጃው ውሳኔው ፀንቶ መዝገቡ በትዕዛዝ ተዘግቶባቸዋል።

ይህንን ተከትሎም ይግባኝ ባይ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አቤቱታውን ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረቡ ቢሆንም ጉባኤው ጉዳዩን ተቀብሎ በመ/ቁጥር 3582/11 ላይ መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም መርምሮ የይ/ባይ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ በይርጋ ይታገዳል በሚል የተሰጠው ውሳኔ በሕጉ ላይ የተጠቀሰውን የይርጋ ጊዜ መሠረት በማድረግ ሲሆን ይህም የሆነው ይ/ባይ መብታቸውን ጊዜውን ጠብቀው የመጠየቅ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በመሆኑ ውሳኔው የጣሰው ሕገ መንግስታዊ መብት ስለሌለ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

የአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ይግባኝ ባይ በፌዴራል መንግስት ሠራተኛነት በቋሚነት ተቀጥሬ በቀድሞ ሚቶ እርሻ ልማት ለ17 ዓመት ከ7 ወር

ከ11 ቀን እና በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ኮሌጅ ለ10 ዓመት ከ1 ወር ከ10 ቀን በአጠቃላይም ለ27 ዓመት ከ8 ወር ከ21 ቀናት ካገለገልኩ በኋላ ከግንቦት 01 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ የተገለልኩ በመሆኑ ዘላቂ የጡረታ አበል እንዲወሰንልኝ ላቀረብኩት ጥያቄ አገልግሎትህ ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የጡረታ አበል አይወሰንልህም፤ ሊወሰን የሚችለው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ነው ከተባለ በኋላ የጡረታ መዋጮ ተመላሹም በአዋጅ ቁ.345/95 አንቀፅ 43/2 መሠረት በይርጋ ይታገዳል ሲባል የተሰጠው ውሳኔ አዋጅ ቁ.345/95 ተሽሮ በአዋጅ ቁ.714/2003 ባለበት የተሻረውን ሕግ መሠረት በማድረግ ተሰጠ ነው።

በሌላ በኩል የይግባኝ ባይ የልደት ቀን ሚያዚያ 18/1947 ዓ.ም ሳይሆን ሚያዚያ 18 ቀን 1937 ዓ.ም ባለመሆኑ ለመጨረሻ ጊዜ ያገለገልኩበት አሰሪ መ/ቤቱ የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ኮሌጅ የጡረታ መብቱ እንዲጠበቅ ለመልስ ሰጪ ጥያቄ ያቀረበው ሚያዚያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በመሆኑ የጡረታ መብቱ እንዲከበር የጠየቅኩት አሰሪዬ በጡረታ እንድገለል ባደረገበት ጊዜ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ሊነሳ የሚችል ይርጋ በሌለበት መብቱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ እንዲሁም የይግባኝ ባይ የቀድሞ አሰሪ ሚቶ እርሻ ልማት ድርጅት በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም የተደረገውን የመንግስት ለውጥ ተከትሎ የፈረሰ በመሆኑ ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መረጃ የማስተላለፍ ግዴታውን በወቅቱ ያልተወጣና ሊወጣም የሚችልበት ያልነበረ በመሆኑ በዚህ አግባብ የባከነው ጊዜ በአዋጅ ቁ. 714/2003 አንቀፅ 49/4(ለ) መሠረት ለይርጋ የማይቆጠር ሆኖ እያለ የይግባኝ ባይ መብት በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ከሕግ አግባብ ውጭ ከመሆኑም ባለፈ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 37 ላይ የተመለከተውን የይግባኝ ባይ ፍትህ የማግኘት መብት እና በአንቀፅ 41 ላይ የተመለከተውን የማህበራዊ መብት ተጠቃሚነትን የማቃረን በመሆኑ ምክር ቤቱ ከነዚህ የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር ላይ በጉዳዩ ላይ የሕገ-መንግስት ትርጉም ይስጥበት የሚል ነው።

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኙ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተጣሱ ከተባሉት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ከሚለው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም ይ/ባይ የሕገ መንግስት ትርጉም ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡበት መሠረታዊ ነጥብ በመንግስት ሠራተኛነት በቀድሞ ሚቶ እርሻ ልማት ከ17 ዓመታት በላይ እና በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ኮሌጅ ከ10 ዓመት በላይ በአጠቃላይም ከ27 ዓመታት በላይ ያገለገልኩ በመሆኑ የጡረታ መብት ሊከበርልኝ ሲገባ አገልግልትህ ከ20 ዓመት በታች በመሆኑ ሊወሰንልህ የሚገባው የጡረታ አበል ሳይሆን የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ነው ከተባለ በኋላ የጡረታ መዋጮ ተመላሹም በይርጋ ይታገዳል በሚል የተሰጠው ውሳኔ የክደት ዘመኔ ሚያዚያ 18 ቀን 1937 ዓ.ም ሳይሆን ሚያዚያ 18 ቀን 1947 ዓ.ም በመሆኑ ለመጨራሻ ጊዜ ያገለገልኩበት የአላጌ ግብርና ቴክ/ኮሌጅ የጡረታ መብቴ እንዲጠበቅ ጥያቄ ያቀረበው ሚያዚያ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ መብቱ በይርጋ የሚችልበት አግባብ ሳይኖር በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ 714/2003 ተተክቶ የተሻረን አዋጅ ቁ.345/95 በመጥቀስ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሰህተት በመፈፀመ የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 41 ላይ የተጠበቀልኝን የማህበራዊ ዋስትና መብቴን የጣሰ ነው የሚል ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የይ/ባይ ሕገ መንግስታዊ የማህበራዊ ዋስትና መብት ተጥሷል ወይስ አልተጣሰም የሚለውን ለመመለስ ጉዳዩን አስቀድሞ ተመልክተው ውሳኔውን በሰጡት አካላት በቀረቡት ማስረጃች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ማየት የሚያስፈልግ ነው፡፡

በዚሁም መሠረት ይ/ባይ በመንግስት ሠራተኛነት በ2 ተቋማት ማለትም በቀድሞ ሚቶ እርሻ ልማት እና በአላጌ ግብርና ቴክ/ኮሌጅ በድምሩ ከ27 ዓመታት በላይ ማገልገላቸው ግራ ቀኙን ያላከረከረ ሲሆን ይ/ባይ በመጀመሪያ በሚቶ እርሻ ልማት ውስጥ ሲቀጠሩ በወቅቱ በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ላይ የልደት ዘመናቸው ሚያዚያ 18 ቀን 1937 ዓ.ም በሚል በፊርማቸው አረጋግጠው የሞሉ መሆኑ ማህደራቸው ተፈትሾ መረጃው ተረጋግጧል፡፡ ይ/ባይ በዚሁ በሚቶ እርሻ ልማት ውስጥ ከቀን 20/07/67 ዓ.ም እስከ 30/02/1985 ዓ.ም ድረስ ለ17 ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ ድርጅቱ በመዘጋቱ ከሥራቸው ተሰናብተው ቆይተው ከመጋቢት 21 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በአላጌ ግብርና ቴክ/ኮሌጅ ማገልገላቸውን ለኤጀንሲው የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ግልባጭ ያሳያሉ፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መብት ጉዳይ የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ ስለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ በየጊዜው እየተሻሻሉ የሚወጡት ሕጎች ሲሆኑ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው የቱረታ መብት ክርክር የተነሳው በ2008 ዓ.ም እንደመሆኑ

በወቅቱ በሥራ ላይ የነበረውና ተፈፃሚነት ያለው ሕግ ስለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁ.714/2003 እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ኤጀንሲው ለይ/ባይ አቤቱታ ውሳኔውን ከአዋጅ ቁ.345/95 አንፃር የሰጠ ቢሆንም ይህ አዋጅ ክርክሩ በተነሳበት ወቅት በሥራ ላይ ያልነበረ ወይም የተሻረ ሕግ በመሆኑ ኤጀንሲው በሕግ አጠቃቃስ ረገድ ስህተት መፈፀሙሙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ይሁን አንጂ አዋጅ ቁ.345/95 እና አዋጅ ቁ. 714/2003 በአንዳንደድ ጉዳዮች ላይ ካልሆነ በስተቀር በመሠረታዊ ይዘት ረገድ ተመሳሳይነት ያላቸውና በተለይም የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ እና የጡረታ መብት የሚጠበቅበትን ጊዜ አስመልክቶ ተመሳሳይ ድንጋጌዎችን የያዙ ስለመሆኑ ከአዋጆቹ ይዘት ለመረዳት የሚቻል ነው፡፡

በዚሁም መሠረት በአዋጅ ቁ.714/2003 አግባብ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሠረት በማድረግ 60 ዓመት ስለመሆኑ በአንቀፅ 18/1(ሐ) ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አኳያ ለይ/ባይ ሊከበር ይገተባ የነበረው የጡረታ አበል ነው ወይስ የጡረታ መዋቾ ተመላሽ ነው የሚለውን በቅድሚያ ስንመለከት ይ/ባይ በሚቶ እርሻ ልማት ያገለገሉት 17 ዓመት ያህል ብቻ መሆኑ ተረገግጧል፡፡ በአዋጅ ቁ. 714/2003 መሠረት ከ20 ዓመት በታች ነገር ግን ከ10 ዓመት በላይ አገልግሎት ያለው ሠራተኛ የጡረታ አበል የማይከፈለው ሲሆን ሊከፈለው የሚገባው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀፅ 19/2 እና 27/1(ሀ) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ያስገነዝባሉ፡፡

ይግባኝ ባይ መጀመሪያ በሚቶ የእርሻ ልማት ሲቀጠሩ የሞሉት የልደት ዘመን ሚያዚያ 18 ቀን 1937 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ የጡረታ መውጫቸው በ1997 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ስሌቱ ያስገነዝባል፡፡ ይ/ባይ በዚህ የእርሻ ልማት ውስጥ ያገለገሉትም ለ17 ዓመት ብቻ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በሌላ በኩል ይ/ባይ በሚቶ እርሻ ልማት ካገለገሉት 17 ዓመት በተጨማሪ በአላጌ ግብርና ቴክ/ኮሌጅ ለ10 ዓመታት ያህል አገልግያለሁ በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ይህንን አገልግሎት የሰጡት መቼ ነው የሚለው ሲታይ ከመጋቢት 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

በመሠረቱ ሠራተኛው ከጡረታ መውጫ ዕድሜው በኋላ አገልግሎቱ በሕግ መሠረት ተራዝሞለት በሥራ ላይ እንዲቆይ የተደረገበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ከጡረታ መውጫ

መውጫ ዕድሜ በኋላ ያለው የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ የማይደረግ ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.714/2003 አንቀፅ 17/3(ሀ) ድንጋጌ የሚያስገነዝብ ነው። ከዚህ አኳያ ይ/ባይ መጀመሪያ ሲቀጠሩ ከሞሉት የልደት ዘመናቸው አንፃር የጡረታ መውጫቸው በ1997 ዓ.ም በመሆኑ ከ1997 ዓ.ም ወዲህ በአላጌ ግብርና ቴክ/ኮሌጅ ጊዜ ለጡረታ አበል ዓላማ ሊታሰብላቸው የሚችል አይደለም።

ስለዚህም የይ/ባይ የአገልግሎት ዘመን ከ20 ዓመት በታች በመሆኑ ሊከፈላቸው የሚገባው የጡረታ አበል ሳይሆን የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ነው መባሉ ከመንግስት ሠራተኞች የቱረታ አዋጅ ቁ.714/2003 አኳያ በአግባቡ ነው።

ከዚህ በመቀጠል የይ/ባይ የቱረታ መዋጮ ተመላሽ በይርጋ ይታገዳል የመባሉን አግባብነት ስንመለከት የይ/ባይ ጡረታ መውጫ ጊዜ 1997 ዓ.ም እንደሆነ የእድሜአቸው ስሌት የሚያስገነዝብ ሲሆን የይ/ባይ የጡረታ መብት እንዲከበር ጥያቄ ለኤጀንሲው የቀረበው ደግሞ በ2008 ዓ.ም በመሆኑ ይህ ጊዜ ሲሰላ ከ10 ዓመት ያለፈው ስለመሆኑ ለመረዳት ይቻላል። በአዋጅ ቁ.714/2003 መሠረት ደግሞ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ጥያቄን በሚመለከት የሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከሞላ ወይም ከሞተ ከ3 ዓመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑና ይህ ጊዜም መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ ስለመሆኑ በአንቀፅ 49(2) እና (3) ስር በግልፅ ተደንግገኗል።

በመሆኑም የይ/ባይ የጡረታ ተመላሽ ጥያቄ ለኤጀንሰው የቀረበው የይ/ባይ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከሞላ በሕጉ ላይ የተመለከተው የ3 ዓመት ይርጋ ጊዜ ካለፈው በኋላ ለዛውም 10 ዓመት አልፎት በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል መባሉም በአግባቡ ነው።

ሲጠቃለልም የይ/ባይ የጡረታ መብት ጥያቄ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔ የተሰጠው ጉዳዩን በፍሬ ነገር በማጣራት ወቅት ከተረጋገጠጠው የይ/ባይ የአገልግሎት ዘመን፣ የልደት ዘመን እንዲሁም ጥያቄው ከቀረበበት ቆይታ አንፃር በሥራ ላይ የነበረው የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ የጡረታ አበልን የማያስገኝላቸውን ይ/ባይ ሊያገኙ ይችሉ የነበረው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ም በይርጋ የሚሚገድ ሆኖ በመገኘቱ ሲሆን ይህም ሕግና ማስረጃን በአግባቡ በመመዘን የተሰጠ ውሳኔ ነው ከሚባል በስተቀር የይ/ባይን ሕገ-መንግስታዊ የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥሷል ለመላት የሚቻል ባለመሆኑ ውሳኔው የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ሆኖ አልተገኘም።

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡

የይ/መ/ቁጥር፡- 756/2015

ይግባኝ ባይ፡---------- ወ/ሮ ወርቁ ኤርጋኖ

ተጠሪ፡---------- ወ/ሮ ዘነበች ላቾሬ

<u>የይግባኝ አቤቱታው ባጭሩ፣</u>

ጉዳዩ ለም/ቤቱ ሊቀርብ የቻለው ይግባኝ ባይ ነሐሴ 23 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት ይግባኝ ነው፡፡

ጉዳዩም ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በከምባታ ጠንባሮ ዞን ሀደሮ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ላይ የአሁን ይግባኝ ባይ ከሳሽ በመሆን ከአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ ውጭ ከሆኑት የቀድሞ ባለቤታቸው አቶ ዘለቀ አሸንጎ ጋር በነበራቸው የንብረት ክፍፍል ክርክር ላይ የአሁን መልስ ሰጪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

መልስ ሰጪ በጣልቃ ገብነት ያቀረቡት አቤቱታም መሠረታዊ ይዘቱ ባጭሩ ሲታይ፡- ከሳሽ (የአሁን ይግባኝ ባይ) ከተከሳሽ (አቶ ዘለቀ አሸንጎ) ጋር ከሚከራከሩባቸው ንብረቶች መካከል በሀደሮ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ 3(ሦስት) የተለያየ ቆርቆሮ ክዳን ቤቶች፤ 2(ሁለት) በተለያዩ አዋሳኞች መካከል የሚገኙ ባህር ዛፍ ከነይዞታቸው፤ እንዲሁም አዋሳኞቹ በክሱ ላይ በተጠቀሰ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ቡና ከነይዞታው በዋናነት የተፈሩት ተከሳሽ እና ጣ/ገብ በ1968 ዓ.ም ጋብቻ መስርተን ባለንበት ተከሳሽ ለውትደርና ሲሄድ በወቅቱ የቦታ ጥበት ስለነበረብን በወቅቱ ከነበሩ ቀበሌ አመራሮች መሬተን ተቀብዬ ቡናና ባህር ዛፍ ተክዬበት ተከሳሽ ከውትደርና እስኪመለስ ድረስ ከልጆቼ ጋር ስጠቀምበት የቆየሁ ሲሆን ተከሳሽ ከተመለሰ በኋላ አስፈራርቶኝ ያለፈቃዴና ይሁንታ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው ውስጥ ከከሳሽ ጋር እየኖረ የአሁኖቹን ቤቶች ከይዞታው ለይ እየቆረሱ በመሸጥና በቦታው ላይ የተከልኳቸውን ቡናና ባህር

ዛፍ በመሸጥ የሰሩት እንጂ ከሳሽ አንዳችም ቤቱን የሰራችበት የራሷ የገቢ ምንጭ የሌላት እንዲሁም በራሷ ጥረት ያፈራቸው ባለመሆኑ የአከራካሪዎች ይዞታና በይዞታው ላይ ያሉ ንብረቶች ግማሽ ድርሻ የጣልቃ ገብ ነው ተብሎ ከሳሽ በንብረቱ ላይ መብት አላት የሚባል ከሆነ ከተከሳሽ ድርሻ እንድትጋራ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቋን ያሳያል፡፡

ከሳሽ (የአሁን ይግባኝ ባይ) ለጣልቃ-ገብ አቤቱታ በሰጡት መልስ፡- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማንሳት እና በፍሬ ነገር ክርክር ደግሞ የጣ/ገብ ጋብቻ በሁኔታ በ1982 ዓ.ም የፈረሰ ነው፤ ከሳሽና ተከሳሽ ትዳር ከመሰረቱበት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ምንም ንብረት አላፈሩም ተብሎ ግምት አይወሰድም፤ አከራካሪውን ይዞታ ተከሳሽ ውትድርና ላይ እያለ ጣ/ገብ የተመራችው ሳይሆን ይዞታው ለተከሳሽ ተመርቶ ጫካ የነበረውን መንጥረን አከራካሪዎቹን ንብረቶች አፍርተንበታል፤ ጣ/ገብ ቤቶቹን አልሰራችም፣ ቤቶቹ የተሰሩት ይዞታው ተሸጦ ነው ብትልም ያቀረበችው የሽያጭ ውል የለም፤ በይዞታው ላይ ፈፅሞ ኖራ አታውቅም፣ ገብታም አታውቅም፡፡

ስለዚህም አከራካሪዎቹ ንብረቶች በከሳሽና ተከሳሽ ልፋትና ጥረት የተፈሩ በመሆኑ ንብረቶቹ የከሳሽና ተከሳሽ የጋራ ናቸው ተብሎ ተወስኖ የጣ/ገብ አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡ የስር ተከሳሽ (አቶ ዘለቀ አሸንጎ) በበኩል ለጣልቃ ገብ አቤቱታ በሰጠው መልስ አቤቱታውን ሙሉ ለሙሉ በመደገፍ ጣ/ገብ ያቀረበቸው ክርክር እውነተኛ እና የሚነቀፍ ነገር የሌለበት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ማስረጃ ሰምቶ የሚወስነውን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የተነሳውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና የአከራካሪውን ቦታ ምልከታ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በቀረቡት የግራ ቀኙ ማስረጃዎች እና በቦታው ምልከታ ወቅት ከአካባቢው ገለልተኛ ሽማግሌዎች በተገኘው ቃል መሠረት ይዞታው በተከሳሽ ስም ሚስቱ ለሆነችው ጣ/ገብ መመራቱን፤ ጣ/ገብ ይዞታውን ተመርታ በይዞታው ላይ ቡናና ባህርዛፍ በቀበሌ ህዝብ በማስተከል ስትጠቀም መቆየቷን፤ ሆኖም ተከሳሽ ያለጣ/ገብ ፈቃድ በጉልበትና በማስፈራራት ከሳሽን በይዞታው ላይ በማምጣት ማኖሩን፤ ከዛን በኋላም ከሳሽና ተከሳሽ ከይዞታው ቆራርጠው በመሸጥ ቤቶቹን መስራታቸው ተረጋግጧል፡፡

ስለዚህም ተከሳሽ ከጣ/ገብ ጋር በጋራ እንዲጠቀሙ በህግ ከተመራው ይዞታ ተሸጦ የተፈራው ንብረት ከጣ/ገብ ፈቃድ ውጭ በተከሳሽ ተፅዕኖ ጣ/ገብ ለመከላከል እንዳትችል ተደርጎ ከሳሽ የገባችበት በመሆኑ የጣ/ገብ መብት ተለይቶ ሳይሰጥና ድርሻዋን ሳታገኝ ከሳሽ ይዘታውን ከሕግ ውጭ ሙሉ ለሙሉ ጠቅልዬ ይዣ*ያለሁ* በማለት የምታቀርበው ክርክር በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 35/7 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ. 120844 (ቅፅ 20) ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ጣ/ገብ ከአከራከሪዎቹ ንብረቶች ግማሹን የማግኘት መብት ያላት ሲሆን ቀሪውን ግማሽ ከሳሽና ተከሳሽ ይካፈሉ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል።

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታዋን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርባ ከፍተኛ ፍ/ቤቱም ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ መዝገቡን መርምሮ አከራከሪው ይዞታን የስር ተከሳሽ ከውትደርና መልስ ጣ/ገብን አባርሮ ጣ/ገብ ትታ ሄዳ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ተጠቃማ የማታውቅ፤ እንዲሁም ይዞታውን ሸጠው ቤትም የሰሩበት ከሳሽና ተከሳሽ ብቻ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ጣ/ገብ ይዞታውን የማስተዳደር፣ የመጠቀምና ንብረት የማፍራት መብቷ ለረጅም ጊዜ የተቋረጠ ሆኖ እያለ ከጠቅላላው አከራካሪዎቹ ይዞታ ግማሹን ተካፈል መባሉ ተገቢ ስላልሆነ ንብረቱን ከሳሽና ተከሳሽ ብቻ ይካፈሉ ሲል የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ በበኩሏ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርባ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ መዝገቡን መርምሮ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ጣ/ገብ ከአከራካሪዎቹ ይዞታና ከተፈራው ንብረት ግማሹን ልታገኝ ይገባል ሲል የስር የሀደሮ ከተማ አስተዳደር የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል።

የአሁን ይግባኝ ባይ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ብታቀርብም በውሳኔው ላይ በስር ፍ/ቤት የተፈፀመ መሠረታዊ ስህተት የለም ተብሎ ውሳኔው ፀንቶባታል።

ይህንን ተከትሎም ይግባኝ ባይ ጉዳዩ የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት አቤቱታዋን ለሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቅርበው ጉባኤውም ጉዳዩን በመ/ቁጥር 7716/15 ላይ ተቀብሎ ሲመለከት ከቆዬ በኋላ ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም መርምሮ የተጠሪ

ፍቃድ ሳይኖር የተጠሪ የጋራ ንብረት የሆነውን ይዞታ በመሸጥ በተገኘው ሃብት የተሰሩት 3 ቆርቆሮ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶችን ተጠሪ ልትካፈል ይገባል፣ይግባኝ ባይ ደግሞ የንብረቱን ¼ ትካፈል ተብሎ በፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሠረት አድርጎ የተሰጠ በመሆኑ በውሳኔው ላይ ሴቶች መሬትን በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 35/7 ተደነገገውንም ሆነ በአንቀፅ 40/1 የይግባኝ ባይን ንብረት የማፍራት ሕገ-መንግስታዊ መብት ጥስት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው የሕገ-መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የይግባኝ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘትም ባጭሩ ሲታይ፡- ይግባኝ ባይ እንደማንኛውም በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል እንደምትኖር ሴት በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ ከነበሩት ከባለቤቱ አቶ ዘለቀ አሸንጎ ጋር በ1984 ዓ.ም ስንጋባ የአሁኖቹ አከራከሪ ቤቶች ያልነበሩ ሲሆን አሁን በምንኖርበት ቦታ ላይ አንድ ዳሳሳ ጎጆ ቤት ሰርተን ነበር፡፡

በኋላም ይግባኝ ባይ ቀደም ሲል ስሰራ የነበረውን አረቄ በማውጣት፣ ቡና በማፍላት እና ደረቅ እንጀራ በመነገድ እንዲሁም በጋብቻ ውስጥ በተከልናቸው ባህርዛፍና ቡና ከምናገኘው ገቢ አከራካሪዎቹን 3 ቆርቆሮ ቤቶችን ከ2000 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ባለው የተለያዩ ጊዜያት በላቤና በጉልበቴ ስለማሰራቴ በሰው ማስረጃ ከበቂ በላይ አስረድቼ አለሁ፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ቦታ ላይ ገብቼ ከ27 ዓመታት በላይ ስኖር ተጠሪ በድንበርም ሆነ በጉርብትና አብራኝ ያልነበረችና አሁንም የማትኖር ከመሆኑም ባለፈ ከአቶ ዘለቀ አሸንጎ ጋርም በደርግ ዘመን ጦር ሜዳ ከሄደበት ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ከ42 ዓመታት በላይ አብረው እንደማይኖሩ በቀረቡት የተጠሪ ማስረጃም ሆነ የአካባቢው ሽማግሌዎች ጭምር በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ እያለ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40/3 መሰረት የመሬት ባለቤትነት የመንግስትና የህዝብና ብቻ ሆኖ በመሬት ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ማሻሻያዎችም ሆኑ የሚፈራው ንብረቶች የግለሰቡ በመሆናቸው ይግባኝ ባይ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በባለቤቱ ስም ተመዝግቦ ግብር በሚገበርበት ይዞታ ላይ እንደሚስት በጉልበቴና ገንዘቤ በጋብቻ ውስጥ በመሬቱ ላይ ላፈራሁት ግማሽ ደርሻ ሲገባኝ በተቃራኒው ለነዚህ ንብረቶች አስተዋፆኦ ላላበረከተችው ተጠሪ ግማሽ ድርሻ ይገባታል ተብሎ ያለአግባብ እንድትበለፅግ ተደርጓል፡፡

አከራካሪው ይዞታ ወደ ከተማ አስተዳደር የተካለለ ቢሆንም ገና የከተማ ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያልወጣለት በመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የሚመራ ሲሆን በአዋጅ ቁ.110/99 መሠረት የገጠር መሬት ተጠቃሚ መሆን የሚችለው የቤተሰብ አባል ስለመሆኑና የቤተሰብ አባል የሚባለው ደግሞ የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ሰው ብቻ ስለመሆኑ በአስገድጅነት በግልፅ የተደነገገ ሲሆን ይግባኝ ባይ በህጋዊ መንገድ በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ ከሆነው ባለቤቱ ጋር ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ በቆየንባቸው ጊዜያት በቋሚነት አብረን በመኖር እንደቡና እና ባህርዛፍ ያሉትን በመትከል አብረን የምንጠቀም የቤተሰብ አባል ስንሆን ተጠሪ ግን አቶ ዘለቀ አሸንጎ ጋር ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ አብረው ያልኖሩና በይዞታው ለይ የመጠቀም መብታቸው ካቆሙ በትንሹ 27 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ሆኖ እያለ ለሁለት አስርት ዓመታት ያልተጠቀመችበትን ንብረት ለዛውም ግማሹን እንድትካፈል የተሰጠው ውሳኔ የህጉን ዓላማና መሠረታዊ ድንጋጌዎችን ያልተከተለ ከመሆኑም ባለፈ የይግባኝ ባይን ንብረት መብት የሚጋፋ በመሆኑ፤

በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.75/96 አንቀፅ 78 መሠረት አንደኛው ተጋቢ የሌላኛውን ተጋቢ ፈቃድ ሳይጠይቅ የውል ግዴታ የገባ እንደሆነ ፈቃድ ያልሰጠው ተጋቢ ግዴታው ቀሪ እንዲሆን በፍ/ቤት መጠየቅ የሚኖርበት ግዴታው መኖሩን ባወቀበት በ6 ወር ውስጥ አልያም በማናቸውም ሁኔታ በ2 ዓመት ውስጥ ካልቀረበ ሊቀርብ እንደማይችል ተደንግጎ እያለና በአንቀጽ 58 እና 62 መሠረት በተጋቢዎች መካከል ሊኖር የሚገባው የመከባበር፣ መተጋገዝ፣ የመደጋገፍና አብሮ የመኖር ግዴታ በተጠሪና በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ በነበሩት አቶ ዘለቀ አሸንጎ መካከል ሳይኖር የጋብቻ ፅንሰ ሃሳብን በሚያሳካ መልኩ አብረው ሳይኖሩና ሳይተጋገዙ ንብረት ለመካፈል ብቻ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ይዞታ ላይ ይግባኝ ባይ ስኖርና ሳስተዳደር አንድም ቀን ጥያቄ ሳይቀርብ አሁን ከጋብቻ ፍቺ በኋላ የንብረት ክፍፍል ሲጠየቅ የቀረበው ቅሬታና በቅሬታው መሠረትም ተጠሪ የንብረቱ ግማሽ ድርሻ ይገባታል በሚል የተሰጠው ውሳኔ የክልሉን የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 78 ድንጋጌን መሠረት ያላደረገና የይግባኝ ባይን የንብረት መብት የሸራረፈ በመሆኑ፤ እንዲሁም

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን በሚመለከት በሰ/መ/ቁ.50489 (ቅፅ 11) ላይ በግልፅ ባል ሁለት ሚስቶችን አግብቶ የሚኖር በሆነ ጊዜ በመካከላቸው የሚፈራ ንብረት ለተጋቢዎች ሊከፋፈል የሚችልበት አግባብ ሚስቶች ጋብቻ እንደተፈጸመ ከሚቆጠርበት ጊዜ ጀምሮ ከባል ጋር ያፈሩት ሃብት ብቻ ለመካፈል ይችላሉ

በማለት አስገዳጅ ትርጉም የሰጠበት ከመሆኑም ባለፈ በተመሳሳይ ቅፅ የሰ/መ/ቁ.43988 ላይ ጋብቻ ሳይፈርስ የትዳር ግንኙነትን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት የተፈራውን ንብረት የጋብቻ ውጤት ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ በጋብቻ ወቅት የተፈራ ንብረት የጋራ ይሆናል የሚለውን የህግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም በማለት የሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 40/1 ድንጋጌ ጭምር በመጥቀስ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶ እያለ በዚህ ውሳኔ መሠረት ለይግባኝ ባይ ግማሽ ንብረት ሊደርስ ሲገባ ተጠሪ ባልለፋችበት ግማሽ ድርሻ ይገባታል ተብሎ መወሰኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅነት ያላቸውን የሰበር ውሳኔዎችን ያልተከተለ ከመሆኑም ባለፈ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 25 መሠረት የዜጎችን በሕግ ፊት እኩል የመዳኘት መብትን የሚቃረን በአጠቃላይም ውሳኔው ይግባኝ ባይ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40/5፣ 40/1 እና 40/1 መሠረት የተረጋገጠልኝን በጉልቤቴና በገንዘቤ ያፈራሁትን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያሳጣ እና ከቦታ የሚያፈናቅል ከሕገ-መንግስቱ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ምክር ቤቱ ቅሬታዬን በጥልቀት በመርመር ውሳኔው የሕገ-መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ይወስንልኝ የሚል ነው።

<u>በቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ የተሰጠ አስተያየት፣</u>

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኙ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ተጣሱ ከተባሉት የሕገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም ከሚለው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ የነበሩት አቶ ዘለቀ አሸንጎ የአሁን ተጠሪን አግብቶ እየኖረ እያለ በ1969 ዓ.ም አከባቢ ወደ ውትድርና ሲሄድ በወቅቱ ለዘማች ቤተሰብ በሚል ለአሁኑ ክርክር መነሻ ሆነው 1 ሄክታር ይዞታ በተከሳሹ ስም ለተጠሪ መሰጠቱን፤ በዚህ ይዞታ ላይ በወቅቱ የነበሩት የቀበሌ አመራሮች ተጠሪን በመደገፍ የቀበሌውን ማህበረሰብ አስተባብረው ቡናና ባህርዛፍ የመሳሰሉትን ያስተከሉላት መሆኑን፤ በዚህ አግባብ ተጠሪ ይዞታውን አልምታ ከልጆቿ ጋር እየተጠቀመች እያለች ተከሳሽ ከውትደርና ከተመለሰ በኋላ ይ/ባይን አግብቶ ወደ ይዞታው በማምጣት ተጠሪ ብትቃወምም ተጠረን በማስፋራራት እምቢተኛ ሆኖ በጉልበት ይ/ባይን ያኖረበት መሆኑን፤ ከዚህ በኋላም ከይዞታው ላይ ይ/ባይና የስር ተከሳሽ እየቆረሱ በመሸጥ ከሸያጩ በሚገኘው ገቢ አከራካሪዎቹን ቤቶች የሰሩ መሆኑን፤ ቦታው እየተቆረሰ በሚሸጥበት ወቅት ተጠሪና ቤተሰቦቿ ጭምር ሲቃወሙ የነበሩ ቢሆንም ተከሳሽ ግን የተጠሪን

በቤተሰቦች ጭምር በቆንጫራ በማባረር እና በማመፅ ይሸጥ ነበረ መሆኑ ለስር ፍ/ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች በፍሬ ነገር ረገድ በግልፅ የተረጋገጡ ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ይ/ባይ አከራካሪው ይዞታ ለተከሳሽ ተመርቶ ጫካ የነበረውን ራሳችን አልምተንና አከራካሪዎቹን ቤቶች ደግሞ አረቄ በማውጣት፣ ቡና በማፍላትና ደረቅ እንጀራ በመጋገር ከሚገኘው ገቢ በላቤና በጉልበቴ ያሰራሁት ነው በማለት ቅሬታ ያቀረበች ቢሆንም በፍ/ቤት ደረጃ በነበረው ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ይዞታው በተከሳሽ ስም ለተጠሪ ተሰጥቶ አልምታ እየተጠቀመችበት እያለ ተከሳሽ በጉልበት ይ/ባይን በይዞታው ላይ ካገባት በኋላ ተጠሪና ቤተሰቧቿ ጭምር እየተቃወሙ በጉልበት ይዞታውን በመሸጥ ከሚገኘው ገቢ ቤቶቹ የተሰሩ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ይ/ባይ አሁን ንብረቶቹን ያፈራሁት በጉልበቴና በግል ገንዘቤ ነው በማለት የምታቀርበው ክርክር በፍ/ቤት ደረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይ/ባይ ተከሳሽና ተጠሪ ተከሳሹ በ1969 ዓ.ም ጦር ሜዳ በመሄዱና ከተመለሰም በኋላ አብረው ኖረው የማያውቁ በመሆኑ በተጋቢዎች መካከል ሊኖር የሚገባው የመከባበር፣ መደጋገፍና አብሮ የመኖር ግዴታን ሳይወጡና በዚህም የጋብቻን ፅንሰ ሃሳብ የማያሳኩ ሆኖ እያሉ አሁን በይ/ባይ እና ስር ተከሳሽ ከጋብቻ ፍቺ በኋላ የንብረት ክፍፍል ሊያደርጉ ሲሉ ንብረት ለመካፈል ብቻ የቀረበው ጥያቄ ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 78/2 ደንጋጌን መሠረት ያላደረገ ነው የሚል ክርክር ነጥብ ያነሳች ቢሆንም ይ/ባይ በተጠሪና የስር ተከሳሽ መካከል አስቀድሞ ጋብቻ የነበረ መሆኑን ሳትክድና ይህም ጋብቻ ስለመፍረሱ ምንም አይነት አስረጂ ሳታቀርብ አብረው አይኖሩም በሚል ምክንያት ብቻ የምታነሳው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በፍ/ቤት ደረጃ በነበረው ክርክርም ቢሆን ተጠሪ የስር ተከሳሽ ሚስት መሆኗ አከራካሪ ያልነበረ ጉዳይ ከመሆኑም ባለፈ የስር ተከሳሽ ለይ/ባይ ክስ በሰጠው መልስ ላይ ተጠሪ የመጀመሪያ ሚስቱ መሆኗንና አከራካሪዎቹ ንብረቶችም የእርሷ መሆኑን በመጥቀስ ጭምር ሲከራከር የነበረ መሆኑ ሲታይ ተጠሪና የስር ተከሳሽ አብረው የማይኖሩና ባልና ሚስትም ያልሆኑ ናቸው ለማለት የሚያስችል ምንም አይነት የህግ መሰረት የሌለ ነው፡፡

በአከራካሪዎቹ ንብረቶች ክፍፍል ረገድ ያለው ጉዳይም ሲታይ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው አከራካሪዎቹ የቡቡ እና ባህር ዛፍ ልማት ያለባቸው ይዞታዎች የተፈሩት ይ/ባይ የስር ተከሳሽን

ከማግባቷ በፊት በተጠሪና የስር ተከሳሽ ጋብቻ ወቅት የተፈራ ሲሆን አከራካዎቹ ቤቶች ደግሞ የተጠሪና የስር ተከሳሽ በጋብቻቸው ወቅት ያገኙት ይዞታ ተቆርሶ ከተጠሪዋ ፍላጎት ውጭ በጉልበት እየተሸጡ በተገኘው ገቢ የተሰሩ በአጠቃላይም የንብረቶች ዋነኛ ምንጭ የተጠሪና የስር ተከሳሽ የጋራ ሃብት የሆነው የመሬት ይዞታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ከንብረቶቹ ላይ ግማሹ ድርሻዋን ከወሰደች በኋላ የሚቀረውን ግማሽ ድርሻ ይ/ባይ እና የስር ተከሳሽ ይካፈሉ መባሉ ከግራ ቀኙ ወገኞች መካከል አከራካሪዎቹን ንብረቶች በማፍራት ረገድ የግል ገንዘቡን፣ ጉልበቱንና ዕውቀቱን ያበረከተበትን ወገን መብት በአግባቡ የጠበቀ ከመሆኑም ባለፈ ሴቶች መሬትን በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸውና ወንዶችና ሴቶች በጋብቻ ዘመንና በጋብቻ ፍቺ ጊዜ እኩል መብት በሚል በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 35(7) እና 34(1) ላይ ከተደነገገው አካያ የተጠሪን ሕገ መንግስታዊ መብት ያከበረ ነው ከሚባል በስተቀር የይ/ባይን የንብረት መብት የጣሰ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የተጠሪ ግማሽ ድርሻ ያለበት ይዞታንና ከዚሁ ይዞታ ላይ ከፈቃዷ ውጭ በጉልበት በመሸጥ ከተገኘ ገቢ የተፈሩትን ንብረቶች ላይ ተጠሪ የግማሽ ድርሻ መብት አላት በሚል በፍ/ቤቶች ተሰጠው ውሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነው ከሚባል በስተቀር ይ/ባይ ተጣሱብኝ የምትላቸውን ሕገ መንግስታዊ የንብረት መብትና ከይዞታ ያለመፈናቀል መብት ደንጋጌዎችን የጣሰ አይደለም፡፡

ስለሆነም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔም የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው ትርጉም አያስፈልገውም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥ፡፡